አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ተግባቦት ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን የመማር ብልሃቶች ትንተና
## (በሩፍሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)

በ ያሲን አደም ጌታነህ

ሐምሌ 2015 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

# በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን የመማር ብልሃቶች ትንተና

(በሩፍሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ተግባቦት ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር


አማርኛን ለማስተማር ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት


የጥናቱ አማካሪ

ዳዊት ፍሬህይወት (ዶ/ር)

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

# የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ተግባቦት ኮሌጅ

# የአማርኛ ቋንቋ፣ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

# የድህረምረቃ መርሃግብር

ይህ "በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን የመማር ብልሃቶች ትንተና (በሩፍሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)" በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ፣ በያሲን አደም ጌታነህ የቀረበው ጥናት የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና ወጥነት መስፈርት ስለማሟላቱ በፈተና ቦርድ አባላት ተረጋግጦ ተፈርሟል፡፡

## የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ ስም ------------------------------------ፊርማ -------------ቀን................

የውጭ ፈታኝ ስም-------------------------------ፊርማ--------------ቀን...................

የውስጥ ፈታኝ ስም-------------------------------ፊርማ---------------ቀን.....................

# የአጥኚው ማረጋገጫ

ይህ “በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን የመማር ብልሃቶች ትንተና” በሚል ርዕስ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲ፣የቋንቋዎች ጥናት የጋዜጠኝነትና ተግባቦት ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ስነ-ፅሑፍ ፎክሎር ትምህርት አማርኛን በማስተማር ለኤም.ኤ.ዲግሪ በከፊል ማሟያነት ያቀረብኩት ጥናት፣ ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ የራሴ ወጥ ስራ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢዎች የተደረጉና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም የጥናቱ ህጋዊ ባለቤት መብት ያለው መሆኑን በፊርማየ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም……………………………………………….

ፊርማ……………………………………………..

ቀን …………………………………………………...

## ምስጋና

በመጀመርያ ለዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ሙሉ ጤናየን ሰጥቶ ለፍጻሜ እንዲደርስ ላደረገኝ ለአላህ ሱብሃነ ወተዓላ ላቅያለ ምስጋና አቅርቤያለሁ፡፡

በመቀጠል ይህን ጥናት ከመጀመርያ እስከ መጨረሻ በጥልቀት ደጋግመው በማንበብ አስፈላጊና ወሳኝ የሆኑ ሃሳቦችን በመጠቆም፣ ሰዋሰዋዊም ሆኑ የሆህያት ግደፈቶችን በማቅናትና በማረም፣እንዲሁም ጥናቱ አሁን የደረሰበት ደረጃ ቅርጽ እንዲይዝ ፈጣን ምላሽ በመሰጠት በብዙ ሁኔታዎች ላገዙኝና ለተባበሩኝ አማካሪየ ዳዊት ፍሬህይወት (ዶ/ር) ምስጋናየ ልባዊና ለየት ያለ ነው፡፡

በመቀጠል ስራየ የተቃና እንዲሆን የተለያዩ ቁሳቁሶችን በመስጠትና ሙያዊ እገዛ ላደረጉልኝ መምህራን አቶ አህመድ እሸቱ፣ አቶ ሰይድ መንገሻ፣ሀቢብ አሊ፣መሀመድ መኪንና ሙሃመድ ሰይድ ልባዊ ምስጋና ይድረሳቸው፡፡ ለጥናቴ የሚጠቅሙ አስተያየቶቸን፣ ጽሁፎችንናመጽሀፍትን በመስጠት በፍቃደኝነት ለተባበርከኝ ለመምህር አህመድ እሸቱ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

በመጨረሻ ይህ ጥናት በስኬት እንዲጠናቀቅ ከጎኔ በመሆን ላበረታታችኝ ውዷ ባለቤቴ መ/ርት ኑሪት ወንድየ ምስጋናየ ወደር የለውም፡፡ እንዲሁም በቅንነት መረጃ በመስጠት ለተባበሩኝ የሩፍሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት የአስረኛ ክፍል ተማሪዎችና የገንዘብ ድጋፍ ላደረገልኝ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ላቅ ያለ ምስጋናየን አቀርባለሁ፡፡

# የይዘት ማውጫ

**ይዘቶች** **ገፅ**

ምስጋና.................................................................................................... IV
የይዘት ማውጫ.................................................................................................... V
ሰንጠረዥ ማውጫ ................................................................................................ VIII
የአባሪዎች ማውጫ................................................................................................ IX
አጠቃሎ .................................................................................................... X
ምዕራፍ አንድ ....................................................................................................11
መግቢያ....................................................................................................11
1.1 የጥናቱ ዳራ ....................................................................................................11
1.2 የጥናቱ መነሻ ችግር....................................................................................................14
1.3 የጥናቱ ዓላማ....................................................................................................15
1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ ....................................................................................................15
1.5 የጥናቱ ወሰን(ገደብ)....................................................................................................16
1.6 የጥናቱ ውስንነት ....................................................................................................16
ምእራፍ ሁለት
ክለሳ ድርሳናት ....................................................................................................18
2.1 የቃላት ምንነት ....................................................................................................18
2.2 የቃላት ትምህርት ....................................................................................................19
2.3 የቃላት ትምህርት አስፈላጊነት ለሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት..........................................20
2.4. የቋንቋ መማር ብልሃቶች ምንነትና ጠቀሜታ ..........................................................22
2.5 የቋንቋ መማር ብልሃቶች አመዳደብ ....................................................................24
2.6 የቃላት መማር ብልሃቶች ምንነትና አስፈላጊነት ..........................................................30
2.7 የቃላት መማር ብልሃቶች አመመዳደብ....................................................................31
*2.7.1 የ Hedge የቃላት መማር ብልሃቶች አመዳደብ* ..................................................32
2.7.2 የ *Nation ቃላት መማር ብልሃቶች ምደባ* ........................................................33

2.7.3 የ Pemberton የቃላት መማር ብልሃቶች አከፋፈል...34
2.7.4 የOxford ቃላት መማር ብልሃቶች አመዳደብ...35
2.7.4.1 ቀጥተኛ ቃላትን የመማር ብልሃቶች...35
2.7.4.1.1 የትውስታ ብልሃቶች...35
2.7.4.1.2 አዕምሮታዊ ብልሃቶች...37
2.7.4.1.3 አካካሽ ብልሃቶች...38
2.7.4.2 ኢ-ቀጥተኛ ብልሃቶች...38
2.7.4.2.1 ልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶች...39
2.7.4.2.2 ስሜት ነክ ቁጥጥር ብልሃቶች...40
2.7.4.2.3 ማህበራዊ ብልሃቶች...41
2.8 ቀደምት ተዛማጅ ጥናቶች...43
ምዕራፍ ሦስት...47
የጥናቱ ንድፍና ዘዴ...48
3.1 የጥናቱ ንድፍ...48
3.2. የናሙና አመራረጥ...48
3.2.1 የክልልና የወረዳ የናሙና አመራረጥ...48
3.2.2 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ...48
3.2.3 የክፍል ደረጃ አመራረጥ...49
3.2.4 የተማሪዎች የናሙና አመራረጥ...49
3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች...50
3.3.1 የጽሑፍ መጠይቅ...50
3.3.2 ቃለ መጠይቅ...51
3.4 የመረጃ አተናተን ዘዴ...51
ምዕራፍ አራት...52
የመረጃ ትንተና እና የውጤት ማብራሪያ...52
*4.1,የቀጥኛ ብልሃቶች ትንተና*...52
4.1.1 የትውስታ ብልሃቶች ውጤት ትንተና...52
4.1.2 የአዕምሮታዊ ብልሃቶች ትንተና...56

4.1.3 የአካካሽ ብልሃቶች ትንተና ........................................................................64
4.2. ኢ-ቀጥተኛ የመማር ብልሃቶች መረጃ ትንተና ..........................................................67
4.2.1 የልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶች ትንተና ......................................................................67
4.2.2 የስሜት ነክ ቁጥጥር መረጃ ትንተና .......................................................................69
4.2.3 የማህበራዊ ብልሃቶች መረጃ ትንተና .....................................................................72
4.3 የውጤት ማብራሪያ ...............................................................................................73
ምዕራፍ አምስት ........................................................................................................77
ማጠቃለያ፣መደምደሚያና አስተያየት ..............................................................................77
5.1 ማጠቃለያ ...............................................................................................................77
5.2 መደምደሚያ ............................................................................................................81
5.3. አስተያየት ...............................................................................................................82
ዋቢመጻህፍት ...............................................................................................................84
አባሪዎች ......................................................................................................................91

# ሰንጠረዥ ማውጫ

ሰንጠረዥ1:- ማቧደንን የሚጠይቁ የትውስታ ብልሃቶች ላይ ያሳዩት አጠቃቀም .................... 52

ሰንጠረዥ 2:-ማያያዝና በድርጊት ማሳየትን በሚጠይቁ ብልሃቶች ላይ ያሳዩት አጠቃቀም...... 54

ሰንጠረዥ3:- መደጋገምን በሚጠይቁ የአዕምሮታዊ ብልሃቶች ላይ ያሳዩት አጠቃቀም............ 57

ሰንጠረዥ 4:- ምንጭን መጠቀም በሚጠይቁ ብልሃቶች ላይ ያሳዩት አጠቃቀም መረጃ ትንተና ........................................................................................................................ 59

*ሰንጠረዥ 5፡- መተርጎምንና ንበትን መለማመድ በሚጠይቁ ብልሃቶች ላይ ያሳዩት አጠቃቀም* ........................................................................................................................ 61

*ሰንጠረዥ 6፡- ማስታወሻ መውሰድን፣ ትኩረት ቃል ድምቅታንና ተፈጥሮአዊ ልምምድን የሚጠይቁ ብልሃቶች ላይ ያሳዩት አጠቃቀም*.............................................................. 62

ሰንጠረዥ 7:- የአካካሽ ብልሃቶች ጥቅል ትንተና ................................................................ 65

ሰንጠረዥ 8:- ልዕለ አዕምሮታዊ መረጃ ትንተና ................................................................ 67

ሰንጠረዥ 9፡- የስሜት ነክ ቁጥጥር ብልሃቶች ትንተና ......................................................... 70

ሰንጠረዥ 10:- የማህበራዊ ብልሃቶች ጥቅል መረጃ ትንተና ................................................ 72

# የአባሪዎች ማውጫ

አባሪ 1:- በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበ የጽሁፍ መጠይቅ ...................................................... 81

አባሪ 2፡- ለአስረኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበ  ቃለመጠይቅ............................................................ 89

አባሪ 3፡- በኦሮምኛ ቋንቋ የቀረበ የጽሁፍ መጠይቅ......................................................................... 98

አባረ 4፡- በኦሮምኛ ቋንቋ የቀረበ ቃለ መጥይቅ................................................................................. 103

አባሪ 5 ፡- የተተኳሪ ተማሪዎችን ዳራ የሚያሳይ ቅጽ.................................................................... 97

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት አብይ አላማ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የቃላት መማር ብልሃቶችን መለየትና መተንተን ነበር፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች በሩፍሴ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2015 ዓ.ም ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ የሚገኙ በአመቺ ንሞና ዘዴ የተመረጡ 70 የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ የጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችም፡- የጽሁፍ መጠይቅ በዋናነት ሲሆን ቃለመጠይቅ በአጋዥ የመረጃ መሰብሰቢያነት ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ እነዚህ መረጃዎችም በአይነታዊና መጠናዊ የመረጃ መተንተኛ ተተንትነው ገላጭ በሆነ ስልት ቀርበዋል፡፡ በውጤት ትንተናው መሰረትም በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን የሚለማመዱበት ስልት ቃላትን የመማር ብልሃት አጠቃቀማቸው በብቃት ላይ የተመሰረተ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ተጠኚ ተማሪዎች በትውስታ ብልሃት ስር ከቀረቡላቸው ስድስት ብልሃቶች አብዛኞቹ 177(252.9%)ያህልጊዜ በመደጋገም አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ ተረጋግጧል፡፡ አዕምሮታዊ ብልሃቶችን በተመለከተ ለተማሪዎች ከቀረቡላቸው አስራአንድ ጥቅል ብልሃቶች አብዛኞቹን ብልሃቶች 425(607%)ያህል ጊዜ ብልሃቱን በመደጋገም አልፎ አልፎ ተጠቅመዋል፡፡ በአንጻሩ ደግሞ አካካሽ ብልሃቶችን በተመለከተ 101(144.3%)ያህል ጊዜ ደጋግመው ሁልጊዜ እንደተጠቀሙ ሲገልጹ፣ ልዕለአዕምሮታዊ ብልሃቶችን ደግሞ 122(174.2%) ያህልጊዜ ደጋግመው አልፎአልፎ እንደሚጠቀሙ መረጃው ያመለክታል፡፡ በተመሳሳይ መልኩም በስሜትነክ ቁጥጥር ብልሃቶች ስር ከቀረቡላቸው ሶስት ብልሃቶች አብዛኞቹ ተማሪዎች144(205.5%) ጊዜ በመደጋገም አልፎ አልፎ ሲጠቀሙ፣ ማህበራዊ ብልሃቶችን በተመለከቱ ደግሞ 61(87.1%) ያህል ጊዜ አልፎ አልፎ በመደጋገም እንደሚጠቀሙባቸው የትንተናው ውጤት ያሳያል፡፡ በመሆኑም ተጠኚ ተማሪዎች በተደጋጋሚ አብዝተው የሚጠቀሙት አካካሽ ብልሃቶችን ሲሆን ሌሎቹን ብልሃቶች ግን ሁልጊዜ በመደጋገም አብዝተው እንደማይጠቀሙባቸው ውጤቱ ያሣያል፡፡ እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተማሪዎች በራሳቸው ጥረት እንዲለማመዱ መንገድ ቢያመቻቹላቸውና ክትትል ቢያደርጉ፣ እንዲሁም የአማርኛ መማርያ መጽሐፍ አዘጋጆች የቃላት መማር ብልሃትን እንደ አንድ የቃላት ትምህርት ማቅረቢያ መንገድ ቢጠቀሙበት የሚልየመፍትሄሀሳቦችተጠቁመዋል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

በመማር ማስተማሩ ሂደት በተለይም በሁለተኛ ቋንቋ በሚደረጉ መስተጋብሮች ተግባቦቱ የቀለጠፈና የዳበረ ይሆን ዘንድ የቃላት እውቀት የጎላ ሚና አለው፡፡ ስለዚህ ሁለተኛ ቋንቋን ለመማር በዋናነት ለቃላት ትኩረት መስጠት አለበት፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች በተግባቦት ሂደት ልምዳቸውን፣አላማቸውን፣ ፍላጎታቸውን፣ ድርጊታቸውንና ሐሳባቸውን በተመለከተ የታቀደውን አላማ በትክክለኛ መንገድ ለሰዎች ለማስተማርም ሆነ ለመልመድ የቃላት እውቀታቸው ትልቅ አስተዋጽኦ አለው (McCrostie, 2007; Read, 2000; Nation, 2001)፡፡ ኢ-አፍፈት ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋቸው ሀሳባቸውን ማስተላለፍ ፈልገው የቃላት እጥረት ሲያጋጥማቸው በተግባቦት ሂደት የሚያሣድርባቸው የፍርሃት ስሜት ከፍተኛ መሆኑንና በቋንቋው ላይ አሉታዊ አመለካከት እንደሚያሳድርባቸው Nyikos & Fan (2007) አስረድተው በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የቃላት እውቀትን ማዳበራቸው ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳለው ገልጸዋል፡፡

ኢ-አፍፈት ተማሪዎች በንግግርም ሆነ በጽሁፍ ሀሳባቸውን ሲገልጹ የሚያጋጥማቸው የቃላት እውቀት ማነስ ነው፡፡ የዚህ ጥናት አጥኚም በመምህርነት ሙያ በተከታታይ ለአስር አመት ባካበተው ልምድ መሰረት አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ በተለይም አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች ችግር ነው የሚል እምነት አለው ፡፡ ተማሪዎች አማርኛን በአብዛሀኛው የሚጠቀሙት በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ነው፡፡ ወደ ትምህርት ቤት ሲመጡና ሲመለሱ ፣በቤታቸውና በአካባቢያቸው የሚጠቀሙት የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን በመሆኑ የታላሚውን ቋንቋ ቃላት የመለማመድ ሰፊ ዕድል የላቸውም፡፡ በተለይም ቃላትን የመማር ብልሃቶች በብቃት አለመጠቀም፣ ለተማሪዎቹ የቃላት ዕውቀት ማነስ ሊሆን ይችላል በሚል አጥኚው ጥናቱን ለማካሄድ ተነሳስቷል፡፡

የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ቃላት የቋንቋ ብቃትንና በአጠቃላይ ትምህርታዊ ስኬታማነትን ለመተንበይ ዋነኛ መሳሪያ ናቸው (Vermeer, 2001; Harmer, 1991)፡፡ ተግባቦታዊ ክንውን

ዘወትር የሚደናቀፈውም ተገቢ ቃላትን በትክክል በተገቢው አውድ ባለመጠቀም ነው፡፡ ከዚህም ያለ በቂ የቃላት እውቀት ብልሃት እና ልምድ እየዳበረ ሲሄድ መምህሩን ከመጠበቅ ተላቀው በመማርያ ክፍል ውስጥ ሆነ ውጭ በራሳቸው ጥረት ቃላትን ለመማር ይረዳቸዋል ፡፡

በሌላመልኩም Bornay (2011) በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ታሪክ ውስጥ አብዛሀኛዎቹ የቋንቋ ማስተማርያ ዘዴዎች ለሰዋሰው ትምህርት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠታቸው የቃላት ትምህርት የተዘነጉ ነበሩ፡፡ አያይዘውም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ተማሪዎች በራሳቸው ጥረት የቃላት እውቀታቸውን እንድያዳብሩ እንደማይበረታቱ በተለይም በሁለተኛ ቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ለረጅም ዓመታት የቃላት ትምህርት ትኩረት እንዳልተሰጠውና ተዘንግቶ እንደነበር ገልጸዋል፡፡

የቋንቋ መማር ብልሃቶች ሁለተኛ ቋንቋ ለመማር የቋንቋ ክህሎትን ማለትም ማዳመጥን፣ መናገርን፣ ማንበብን እና መጻፍን ለመማር እና የመሳሰሉትን በርካታ ክሂሎች ለመማር የሚረዱ ተብለው ተለይተው በዓይነት ተከፋፍለዋል:: ከነዚህም መካከል የዚህ ጥናት ትኩረት የሆኑት የቃላትመማር ብልሃት ዓይነቶች ይገኙባቸዋል፡፡ ከዚህ የተነሳም የዚህ ጥናት አቅራቢ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎችን ለበርካታ ዓመታት ሲያስተምር ችግር እንዳለ ተመልክቶ ስለነበር ትኩረቱን በዚህ ዙሪያ ለማድረግ ችሏል፡፡ አንድን ሀሳብ ለመረዳትም ሆነ መልዕክት ለሌላ ሰው ለማስተላለፍ ጥረት በሚደረግበት ሁኔታ ተማሪዎች የሚገለገሉባቸውን የቃላት መማር ብልሃቶች በሚተገብሩበት ግዜ ሙያዊ እገዛ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

ሙያዊ እገዛ ልጆች እድገት እንዲያሳዩና በራሳቸው መንገድ እንዲማሩ የሚደረግ ድጋፍ ወይም እገዛ ነው፡፡ ይህም ልጆች በሚያከናውኑት የመማር ሂደት የሚደረግ ማንኛውንም የመደገፍ ተግባር የሚመለከት ነው፡፡ በሌላ መልኩም ሙያዊ እገዛ በተናጠል በሚደረግ ተግባርና በሌሎች እገዛ በሚከናወን ተግባር መካከል ያለውን የእድገት መጠን ክፍተት ለመሙላት የሚከናወን ድጋፍ ነው፡፡ በመሆኑም የእድገት መጠን ክፍተትን ለመሙላት የሚከናወነው ይህ ሙያዊ ድጋፍ የእድገት መጠን ክፍተት የመፈጸሚያ ዋነኛ ስልት ነው (Lantolf, (2006) Oxford & Schraman, (2007) ፡፡

እንደ Macaro (2001) አገላለጽ ቃላት ቋንቋን ለመልመድና ለማፍለቅ በጣም መሰረታዊ ቢሆኑም የሁለተኛ ቋንቋ ቃላት ትምህርት ውጤታማ በሆነ መልኩ እንደት መቅረብ አለበት?

የሚለው ጥያቄ ለብዙ ጊዜ አወዛጋቢ ሆኖ መቆየቱን ገልጸዋል፡፡ ከአወዛጋቢነቱም የተነሳ የተሻለ የቃላት ማስተማሪያ ዘዴ ለመምህራን ማቅረብ አዳጋች ሆኖ መቆየቱን ገልጸዋል፡፡ መምህራኑም የተሻለ ዘዴ ባለመጠቀማቸው ምክንያት የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ተተኳሪውን ቋንቋ ለተግባቦታዊ አገልግሎት ለመጠቀም የቃላት ዕውቀታቸው ውስን ሆኖ ዘወትር ሲያማርሩና ቃላትን ለመማር ብዙጊዜ ሲያጠፉ እንደሚታዩ አስረድተዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ Atkins እና ሌሎች (1995:199) እንደገለጹት ብዙዎቹ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በተተኳሪው ቋንቋ የመጠቀም ሰፊ ዕድል የላቸውም፡፡ በቋንቋው የሚጠቀሙት በመማርያ ክፍል ውስጥ በሚማሩበት ወቅት ላይ የተወሰነ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ተማሪዎቹ ቋንቋውን ለተለያዩ ጉዳዮቻቸው ሲጠቀሙ በጣም ይቸገራሉ፡፡ በዚህ በጣም ውስን በሆነ አጋጣሚ ተማሪዎች የቋንቋ ትምህርታቸውን ውጤታማ ለማድረግ በራሳቸው ጥረት ቋንቋውን መማራቸው ወሳኝነት ይኖረዋል፡፡ ስለዚህ ተማሪዎቹ ለትምህርታቸው ኃላፊነትን ወስደው በመማርያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጭ በተለያዩ መንገዶች ራሳቸውን ለመርዳት መነሳሳት አለባቸው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከተለያዩ ምሁራኖች ሀሣብ ለመረዳት እንደሚቻለው በሙያዊ ድጋፍ የተሻለ እውቀት ያላቸው ሰዎች ከእነሱ ያነሰ ችሎታ ያላቸውን በማገዝ ክፍተቱን መሙላት ይቻላል፡፡ በተለይም ለሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪ ከጊዜ ወደ ጊዜ የእያንዳንዱን ቃል ፍች ከማስተማር ይልቅ ተማሪው በራሱ ጥረት አዳዲስ ቃላትን የሚለምዱበት ብልሃት እንዲያዳብሩ ማበረታታት ከፍተኛ አስተዋፅዖ አንዳለው ይጠቁማሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ኢ-አፍፊት የሆኑ ተማሪዎችን የሚያስተምሩ የቋንቋ መምህራን ውጤታማ የቃላት ትምህርት ለመስጠት በተሻለ መንገድ የቃላት ትምህርት የሚሰጥባቸውን ሂደቶችና ዘዴዎችን ከመገንዘብም አልፈው በተግባር ማሳየት ይጠበቅባቸዋል፡፡

በመሆኑም እነዚህ የቋንቋ መምህራን ቃላትን ሲያስተምሩ የተለመዱትን የቃላት ማስተማርያ ዘዴዎች ብቻ ስለሚጠቀሙ የተማሪዎች የቃላት ዕውቀትና ተግባቦት የዳበረ አይደለም፡፡ ምክንያቱም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቃላት መማር ብልሃቶችን በተደጋጋሚ ባለማስተማራቸውና ትኩረት ባለመስጠታቸው ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ጥናትም በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸው የፈቱ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን ሢጠቀሙ የሚችሉባቸውን የቃላት መማር

ብልሃቶች በመተንተን ያተኮረ ነው፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ ለጥናቱ መነሻ ችግር የሆኑ ነጥቦች ዘርዘር ባለና በተብራራ መልኩ ቀርቧል፡፡

## 1.2. የጥናቱ መነሻ ችግር

የዚህ ጥናት መነሻ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ቆይታቸው እንድማሩ ከሚያስገድዷቸው ምክንያቶች አንዱና ዋነኛው ተግባቦታዊ ብቃትን ማዳበር አስፈላጊ ነው፡፡ የቋንቋ ተማሪዎች አንብበው ለመረዳት ከጓደኞቻቸው እና ከመምህራቸው ጋር ተገቢውን መስተጋብር ይፈጥሩ ዘንድ የቃላት ዕውቀት ያስፈልጋቸዋል፡፡

ይህን አስመልክተው Little (1994;106) እንደገለጹት በቋንቋ አጠቃቀም ውስጥ ጎልቶ የሚታየው ችግር ቃላትን ረቀቅ ባለ መንገድ ማዋቀር ላይ ሳይሆን ቃላት እርሥ በርሣቸው ዝምድናን ፈጥረው ሊተላለፍ የተፈለገውን ፍች እንዴት ግልፅ እንዳደረጉ መረዳቱ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በተግባቦት ተግባር ላይ ብቁ ሁነው እንድገኙ ለማድረግ ለቃላት ትምህርት ልዩ ትኩረት መስጠት ነው፡፡ ከላይ በተነሳው ሀሳብ መሠረት የቃላት እውቀት ለሁለተኛ ቋንቋ አፍፈት የሆኑ ተማሪዎች በየትኞቹ ብልሃቶች እንደሚማሩ ለማጥናት ሲነሣ በመረጠው ርዕስ ዙርያ የተወሰኑ ጥናቶች ለማየት ሞክሯል፡፡

ከነዚህም መካከል ንጋቱ (2000) "በሲዳምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን ሲማሩ የሚጠቀሙባቸው ቃላትን የመማር ብልሃቶች ፍተሻ" በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ አማርኛን በማስተማር ለሁለተኛ ድግሪ ማሙያ የቀረበ ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ አላማም በሲዳምኛ አፋቸውን የፈቱ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን ሲማሩ የሚጠቀሙባቸውን ቃላትን የመማር ብልሃቶች መመርመር ነው፡፡ የጥናቱ ውጤትም ተማሪዋቹ የአማርኛ ቃላትን የመማር ብልሃቶች አጠቃቀም በብቃት ላይ የተመሰረተ አለመሆኑን ያመላክታል፡፡

በላይነሽ (2002) "በኦሮሚያ ክልል የመቱ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን ለመማር የሚገለገሉባቸው የመማር ብልሃቶች ፍተሻ" በሚል ርዕስ ሲሆን የጥናቱም ውጤት ተጠኚዎቹ ቃላትን ሢማሩ ቃላትን የመማር ብልሃት አጠቃቀማቸው ዝቅተኛ ነው፡፡ ይህ ጥናት ምንም እንኳ ከሁለቱም ጋር በርዕሱ ቢመሳሰልም ከትኩረት አቅጣጫ፣ከአላማና ከቦታ አኳያ ይህ ጥናት ይለያል፡፡

በአጠቃላይ በታዩት ጥናቶች ዙርያ ክፍተት መኖሩ እና አጥኚው ከ4 አመት በላይ በ1ኛ ደረጃ እና ከ6 አመት በላይ በ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ባስተማርኩባቸው አመታት የተለያዩ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ መምህራን ቃላትን የማስተማር ብልሃታቸው የአንደኛ ደረጃ ሆኑ የከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ቃላትን የመረዳት ችግር እንዳለባቸው ለመረዳት ችያለሁ። ይህ ችግር የተከሰተው ምናልባት ቃላትን የማስተማር ብልሀቶችን በተገቢው ሁኔታ ያለመጠቀም ችግር ሊሆን ይችላል በማለት በማሠቡ ነው።

ጠቅለል ባለ መልኩ ይህ ጥናት በተማሪዎቹ የቋንቋ ችሎታ እና በቃላት ብልሃት አጠቃቀማቸው መካከል ተጣጥሞነት መኖርና አለመኖሩን ለመመርመር እንዲሁም የቃላት ብልሃቶችን በብዛት መገልገል በቋንቋ ችሎታቸው ላይ ልዩነት ያሳያሉ ወይስ አያሳዩም የሚሉትን ለመጠቆም አሥቧል።

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን ለመማር የሚጠቀሙባቸውን የቃላት መማር ብልሃቶች መለየትና መተንተን ነው ። ከዚህ አጠቃላይ አላማ በመነሳት ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ይኖሩታል።

1. ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን በሚማሩበት ጊዜ የትኞቹን ብልሃቶች በተደጋጋሚ አብዝተው እንደሚጠቀሙ መለየት

2.በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በራሳቸው የአማርኛ ቃላትን የሚማሩበትን መንገድ ቃላትን የመማር ብልሃቶች በብቃት መጠቀም ላይ የተመሰረተ መሆን ወይም አለመሆኑን መመርመር

3. የተለያዩ ብልሀቶችን አብዝቶ መጠቀም ለሁለተኛ ቋንቋ መማር ያለውን ጠቀሜታ መመርመር

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

ከጥናቱ ግኝት ተማሪዎች ቃላትን በሚማሩ ጊዜ ስላላቸው የቃላት ብልሃት አይነቶች አጠቃቀም ውጤታማነትን በማስገኘት ወይም ባለማስገኘት ረገድ የሚኖረውን ሚና በተመለከተ

ስነትምህርታዊ አንደምታቸውን ስለሚጠቁም የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል፡፡

1.ለሥርዓተ ትምህርትና ለመጽሐፍት አዘጋጆች በቃላት ትምህርት ይዘት አዘገጃጀት ተግባር ላይ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀምን ከግምት ያስገባ እንድሆን ፍንጭ ይሰጣል፡፡

2.የሁለተኛ ቋንቋ ቃላት በመማር ሂደት አጋዥ የሆኑ ቃላትን የመማር ብልሃቶች እንድዘወተሩ ሃሳብ መስጠት

3. ለወደፊቱ በቃላት መማር ብልሃት አጠቃቀም ዙርያ ጥናት የሚያካሂዱ ተመራማሪዎች ካሉ ይህ ጥናት እንደ መነሻ ሆኖ ያገለግላል፡፡

4.ይህን ጥናት የሚያነቡ ተማሪዎች ቃላትን ለመማር የመምህራን ጥገኛ ከመሆን በራሣቸው የመማር ብልሃትን ተጠቅመው ውጤታማ እንድሆኑ ማስቻል ፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን (ገደብ)

ይህ ጥናት የሚካሄደው በአማራ ክልል በኦሮሚያ ብሔረሰብ ልዩ ዞን በደዋ ጨፋ ወረዳ በሩፍሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው፡፡ ጥናቱም በ2015 ዓ.ም በአሥረኛ ክፍል በመማር ላይ ከሚገኙ አፋቸውን በኦሮሞኛ ቋንቋ በፈቱ ከሁለት ክፍል ተማሪዋች በመውሰድ ብቻ ነው፡፡ ጥናቱ በመማር ማስተማር ዙርያ የሚገኙትን ችግሮች ሁሉ የሚዳስስ ሳይሆን አፋቸውን በኦሮሞኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቃላትን መማር ብልሃቶች ላይ ብቻ ያተኮረ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ጥናቱ ከተጠቀሰው ትምህርትቤትና ከተጠኚዎች ውጭ ያሉትን ተማሪዎች አያካትትም፡፡

## 1.6 የጥናቱ ውስንነት

ይህ ጥናት በሚካሄድበት ጊዜ ከተመራማሪውም ሆነ ከምርምሩ ሂደት አንጻር ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የጥናት ውስንነቶች ይታባቸዋል፡፡ ይኸውም አጥኚው ጥናቱን በሚያከናውንበት ጊዜ የተጠኚዎችን የአፍ መፍቻ ቋንቋ ስላለመደ መረጃ ለመሰብሰብ የተቸገረበት ሁኔታ ነበር፡፡ ተተኳሪ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት ስለሚማሩ ለቋንቋው ያላቸው አመለካከት መረጃ በሚሰበሰብበት ወቅት ችልተኝነት፣ የቃላት እውቀት ማነስና የብልሃቶችን

ምንነት ያለመረዳት ችግር ነበር። በእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ ያለውን የንሞና መጠን በመለየት በዚህ ጥናት ከተመረጡት ሰባ ተማሪዎች በላይ ከፍብሎ በስፋት ጥናቱ መካሄድ አለመቻሉ ውስንነቱን ያመለክታል።

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1 የቃላት ምንነት

የቃልን ምንነት በሚመለከት ወጥነት ያለው አንድ አይነት ብያኔ ባይገኝም የተለያዩ ምሁራን የየራሳቸውን ሀሳብ ለማስቀመጥ ሞክረዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል Schmitt (2000) ቃል የሚለው እሳቤ አንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ቃላት የተገነባና አንድ ነጠላ ፍች ያለው መሆኑን ገልጸው ሃሳባቸውን በምሳሌ ሲያጠናክሩ "ሞተ" ነፍሱ ወጣ"፣ ከዚህ አለም ተለየ "ወዘተ.የሚሉ ተመሳሳይ ፍችዎችን ቢያመላክትም የያዙት የቃላት መጠን የተለየ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ስለዚህ እንደ ምሁራኑ አባባል ቃል ነው ወይም አይደለም ለማለት ፍች መያዙ እንጅ የቃላት መጠኑ ብዛት መለኪያ እንዳልሆነ ያስገነዝባል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ Ur (1996:60) በበኩላቸው ሲያብራሩ ቃል ሲባል ከአንድ በላይ የሆኑ ድምጾች ተቀናጅተው የሚፈጥሩት ትርጉም ያለው የድምጾች ስብስብ ነው፡፡ በፈሊጣዊ አገላለጻቸውም ደግሞ ከመደበኛው ትርጉም የተለየ ፍች ሊኖራቸው የሚችሉ የድምጾች ስብስብ ቃላት ይባላል በማለት ገልጸዋል፡፡

ቃላት በንግግር ድምጾች ቅንብር አማካኝነት የሚከሰቱ፣ የተለያዩ ፅንሰ ሃሳቦችን ወክለው የሚቆሙ፣ በጭራሽ ወደ ሌላ አነስተኛ ክፍልፋዮች ሊከፋፈሉ የማይችሉ፣ ትርጉም አዘል ቅንጣቶች(አሃዶች)የቋንቋ ክፍሎች ወይም አካላት ናቸው( ታደስ 2004:110):: በሌላ በኩልም የቃላት ምንነትን በተመለከተ ባየ (2000፣72) ቃል ከምዕላድ በላይ የሆነ ትርጉም የሚሰጥና ራሱን ችሎ የሚቆም ወደ አነስተኛ ክፍሎች መከፋፈል የሚችል ከቃላት ክፍሎች ውስጥ ሊመደብ እንደሚችል ጠቅሰዋል:: አያይዘውም He (2010:11) "ቃላት የድምጾች ቅንጅት ሲሆኑ ይህም ቅንጅት በጽህፈት ጊዜም ሆነ በንግግር ጊዜ አንድን እሳቤ የሚወክልና ማግባባት የሚያስችል ትርጉምም አለው" ይላሉ፡፡ ይህም የቃላት ሚና በፅሁፍ ተነባቢነትና አንብቦ በመረዳት፣አንብቦ በመዝናናትና በመማር ሰኬታማነት ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ ያሳድራል፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ከምሁራን ሀሳብ ለመረዳት እንደሚቻለው ድምጾች ትርጉም አልባ ይሁኑ እንጅ በቋንቋው መዋቅር በስርዓት ከተሰደሩ ትርጉም አዘል የሆኑ ቃላት ይመሰረታሉ፡፡

የቃላትን አመሰራረት ስናይ ደግሞ የድምጾች፣የምዕላዶችና የቃላት የእርስ በርስ ቅንጅት ሊሆን ይችላል፡፡

## 2.2 የቃላት ትምህርት

ቃላትን ተማሪዎች እንድማሩ ማስቻል ለቋንቋ ትምህርት ውጤታማነት ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡ ምሁራን እንደገለጹት ከዚህ ቀደም ቃላት ትክክለኛው ቦታ አልተሰጣቸውም ፤የቃላት ትምህርት ብዙውን ጊዜ የሚሰጠው በሌሎች ክሂሎች ውስጥ ነው፡፡

ይህን አስመልክተው ደረጀ (2013:164) እንደገለጹት ማንኛውም የቋንቋ ተግባቦት እንዲኖር የቃላት እውቀት ወሳኝ ነው፡፡ የሚፈጥሯቸውን ቃላት ከነቅንጅታቸው ተገንዝበው በቃላት አማካኝነት የሚተላለፈውን መልእክት ለመረዳት መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚህ መሰረት በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ቃላት ሁልጊዜ ትኩረት የሚሰጣቸው ናቸው፡፡ የተማሪዎቹ የቃላት እውቀት ለማንበብ ፣ለመጻፍ፣ለማዳመጥ ሆነ ለመናገር እንዲሁም ለማሰብና ለማሰላሰል ወሳኝ ነው፡፡ የቃላት ትምህርት ተማሪዎች አንብበው በሚረዱት ላይ ተፅእኖ ያደርጋል፤ አንብበው ካልተረዱ በእውቀታቸው ላይ በማሰብና በማሰላሰል ዕድላቸው ላይ ሁሉ ጫና ያሳድርባቸዋል፡፡ ስለዚህ በትምህርት ቤት ይሁነኝ ተብሎ የቃላት ትምህርት ደረጃ በደረጃ እንዲሰጥና የተማሪዎቹ የቃላት እውቀት ክምችት እንዲያድግ ጥረት ይደረጋል፤ ወደ ፊትም መደረግ ያለበት አብይ ተግባር ነው በማለት አስረድተዋል፡፡

ከላይ ከምሁራኑ ሀሳብ ለመረዳት እንደሚቻለው ቃላትን ማስተማር ለቋንቋ ትምህርት ውጤታማነት በጣም አስፈላጊ አንደሆነና የቃላት አውቀት ለተግባቦትም ሆነ ሌሎች ትምህርቶችን ለመቅሰሚያነት እንደምንገለገልበት መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ቃላትን ትኩረት ሰጥቶ ከመደበኛው ቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ማስተማር ያስፈለገው ተማሪዎች በቂ የቃላት ክምችትና እውቀት ኖሯቸው ቋንቋውን በአግባቡ እንዲጠቀሙ ለማድረግ ነው pikulski & Templeton (2004)፡፡

በ17 ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መሰረት የጣለው ይህ የቃላት ትምህርት ሁኔታ እየተስፋፋና እያደገ ከመሄድ ይልቅ ጭራሹንም ለረጅም ጊዜ ተረስቶ ቆይቶ እንደገና ማንሰራራት የጀመረው ከ1970 ዎቹ ወድህ እንደሆነ በዘርፉ የተሰማሩት ምሁራን ይገልጻሉ ፡፡ ለቃላት ትምህርት ለረጅም ጊዜ ተረስቶ መቆየት በምክናየትነት ከሚጠቀሱት መካከል በስነ-ልሳን ዘርፍ ይሰጡ

ከነበሩት የተለያዩ የአመለካከት አቅጣጫዎች ይገኙባቸዋል፡፡ በተለይም ለቋንቋ ትምህርት ወሳኙ ሰዋሰዋዊ ስርዓትን ማወቅ እንጅ የቃላት ትምህርት ሽምደዳ አይደለም የሚለው ሰነልሳናዊ እሳቤ ለቃላት ትምህርት መዳከም መንስኤ ሊሆን ችሏል ማለት ነው፡፡ ለቋንቋ ትምህርት ውጤታማነት አገባብን እንጂ ቃላትን በማስተማር ጊዜ ማባከን አይገባም የሚለውን አስተሳሰብ የሚቃወሙና ለቃላት ትምህርት ድጋፍ የሚሰጡ ምሁራን ብቅ ማለታቸው አልቀረም ፡፡ የእነዚህ ምሁራን አስተሳሰብና እምነት ደግሞ ቋንቋን በማስተማር ሂደት በተለይ ተግባራዊ ሥነ-ልሳን (Applied Linguistics) የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ አያይዘውም የቃላት ትምህርት ከሰዋሰው ትምህርት ጋር አብሮ መሰጠት እንደሚችልም ያምናሉ (ታደሰ 2004:110)፡፡

በአጠቃላይ ከምሁራኖች ገለጻ መረዳት እንደሚቻለው የቃላት ትምህርት የሚያካትታቸው ጉዳዮች የተለያዩ መሆናቸውና ተማሪዎች የቃላት እውቀትን ትኩረት ሰጥተው እንዲማሩ እነዚህ ምሁራኖች በመሰረተ ሀሳብ ደረጃ ተመሳሳይ ጉዳዮችን እንደዳሰሱ መረዳት ይቻላል፡፡

## 2.3 የቃላት ትምህርት አስፈላጊነት ለሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት

በቋንቋ መማር ሂደት ውስጥ የቃላት እውቀት ቁልፍ ሚና አለው፡፡ ለዚህም ምክንያት በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት ለቃላት ትኩረት መሰጠት እንዳለበት ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ ለምሳሌ Hunt እና Belgar(2002:83) በበኩላቸው ተማሪዎች ራስ አገዝና ውጤታማ እንዲሆኑ ከተፈለገ ቃላትን በተገቢው አውድ አቅርቦ ማለማመድ ተገቢ ነው፡፡ በአውድ ከሚቀርቡት ቃላት መካከል ከሃያዎቹ አስራ ዘጠኙ የሚታወቁ መሆን አለባቸው፡፡ ይህም የቃላትን ፍች ከአገባባቸው በመገመት ተማሪዎች በቀላሉ ለመገንዘብ ያስችላቸዋል በማለት ያስረዳሉ፡፡ ይህን ሀሳብ በማጠናከር Nation (1990)ም ስኬታማ ተግባቦት እንዲኖር ተማሪዎች የተተኳሪውን ቋንቋ ቃላት በሥርዓትና በጥልቀት ማወቅ አለባቸው፡፡ በስፋትና በጥልቀት ማወቃቸው ሃሳባቸውን በግልፅና በተቀላጠፈ መንገድ እንዲገልጹ ከመርዳቱም በላይ ሐሳቦችን በጥልቀት ለመመርመርና ለመረዳት ያስችላቸዋል፡፡

በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የቋንቋ አሃዶች እድገታቸውን ጠብቀው በትምህርቱ ሊሸፈኑ ይገባል፤ ይህም በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት የቋንቋ አሃዶች እድገት ባለው አካሄድ ተማሪዎች ትምህርቱን በቀላሉ እንድማሩ በሚያስችላቸው ሁኔታ የቃላት ትምህርት ማስታወስን የሚፈልግ

መሆኑን ባገናዘበ መንገድ በተወሰነ በጊዜ ርቀት በመደጋገምና በተለያዩ አውዶች ለመማር እድል በሚሰጥ መንገድ መቅረብ ይኖርባቸዋል (Nation 2006:6) ።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የምሁራን ሃሳቦች ቃላትን መማር ቀላል ተግባር እንዳልሆነ የሚያመላክቱና በተለይም ለሁለተኛ ቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ለቃላት ተገቢውን ትኩረት መስጠት እንዳለበት፣ ቃላትን በተለያየ አውድ እያስገቡ ማስተማር እንዳለባቸው ያስገነዝባሉ።

በሌላ በኩል Harmer (1991) እንደገለጹት በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ የተለያዩ ነባራዊ ነገሮችንና እሳቤዎችን ወክለው የሚገኙትም ቃላት ናቸው። ሰዋሰዋዊ መዋቅር የቋንቋውን አፅም ቢመሠርት ቃላት ደግሞ ወሳኝ የሆኑትን የቋንቋውን ብልቶች ሥጋና ደም ሆነው ሕይወት እንዲዘራ ያደርጉታል። በንግግርም ሆነ በጽሑፍ ሐሳብን ለመግለጽ፣ ከሌላ አቅጣጫ የሚሠነዘሩ ሐሳቦችን አዳምጦና አንብቦ ለመረዳት፣ በአጠቃላይ ለተግባቦታዊ ክንውን መሳካት የቃላት ዕውቀት መኖር ወሳኝ ነው (Nation, 1990)። ከዚሁ ጋር በተያያዘ McCarthy (1990) የቃላት እውቀት በተግባቦት ሂደት ውስጥ ያለውን ጉልህ ሚና ሲያስረዱ፣ ተማሪው የቋንቋውን መዋቅር በጥሩ ሁኔታ የመማሩ ጉዳይ ብቻ የሚፈይደው ነገር የለም፤ ትርጉም ያለው ተግባቦት ለማከናወን መሠረታዊው ነገር የቃላት እውቀት መኖር ነው።

ከነዚህ ምሁራን አገላለጽ የምንገነዘበው የቃላት እውቀት በቋንቋ መማር ሂደት ውስጥ ያለው ሚና ከፍተኛ መሆኑን ነው። በመሆኑም በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ ለቃላት የሚገባውን ትኩረት መስጠትና ለተግባቦት የሚያበቃ የቃላት ትምህርት ማቅረብ እንደሚገባ መረዳት ይቻላል።

ቃላትን መማር በተለይም በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ቀላል ተግባር እንዳልሆነ ከሌሎች የቋንቋው ገፅታዎች ይልቅ ፈታኝና የመምህሩንም ሆነ የተማሪውን ከፍተኛ ጥረት የሚጠይቅ ተግባር ነው (Read, 2000):: ቃላትን ማወቅ አያሌ የቃላት እውቀት አይነቶችን ይመለከታል ለምሳሌ የቃላት ፍቺን፣ የቃላት ቅርጽን፣ ፍካሪያዊና እማሪያዊ ፍቺን፣ ሰዋሰዋዊ አጠቃቀምን፣ እማሪያዊና ፍካሪያዊ ፍቺን ሲያጠቃልል ቅርጽ ደግሞ የቃላት አጻጻፍ /ስርዓተ ሆሄያትን (spelling)እና ንበትን ያጠቃልላል (Nation, 2001)። በዚህም በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ዘንድ ዘወትር አስቸጋሪ የቋንቋ ክፍል እንደሆነ ይገለጻል። የቃላት አውቀት እጥረት መኖር ደግሞ ተግባቦትን ያደናቅፋል (Rajaee, 2013)። አያይዘውም Mukoroli(2010:1) "ቃላት የመማር

ማስተማሩ ሂደት ለመምህራኑም ሆነ ለተማሪዎች እጅግ አስቸጋሪ ሆኖ ቆይቷል። ለዚህም ዋነኛ ምክንያት ለቃላት ትምህርት ዝቅተኛ ግምት መሰጠቱ ነው" ይላሉ።

በአጠቃላይ ከነዚህ ምሁራን ሀሳብ መረዳት የሚቻለው፣ ቃላትን መማር ቀላል ተግባር እንዳልሆነና በተለይም በሁለተኛ ቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ለቃላት ተገቢው ትኩረት መሰጠት እንዳለበት ነው።

## 2.4. የቋንቋ መማር ብልሃቶች ምንነትና ጠቀሜታ

ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ብልሃቶችን አስመልክቶ የተለያዩ ምሁራኖች ስለብልሃት ምንነት በየሙያቸው ይገልጻሉ። እንደ Cubukcu (2007:95) አገላለፅ ብልሃት ግለሰቦች ተግባራትን ለመገንዘብ እና ለማከናወን የሚነድፉት እቅድ ነው። ብልሃት ግለሰቦች የመማር ባህሪያቸውን በሚያቅዱበት እና በሚገመግሙበት ወቅት እንደት እንደሚያስቡ እና አንደሚተገብሩ ጠልቀው ለማሰብ ያስችላቸዋል። በተጨማሪም Ling (2011) & Griffiths (2004) ብልሃት የሚለው ፅንሰ ሀሳባዊ ቃል የመማር ባህሪ ፣እቅድ ፣ዘዴ ወዘተ ነው በሚሉ ተቀራራቢ ትርጉም ባላቸው ቃላት ይገልጻሉ።

Wharton (2000:204) እንዳብራሩት ቋንቋን የመማር ብልሃቶች በተማሪዎች የሚከናወኑ፣ ዕውቀትን የሚያካብቱበት፣ ሀሳብን አስታውሶ መጠቀምን የሚያፋጥኑ የአሰራር ባህሪዎች ፣ ልምምድ፣አካሄዳዊ ቴክኒኮች ሲሆኑ እነዚህ ብልሃቶች ተማሪው የቋንቋውን ትምህርት ሂደት ተስማሚና አዝናኝ በሆነ መንገድ ለመወጣት የሚያስችሉ ብልሃቶች ናቸው።

ከዚህ በላይ ከምሁራኑ ሀሳብ መረዳት እንደተቻለው የቋንቋ መማር ብልሃቶች ሰዎች አንድን ሀሳብ ለመረዳት፣ መረጃ ለማከማቸት፣ አዳዲስ መረጃ ለማግኘት፣ መማርን ለመቆጣጠርና ለመገምገም ወይም አንድን የተወሰነ ተግባር ለማከናወን የሚገለገሉባቸው የተለዩ አስተሳሰቦች፣ እርምጃዎችና ስልቶች ናቸው።

እንደ Ellis (1994:532) አባባል የቋንቋ መማር ብልሃቶችን ከማብራራት ይልቅ መለያ ባህርያቸውን መዘርዘሩ ተመራጭ መሆኑን ይገልጻሉ። እነዚህ መለያ ባህርያቶችም አንደሚከተለው ቀርበዋል።

- የቋንቋ መማር  ብልሃቶቹ ችግር ተኮር  ናቸው በመሆኑም የቋንቋ ተማሪው አንድ ልዩ ችግር ሲያጋጥመው የመማር ብልሃቱን እንደ ማጥቂያ መሳሪያ በመጠቀም ችግሩን ለመቋቋም ይጠቀምባቸዋል ።
- ተማሪዎች በአጠቃላይ ስለሚጠቀሙባቸው የቋንቋ ብልሃቶች ግንዛቤ አላቸው፡፡
- የቋንቋ መማር ብልሃቶች ስነ ልሳናዊ ባህርያትን ለመገልገል ያስችላሉ (ለምሳሌ የአንድን ቁሳቁስ መጠርያ ለማወቅ ሌሎች ሰዎችን መጠየቅ) እንዲሁም ኢ- ስነ ልሳናዊ ባህሪያትን ለመጠቀም ለማወቅ ሌሎች ሰዎችን መጠየቅ) እንዲሁም ኢ- ስነልሳናዊ ባህርያትን ለመጠቀም ያስችላሉ (ለምሳሌ ሌሎች ሰዎች የእቃውን ስም እንዲጠሩ ለማድረግ እቃው ወዳለበት በእጅ ማመልከት)፡፡
- ስነ ልሳናዊ የቋንቋ መማር ብልሃቶች በአፍ መፍቻ ቋንቋ እና በሁለተኛ ቋንቋ ተግባራዊ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡
- አንዳንድ የመማር ብልሃቶች ባህሪያዊ ሌሎች ደግሞ አእምሮአዊ ስለሆኑ ባህርያዊ የሆኑትን በግልጽ መመልከት ሲቻል፣ አእምሮአዊ  ብልሃቶች የሆኑትን ግን በተዘዋዋሪ እንጅ በቀጥታ ማየት አይቻልም፡፡
- የቋንቋ መማር ብልሃቶች በአብዛሀኛው ለመማር የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ ኢ- ቀጥተኛ ሲሆን አንዳንዶቹ ግን ለምሳሌ እንደትውሰታ ብልሃቶች የመሳሰሉት ለመማር የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ግልጽና ቀላል ነው፡፡
- በቋንቋ ብልሃቶች አጠቃቀም ዙሪያ ተጠቃሚው እንደሚያከናውነው ተግባር እና እንደ ተገልጋዩ ምርጫ የጎላ ልዩነት ይታያል፡፡

በአጠቃላይ ስለብልሃቶች ምንነት ከቀረቡት መረጃዎች ማጠቃለል የሚቻለው ብልሃቶች የመማር ችግርን ለመፍታት ወይም መማርን ለማቀላጠፍ የምንጠቀምባቸው ዝርዝር ዘዴዎች ናቸው በሚል በአጭሩ ማስቀመጥ ቢቻልም ስለብልሃቶች ምንነት በጥልቀት ለመረዳት ደግሞ መለያ ባህሪያቸውን መፈተሽ አስፈላጊ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ብልሃቶች በግንዛቤያዊ ደረጃ በማዛመድ ደረጃ እና በቅጽበታዊ የክንውን ደረጃ ላይ ሊከሰቱ እንደሚችሉ ግንዛቤ ሊኖር ይገባል፡፡

Huttunen (1996:88) እንዳስገነዘቡት በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ስኬታማ ለመሆን የቋንቋ መማር ብልሃቶች ትልቅ አስተዋጽኦ አላቸው፡፡ የቋንቋ መማር ብልሃቶች ሁለተኛ ቋንቋን በመማር ሂደት ውስጥ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች አሉት፡፡

- የተማሪዎችን የቋንቋ ብቃትና የተግበቦት ችሎታቸውን እንዲሻሻል ያደርጋሉ፡፡
- ቋንቋውን የመልመድና የመማር ሁኔታዎችን ያሳያሉ፡፡
- በቋንቋ ተግባቦት ጊዜ የብቃት እጥረት ቢከሰት ተግባቦቱ እንዳይቋረጥ የማካካሻ ዘዴ ይጠቀማሉ፡፡
- የአማርኛ ቋንቋን በብቃት በመጠቀም ዙሪያ መሰረታዊ ክሂሎችን ማለትም የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ክሂልን ለማሻሻል የሚያስችል ልምምድ ለመፍጠር ያግዛል፡፡

## 2.5 የቋንቋ መማር ብልሃቶች አመዳደብ

በተለያየ ወቅት ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ብልሃቶች አስመልክቶ ተመራማሪዎች በተለያየ የክፍል ደረጃዎች ላይ ባሉ የቋንቋ ተማሪዎች እና ከመማሪያ ክፍል ውጭ ሰዎች በራሳቸው ፍላጎት ሁለተኛ ቋንቋቸውን ሲማሩ በሚያሳዩት የመማር ክንዋኔዎች ላይ ጥናት በማድረግ የተለያዩ የመማር ብልሃቶች እንዳሉ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡

ለምሳሌ Cook (1991፣127) እንዳስገነዘቡት በሁለተኛ ቋንቋ ስኬታማ የሆኑ ግለሰቦች ስኬታማ ካልሆኑት ሰዎች ቋንቋውን ሲለማመዱና ሲማሩ የሚገጥሟቸውን መሰናክሎች ቀለል ባለስልት ለማለፍ ስለሚፈልጉ ወይም በአንድ አይነት መንገድ ሆኖ ይበልጥ በብቃት ስለሚወጡ ይሆናል፡፡ ለዚህም እንደማሳያ የሚያገለግለን የተሻሉ ጥሩ ቋንቋ ተማሪዎች የመማር ብልሃት ነው፡፡ ምሁራኑ አያይዘውም ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች የሚጋሯቸውን ስድስት የመማር ብልሃቶችን በዝርዝር ገልጸዋል፡፡ እነሱም:-

- በቋንቋ ትምህርት ሂደት ራስን ማሳተፍ:- የተሻሉ የቋንቋ ተማሪዎች የተዘጋጀላቸውን ትምህርት ዝምብለው የሚቀበሉ ሳይሆን በትኩረት በመማር በንቃት ይሳተፋሉ፡፡ ቋንቋውን ለመማር የሚስማማቸውን በማዘጋጀት ይጠቀማሉ፡፡እንደየ ፍላጎታቸው አንዳንዶቹ በሁለተኛ ቋንቋ ዜናዎችን ሲያዳምጡ ሌሎቹ ደግሞ ፊልሞችን በማየት ይሳተፋሉ፡፡

- ተስማሚ የመማር ብልሃት መፈለግ:- የተሻሉ የቋንቋ ተማሪዎች ለሚመቻቸው የቋንቋ ትምህርት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተው ይማራሉ፡፡ በመሆኑም ከመማር ማስተማሩ ሂደት ጋር በቁርጠኝነት በመነሳት ለራሳቸው የሚመቻቸውን ስልት በፍጥነት ይሰራሉ፡፡ ይህም አንዳንድ የተሻሉ የቋንቋ ተማሪዎች ቤታቸው ውስጥ ቴሌቪዥን፣ ሬዲዮና ቴፕ በማዳመጥ፣ልቦለድ፣ የሰዋሰው መጻሕፍት በማንበብ፣ የንግግር ወይም ተግባቦታዊ ቋንቋ መማርን ያዳብራሉ፡፡

- የቋንቋውን ሥርዓትና ተግባቦታዊ ዕውቀት ማሳደግ:- የተሻሉ የቋንቋ ተማሪዎች ፣ ቋንቋ አስቸጋሪ ሥርዓቶችና ህጎች እንዳሉት ብቻ ሳይሆን አገልግሎታቸውንም ለይተው ይጠቀማሉ፡፡ የተሻሉ የቋንቋ ተማሪዎች ፣ ቋንቋን እንደ አንድ የእውቀት ዘርፍ ወይም እንደ መግባቢያ መሣርያ ብቻ ለይተው የሚመለከቱ ሳይሆኑ እንደ መግባቢያ መሣርያም እና የእውቀት ዘርፍም ጭምር የሚመለከቱ ናቸው፡፡ በመሆኑም አንዳንዶቹ የቃላትን ትርጉም በትኩረት ሲያጠኑ ሌሎቹ ደግሞ በሁለተኛ ቋንቋቸው ጭውውትበማድረግና ምልልስ በማካሄድ መለማመድን ይመርጣሉ፡፡

- የቋንቋ እውቀትን ለማዳበር ዘወትር ትኩረት መስጠት:- የተሻሉ የቋንቋ ተማሪዎች በፊት በነበረው የሁለተኛ ቋንቋ እውቀት ተደስተው የሚጠቀሙ ሳይሆኑ ይበልጥ ለማሻሻልና ለማዳበር ዘወትር የሚለፉ ናቸው፡፡ ከሌሎች ሰዎች የሰሙትን ከራሣቸው ንግግር ጋር በማወዳደር ትክክል መሆን አለመሆናቸውን ያረጋግጣሉ፡፡ የቋንቋውን ተናጋሪዎች እንዲያስተካክሏቸው ሀላፊነት ይሰጣሉ፡፡

- ሁለተኛን ቋንቋ በራሱ ስርዓት መጠቀም :- የተሻሉ የቋንቋ ተማሪዎች የሁለተኛ ቋንቋ እውቀታቸውን የሚያዳብሩት በቋንቋው በግልፅ በመገልገልና አስፈላጊውን ትኩረት በመስጠት ነው፡፡ ማንኛውም ነገር ከአፍመፍቻ ቋንቋቸው ጋር እያገናኙ ሁለተኛ ቋንቋን በራሱ ሥርዓት ይጠቀማሉ፡፡

በሌላ በኩል O'malley እና Chamot (1990፣137-139) እንደገለጹት ሁለተኛን ቋንቋ ለመማር የሚያገለግሉ ሶስት መሰረታዊ የሆኑ የመማር ብልሃቶች አሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል ልዕለአዕምሮታዊ፣ አዕምሮታዊ፣ ማህበራዊ ስሜትነክ ቁጥጥር ብልሃቶች ሲሆኑ እያንዳንዳቸውም በስራቸው የሚከተሉትን ንዑሳን ዝርዝር ብልሃቶችን ያካትታሉ፡፡

ልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶች (Meta Cognitive Strategies)

እንደ Omalley እና Chamot (1990) አገላለፅ የሚማሩትን የቋንቋ ትምህርት ይዘት በማቀድ፣ የሚተገሩትን የቋንቋ ትምህርት ስራ ሂደት በመከታተል፣ የራስን ንግግርና ጽሁፍ በራስ በመገምገም ቋንቋ ለመማር የሚረዱ ብልሃቶች ናቸው። በዚህ ብልሃት ስር የሚከተሉት ንዑሳን ብልሃቶች ይገኛሉ።

- ማቀናጀት:- ተማሪዎች ሊጠቀሙባቸው ወይም የሚማሯቸውን ዋናዋና የትምህርት ርዕሶች  በማቀናጀትና በልዩልዩ የመረጃ ምንጮች በማሰባሰብ አስቀድመው ዝግጅት የሚያደርጉበት ነው ።
- በተለየ ሁኔታ ትኩረት ማድረግ:- በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዙርያ ከሚቀርቡ ይዘቶች መካከል በራስ አስተያየት አስፈላጊና መሰረታዊ የሆኑትን ለይቶ ትኩረት የመስጠት ብልሃት ነው።
- ራስን መምራት:- ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ለመማር የሚረዱ ቅድመ ሁኔታዎችን የሚያመቻቹበት ከሁኔታዎች ጋር ራሳቸውን የሚያስተካክሉበት፣ ለመለማመድ ምቹ ሁኔታዎች  መፈጠራቸውን  የሚያረጋግጡበትና በቋንቋው የመግባባት ብቃት ማዳበር አለማዳበራቸውን ራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩበት ብልሃት ነው።
- ትኩረት መስጠት:- ተማሪዎች አላማቸውን ለማሳካት  አዕምሮን ነፃና ክፍት በማድረግ የታላሚውን ቋንቋ ትምህርት አፅንኦት ሰጥቶ ለመከታተል አስቀድሞ የመወሰን ብልሃት ነው።
- ችግርን መለየት:- በቋንቋ ትምህርት ዙሪያ ለመማርና ለመለማመድ መሰናክል የሆኑ ችግሮችን ለይቶ በማውጣት መፍትሄ የማዘጋጀት ብልሃት ነው።
- ራስን ማየት:- ተማሪው በትምህርቱ ሂደት የሚማሯቸውን ነገሮች በትክክል መረዳቱን፣ ያቀዳቸውን ተግባራት በትክክል እየተገበራቸው መሆኑን በአጠቃላይ ትምህርቱን በትክክል እየተከታተለ መሆኑን  ስራውን በራሱ የሚቆጣጠርበት ነው።

አዕምሮታዊ ብልሃቶች (Cognitive Strategies)

ተማሪው በግልፅ የታላሚውን ቋንቋ ተግባራት ሲሰራ የሚጠቀምባቸው ብልሃቶች ናቸው፡፡ በዚህ ስር ሌሎች ንዑሳን ብልሃቶች ይካተታሉ፡፡

- መተርጎም:- ተማሪው በአማርኛ ቋንቋ አዳዲስ ወይም እንግዳ ሃሳብ መረዳት ሲያቅተው ወደ አፍ መፍቻ ቋንቋ ተርጉሞ መረዳትን የሚጠቁም ብልሃት ነው፡፡
- መደጋገም:- የታላሚውን ቋንቋ ተግባራት ደጋግሞ የመስራትና የመለማመድ ብልሃት ነው፡፡
- ማቧደን:- ተያያዥነት ያላቸው የትምህርት ይዘቶችን (ለምሳሌ ቃላትን፣ ሀረጋትንና ርዕሰ ጉዳዮችን) እንደየ ባህሪያቸውና ግንኙነታቸው በምድብ በምድብ አቀናጅቶ የማጥናት ብልሃት ነው፡፡
- ምንጭ መጠቀም:- ለተማሪዎች የቃላት መማር ብልሃት አጠቃቀምንና የቋንቋውን ትምህርት ሊያሻሽሉ የሚችሉ የመረጃ ምንጮችን (ለምሳሌ፣ልቦለድ፣ የማጣቀሻ መጻሕፍት፣ መፅሔቶች፣ ጋዜጣዎች)በማንበብ የመገልገል ብልሃት ነው፡፡
- ማስታወሻ መያዝ:- በማንበብና በማዳመጥ ሂደት አስፈላጊ የሆኑ ለቋንቋ ትምህርት ስኬታማነት የሚያገለግሉ በቃልም ሆነ በጽሁፍ የቀረቡ ማጠቃለያዎችንና ዋናዋና ፍሬ ሃሳቦችን ማስታወሻ የመያዝ ብልሃት ነው፡፡
- አውድን መጠቀም:-ተማሪው በሚያነብበት ወቅት አዳዲስ ቃላትን ሐረጋትንና ጽንሰሀሳባዊ ፍችን ለመገንዘብ እንዲሁም አንባቢው እንዳሚላ ተቆርጦ የቀረውን ሃሳብ ገምቶ የተሟላ ሃሳብ ለመጨበጥ የገባበትን አውድ የመመርመር ብልሃት ነው፡፡
- ስዕል መፍጠር:- ጽንሰሀሳቦችንና እንግዳ ቃላትን በቀላሉ ለመያዝና የረጅም ጊዜ ትውስታ ለመፍጠር ከሚታወቅ ተጨባጭ ነገር (ለምሳሌ ስዕል፣ዕቃ) ጋር በማያያዝ በአዕምሮ ስዕል የመፍጠር ብልሃት ነው፡፡
- ማጠቃለል:- በመናገር፣ በማዳመጥ፣ በማንበብ የተካበተውን ዕውቀት ወይም ቋንቋነክ ጽንሰሀሳብ በማሣጠር ጠቅለል የማድረግ ብልሃት ነው፡፡

ማህበራዊ ስሜት ነክ ቁጥጥር ብልሃቶች (Socio affective strategies)

እንደ O'malley እና Chamot (1990) አባባል ይህ ብልሃት ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ሲለማመዱና ሲማሩ ከሰዎች ጋር በመተባበርና በመተጋገዝ ተጨማሪ ገለጻዎችን በመጠየቅ እንዲሁም ራሳቸውን በራሳቸው በማጠናከር ቋንቋን የሚለምዱበትና የሚማሩበት ብልሃት ነው፡ ፡ በማህበራዊ ስሜትነክ ብልሃቶች ስር በተማሪዎች የሚተገበሩ ንዑሳን ብልሃቶች ተካተው እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- *መተጋገዝ፡-* ተማሪዎቹ በቋንቋ ትምህርት ሂደት ልምድ ለመለዋወጥ ወይም ምጋቤ ምላሽ ለማገኘት ሲባል ከተለያዩ ሰዎች ጋር ግንባር ፈጥሮ በጋራ የመስራት ብልሃት ነው፡፡
- *ማብራሪያ መጠየቅ፡-* የቋንቋ ትምህርት ሲማሩና ልምምድ ሲያደርጉ ግልጽ ያልሆኑ ሃሳቦች ሲያጋጥሙ ወይም በተማሩት ቋንቋ ነክ ጉዳይ ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ ሲያስፈልግ መምህራንን፣ ጓደኛን፣ ወላጅን፣ ወዘተ. በማስረጃ የተደገፈ ገለፃ እንዲሰጧቸው የመጠየቅ ብልሃት ነው፡፡
- *ራስን ማበረታታት፡-* ተማሪው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርቱን ሲማር የተሻለ የቋንቋ አጠቃቀም ሲያሳይ ራስን በማድነቅ፣ በመሸለምና በማበረታታት ለቀጣይ ትምህርት መንገዶችን የሚያመቻችበት ነው፡፡
- *ከራስ ጋር መማከር፡-* ግለሰቡ በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት ያደረበትን ፍርሃት፣ ስጋትና ጭንቀት በመቀነስ ማንኛውም ተግባራት በቁርጠኝነት በራሱ ኃይል መስራት እንደሚችል ለራስ በመንገር የጠንካራነት ስሜት እንዲሰማው የሚያደርግበት ስሜት ነው፡፡

ከዚህ በላይ ከምሁራኖች ሃሳብ ለመረዳት እንደሚቻለው የቋንቋ መማር ብልሃቶች ለቋንቋ ትምህርት አስፈላጊና ዋነኛ መሣርያዎች ናቸው፡፡ በተለይም የሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎች አራቱንም ብልሃቶች በእኩል ደረጃ ቢገለገሉባቸው ውጤታማ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን አንደተማሪው የመረዳት ችሎታ፣ ከተማሪው ዕድሜና የግንዛቤ ደረጃ የሚጠቀሙባቸው ብልሃቶች ለእያንዳንዱ የሚሰጡት ግምትና አሥተያየት የቋንቋ አጠቃቀማቸው ደረጃ ሊለያይ ይችላል፡፡

በሌላ መልኩ ደግሞ Ellis ( 1994፡530) ስለቋንቋ መማር ብልሃቶች ምንነት ሲገለጹ " የተማሪዎች የታላሚ ቋንቋን አዳዲስ ስነ ልሳናዊ እና ማህበረ ስነልሳናዊ መረጃዎችን በሚገባ ለማወቅ የሚያደርጉት ጥረት ነው" ይላሉ፡፡ Oxford (1990) የቋንቋ መማር ብልሃቶች ቋንቋ መልመድን የቋንቋ መረጃ መሰብሰብ እና የቋንቋ ችሎታን ለማዳበር ሲሉ ተማሪዎች ይሁነኝ በማለት የሚጠቀሙባቸው ባህሪያት ናቸው ለማለት ይቻላል፡፡ የቋንቋ መማር ብልሃቶች አይነት በአይነት ለመከፋፈል በርካታ ምሁራን የየራሳቸውን ሙከራ ያደረጉ ሲሆን እስካሁን ለብዙ ክሂሎች አከፋፈል እንደ መሰረት ተደርገው የሚወሰዱት ግን የOxford (1990) አከፋፈሎች ናቸው፡፡ ካሉት አከፋፈሎች ይህ የOxford(1990) አከፋፈል ሚዛን እንደሚደፋ ምሁራኑ ይገልፃሉ፡፡ ከተሰጡት ምክንያቶች መካከልም ዝርዝር ብልሃቶችን በተዋረድ በማስቀመጥ በሁለት አበይት ክፍሎች ብቻ በመክፈል እና ለመረዳት ቀላል መሆኑ ተመራጭ ያደርገዋል፡፡

የቋንቋ መማር ብልሃቶችን ቀጥተኛ ብልሃቶች እና ኢ-ቀጥተኛ ብልሃቶች በማለት በሁለት ይከፍላቸዋል፡፡ እንደምሁራኑ አባባል ቀጥተኛ ብልሃቶች ማለት ከታላሚ ቋንቋ ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት የሚፈጥሩትን ብልሃቶች የሚያካትቱ ሲሆን ኢ- ቀጥተኛ ብልሃቶች ማለት ደግሞ በማቀድ በመገምገም ጭንቀትን በቁጥጥር ስር በማድረግ፣ ወዘተ. ቋንቋ መማር ቀጥተኛ ያልሆነ ድጋፍ የሚሰጡትን ብልሃቶች የሚያካትቱ ናቸው፡፡ ሁለቱ አበይት ክፍሎችም በውስጣቸው ሶስት ሶስት ንዑሳንክፍሎችን ይዘዋል፡፡ ቀጥተኛ ብልሃቶች የማስታወስ ብልሃቶችን፣ ግንዛቤያዊ ብልሃቶችን እና አካካሽ ብልሃቶችን ይዘዋል፡፡ ኢ- ቀጥተኛ ብልሃቶች ደግሞ ልዕለ ግንዛቤያዊ ብልሃቶች፣ ስነ ልቦናዊ ብልሃቶች እና ማህበራዊ ብልሃቶችን አቅፈዋል፡፡ የነዚህን ንኡሳን ብልሃቶች ምንነት በሚመለከት Goethals(1994) ሲገልጹ በቀጥተኛ ብልሃቶች ስር የሚገኙት የማስታወስ ብልሃቶች ማለት አዲስ መረጃን ለማስታወስ እና ከአእምሮ አውጥቶ ለመጠቀም የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ አካካሽ ብልሃቶች የሚባሉት ተማሪው የቋንቋ እጥረት ሲያጋጥመው ምትክ ይሆናል ብሎ የሚጠቀምባቸውን በሙሉ የሚያካትቱ ናቸው፡፡ ስነ ልቦናዊ ብልሃቶች ደግሞ በቋንቋ መማር ሂደት ስሜትን ለመቆጣጠር የሚረዱ ሲሆን ማህበራዊ ብልሃቶች ደግሞ ተማሪዎች ቋንቋውን ለመማር ይረዱኛል ከሚላቸው በታላሚ ቋንቋ ችሎታቸው ከተሻሉት ተማሪዎች ጋር ተባብሮ እንዲማሩ የሚያገለግሉት ናቸው (Goethals 1994፡475-476)፡፡

እነዚህ የቋንቋ መማር ብልሃቶች የቋንቋ የመማር እንቅፋቶችን ለመፍታት ወይም ቋንቋ መማርን ከግብ ለማድረስ ጥቅም ላይ የሚውሉ ባህሪያት ወይም ቅደም ተከተላዊ ክንውኖች ሆነው ቀጥተኛ እና ኢ-ቀጥተኛ በሚል በሁለት አበይት ክፍሎች የተከፈሉ ናቸው፡ እነዚህ ክፍሎች በየራሳቸው ንዑሳን እና የንዑሳን ክፍሎች ያሏቸው ሲሆኑ ከተለያዩ የቋንቋ ክሂሎች ጋር ግንኙነት ያላቸው ናቸው፡፡

## 2.6 የቃላት መማር ብልሃቶች ምንነትና አስፈላጊነት

ከቅርብ አመታት ወድህ የቃላት ትምህርት አቀራረብ ከጥንታዊው መምህር መር ወደተማሪ ተኮር አቀራረብ እየተቀየረ መጥቷል፡፡ ቃላትን የመማር ብልሃቶች በቃላት ትምህርት ውስጥ ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው የዘርፉ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ ለአብነት ያህል McCarthy (1990፣124) እንደገለጹት ተማሪዎች የቃላት ትምህርታቸውን በብቃት ለመወጣት በርካታ ብልሃቶችን ይጠቀማሉ፡፡ ሆኖም ግን አንዳንድ ተማሪዎች ከሌሎቹ ይበልጥ የመማር ብልሃቶችን በአጥጋቢው ሁኔታ ይጠቀማሉ፡፡

Catalon (2003) እንዳብራሩት የቃላት መማር ብልሃቶች ተማሪዎች ቃላትን ለማወቅ ትኩረት ሰጥተው ሲማሩ የሚተገብሯቸው ክንውኖች ናቸው በማለት ገልጸዋል፡፡ የቃላት መማር ብልሃቶች ተማሪዎች ለእንግዳ ቃላት ሲጋለጡ የቃላቱን ትርጉም ለመገንዘብና ቃላቱን በዘውታሪነት በአእምሯቸው ውሰጥ ስርጾ እንዲቀር የሚገለገሉባቸው የራሳቸው መለያ ባህርያት ናቸው (Jurkovic, 2006)፡፡ በአጠቃላይ የቃላት መማር ብልሃቶች የእንግዳ ቃላትን ትርጉምና የታወቁ ቃላትን ፍቺ ለመለየት፣ በረጅም ጊዜ ትውስታ በመፍጠርና በሚያስፈልግ ጊዜ አስታውሶ በአዳምጦ መረዳት፣ በአንብቦ መረዳት፣ በንግግርና በጽሁፍ ጊዜ አፍልቆ ለመጠቀም የሚያስችሉ ብልሃቶች ናቸው (Catalon, 2003)፡፡ በሁለተኛ ቋንቋ ቃላት ትምህርት ሂደት የቃላት መማር ብልሃቶችን ጉልህ ጠቀሜታ Mahadavi (2014) ከቻይናዎች ምሳሌያዊ አነጋገር በመነሳት እንዳስረዱት «ዓሣ እንዲበላ ስጠው! ለአንድ ቀን ዓሣ ይበላል፣ ዓሣ እንዴት እንደሚያጠምድ አስተምረው እድሜ ልኩን ዓሣ ይበላል፡፡» ከላይ ከምሁራኑ ሀሳብ መገንዘብ እንደተቻለው መምህራን ተማሪዎችን ሲያስተምሩ ለመማር የሚፈልጉትን ቃላት ሁሉ ሳይሆን የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ለወደፊት በራሳችው መንገድ ቃላትን ፈጥረው የሚማሩበትን ስልት እንዳውቁ በምሳሌያዊ አነጋገር ማስረዳት እንደሚቻል ነው፡፡

ስለዚህ መምህራን ተማሪዎች ከተወሰነ የመማሪያ ክፍለ ጊዜያቸው ውጭ ባለው ሰፊ ጊዜ በክፍል ውስጥ ያልተማሩዋቸውንና ያልተወያዩባቸውን አዳዲስ ቃላት በትርፍ ጊዜያቸው በራሳቸው መንገድ ለመማር የሚያስችላቸውን ዘዴዎች ሊያሳውቋቸው እንደሚገባ ይገልጻሉ (በላይነሽ, 2010) ፡፡

እንደ Nation (2001) እና Schmitt (1997) አገላለጽ የቃላት መማር ብልሃቶች የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት የአዳዲስ ቃላትን ትርጉም ለመገንዘብና በረዥም ጊዜ ትውስታ መዝግቦ ለማቆየት ራሳቸውን ለማገዝ የሚገለገሉባቸው አዋጭነት ያላቸው ብልሃቶች ናቸው፡፡

ከላይ ከምሁራን ሀሳብ ለመረዳት እንደሚቻለው ተማሪዋች የቃላት ብልሃትን ተጠቅመው ሲማሩ ለትምህርታቸው ሀላፊነት ወስደው በመማርያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጭ የተማሩትን በማስታወስ በራሳቸው ጥረት መለማመድ እንዳለባቸው ያስገነዝባል፡፡

## 2.7 የቃላት መማር ብልሃቶች አመመዳደብ

ቃላትን የመማር ብልሃቶች አከፋፈል አንድ ወጥ መንገድ የተከተለ አይደለም፡፡ ምሁራኑ የቃላት መማር ብልሃቶችን የከፋፈሏቸው በተለያየ መንገድ ነው፡፡ ለምሳሌ Hedge (2000:117-118) የቃላት መማር ብልሃቶችን በሁለት ዋና ዋና ምድብ በመክፈል አዕምሮታዊና ልዕለ አዕምሮታዊ በማለት በእያንዳንዳቸው ስር ሌሎች ንዑሳን ብልሃቶችን አካተው አቅርበዋል፡ ፡ Nation (2005:589) ከሌሎቹ በተለየ ሁኔታ የቃላት መማር ማስተማር ልምድ መሰረት በማድረግ በሶስት ምድብ በመክፈል በእያንዳንዳቸውም ስር ሌሎች ንዑሳን ብልሃቶችን አካተው አቅርበዋል፡፡ በመሆኑም ይህ የNation አከፋፈል እያንዳንዱን ንዑስ ብልሃት በየትኛው አጠቃላይ ምድብ ስር እንደሚገኝ በግልጽ ባለማቅረባቸው የንዑስ ብልሃቶቹን ጽንሰ ሃሳብ በአጭር ጊዜ ለመረዳት ከባድ በመሆኑ አስተማማኝነቱን ዝቅ ያደርገዋል፡፡

በሌላ በኩልም Pemberton (2003) የቃላት መማር ብልሃቶችን በሁለት ጎራ በመክፈል በእያንዳንዳቸው ስር በተማሪዎች የሚከናወኑ ተግባራትን በዝርዝር አቅርበዋል፡፡

ቃላትን የመማር ብልሃቶች ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት መንገዶች በተለየ ሁኔታ ከከፈሉት ምሁራን መካከል Oxford (1990)የመጀመርያው ተጠቃሽ ነው፡፡ Oxford (1990) የመማር ብልሃቶችን በሁለት ታላላቅ ምድቦች ቀጥተኛና ኢ-ቀጥተኛ የቃላት መማር ብልሃቶች

በመክፈል በእያንዳንዱ ስር ሶስት ሶሥት ንዑሳን ብልሃቶችን ከሌሎች በርካታ ዝርዝር ብልሃቶች ጋር በማካተት አቅርበዋል፡፡ ይህ የምሁሩ አከፋፈል በሌሎች ጥናቶች የቀረቡ የመማር ብልሃቶችን አካቶ የያዘ፣ ብልሃቶቹንም በጥልቅና በስፋት መረጃዎችና ምሳሌዎች አስደግፎ የሚያቀርብ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ቃላትን የመማር ብልሃቶችን አተገባበር እንደ አስፈላጊነቱ ምሳሌዎችን በመስጠት በግልፅ የሚያሳይና የቋንቋ ክሂሎችን ከግምት ውስጥ ያስገባ ነው፡፡

ከዚህ በላይ በተለያዩ የመስኩ ምሁራን ስለቃላት መማር ብልሃቶች አመዳደብ የየበኩላቸውን ክፍፍል አቅርበዋል፡፡ ከቀረቡት አከፋፈሎች እንደምንረዳው የቃላት መማር ብልሃቶች በተለያዩ ምድብ ስር ሊካተቱ እንደሚችሉና በአመዳደቡ ሆነ በአከፋፈሉ ረገድ ምሁራን ወጥ የሆነ አከፋፈል እንደሌላቸው አስተውለናል፡፡ ይህም ልዩነት ምሁራን እንደተነሱበት የጥናት ትኩረት አቅጣጫ መለያየት የብልሃቶቹ ምድብ አከፋፈል አንድ ወጥ አለመሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት በ Oxford (1990) የቀረበውን አመዳደብ መሰረት ያደረገ ነው ፡፡ የእያንዳንዱ ምሁራን የቃላት መማር ብልሃቶች አከፋፈል በዝርዝር ለመመልከት እንሞክራለን፡፡

### *2.7.1 የ Hedge የቃላት መማር ብልሃቶች አመዳደብ*

እንደ Hedge (2000 :117-118) አገላለፅ አዳዲስ ቃላትን ለመማር አላማውን በመረዳት፣ በመከፋፈል እና ቃላትን በአእምሮ መዝግቦ በመያዝ ተማሪዎች ቋንቋን ለመማር ሲፈልጉ ሰፊ የሆኑ ብልሃቶችን መጠቀም እንዳለባቸው ይገልጻሉ፡፡ አያይዘውም የቃላት መማር ብልሃቶችን በሁለት ዋና ዋና ምድብ ማለትም አእምሮታዊና ልዕለ አእምሮታዊ በማለት በእያንዳንዳቸው ስርም ንዑሳን ብልሃቶችን ከፍለው አቅርበዋል፡፡

- አእምሮታዊ ብልሃቶች
    - ✓ የቃላትን ተዛምዶ መጠቀም
    - ✓ ቃላትን በመመደብ መማር
    - ✓ የቃላትን ትርጉም ከመዝገበ ቃላት በመፈለግ
    - ✓ የቃላትን አውዳዊ ፍች በመጠቀም መማር
    - ✓ ኢ-ቀጥተኛ በሆነ መንገድ ብልሃቶችን መረዳት
- ልዕለ አእምሮታዊ ብልሃቶች

- ✓ ቃላትን በምድባቸው መዘርዘር
- ✓ ቃላትን በምልልስ መልኩ እንደገና መጠቀም
- ✓ ቃላትን በማዛመድ  ለአንድ አላማ መጠቀም
- ✓ ከአገባቡ በመረዳት ትክክለኛውን ቃላት በማጣመር ማወቅ

### 2.7.2 የ Nation ቃላት መማር ብልሃቶች ምደባ

ይህን ነጥብ አስመልክተው Nation (2005፣ 589-593) ከሌሎች በተሻለ ሁኔታ ምርምር በማድረግ ሳይሆን የራሳቸውን የቃላት መማር ማስተማር ልምድ መሰረት በማድረግ ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች የሚገለገሉባቸውን የቃላት መማር ብልሃቶች በአጠቃላይ በሦስት ዋና ዋና ምድብ ማለትም ማቀድ፣ ምንጭ መጠቀምና ሂደታዊ ብልሃቶች በማለት በእያንዳንዳቸው ስርም ንዑሳን ብልሃቶችን በመዘርዘር አስረድተዋል፡፡

| ምድቦች | ንዑሳን ብልሃቶች |
|---|---|
| ሂደታዊ | ትውስታን መፍጠር<br>- ማሰላሰል (ማገናዘብ)<br>- ማመንጨት (ማፍለቅ) |
| ምንጭ መጠቀም | - አውድን መጠቀም<br>- ቃላትን መተንተን<br>- የአፍ መፍቻ ቋንቋን ከሁለተኛ ቋንቋ ጋር እያገናኙ መማር<br>- ቃላትን በመተካት በሁለቱም ቋንቋ መማር<br>- መዝገበ ቃላት መጠቀም |
| ማቀድ | -  ቃላትን መምረጥ<br>-  ደጋግሞ ማቀድ<br>- ብልሃቶችን መምረጥ<br>- የእውቀት ዘርፎችን መምረጥ |

ከዚህ በላይ ከምሁራኑ የቃላት መማር ብልሃቶች አከፋፈል እንደምንረዳው አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ውስጥ የሌሉ ድምጾችን በታላሚው ቋንቋ ውስጥ ተነውረው አገልግሎት ላይ የማይውሉ ቃላትን ለይተው በተተኪ ቃላት መጠቀም እንዲችሉ፣ መዝገበ ቃላት ላይ በመፈለግ የተለያዩ አዳዲስ ቃላትን በቀላሉ ለማጥናትና በአገኙት አጋጣሚ ሁሉ የቃላት እውቀታቸውን ለማሳደግ የበኩላቸውን ማበርከት እንዲችሉ የቃላት መማር ብልሃቶችን መማር እንዳለባቸው ያስገነዝባል፡፡

## 2.7.3 የ Pemberton የቃላት መማር ብልሃቶች አከፋፈል

ሁለተኛ ቋንቋ የቃላት መማር ብልሃቶችን አስመልክቶ ጥናት ያካሄዱ ምሁራን ብልሃቶቹን የከፋፈሉት በተለያየ መንገድ ነው፡፡ ለአብነት ያህል Pembertton (2003) እንደገለጹት ቃላትን ለማስታወስ የተለያዩ ጠቃሚ ብልሃቶች እንዳሉ በመግለጽ በሁለት ዋና ዋና ምድቦች በመክፈል በስሩም ንዑሳን ክፍሎችን በመዘርዘር አቅርበዋል፡፡ እነሱም

ምድብ አንድ  ቃላትን የመማር ብልሃቶች፦ ቋንቋን የመማር ብልሃት አንዱ ክፍል ሲሆን የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት አዳዲስ ቃላትን በቀላሉ ለመማርና መዝግቦ ለማቆየት ራሳቸውን ለመርዳትና አላማዎችን ለማሳካት ሲባል በተለያየ መልኩ እገዛ የሚያደርጉ ስልቶች ናቸው፡፡ የሚከተሉትን ዝርዝር ብልሃቶች በውስጡ ያካትታል፡፡

የቃላት ሽምደዳ ፦ ለብዙጊዜ በመጻፍና በመናገር ፣በቴፕ ሪከርድ በማድረግም ሆነ በምስልና በድምፅ በማቀናበር (ለምሳሌ በግጥም፣ ፊልምን በመከታተል) እየሸመደዱ ቃላትን መማር ይቻላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በፅንሰ ሀሳብ የተማሩትን ቃላት በፅሁፍ በመቀየርና አዲሱን የተማሩትን ቃላት ከአካባቢያቸው ቁሳቁስ ጋር በማዛመድ ቃላትን መማር ነው ፡፡

ቃላትን መጠቀም ፦ ተዛማጅነት ያላቸውን ቃላት በመጠቀም ዓረፍተነገር በመመስረትና ያላወቁትን ቃላት በትረካ መልክ በመጻፍ መማር ነው፡፡

የተማሩትን ቃላት አንደገና መድገም፦ ለብዙ ጊዜ ታትመው የሚወጡ ጋዜጦች ፣መጽሔቶች ላይ ቃላትን መማር ይቻላል፡፡

ምድብ ሁለት ቃላትን የሚረሱባቸውን መንገዶች መቀነስ፦ ቃላትን በመደጋገም ለመማር የትምህርት ስዓቱን መጨመርና ለቃላት ጥናት ራሱን የቻለ የጊዜ ሰለዳ በማዘጋጀት (ለምሳሌ ከቁርስ በፊትና ከምኝታ በፊት) ቃላትን በመማር ማስታወስ ይቻላል። እንደ ምሁራኑ አባባል የቃላት መማር ትልቁ ችግር ዛሬ የተማሩትን ነገር የመርሳት እና ብዙ የቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎች በዚህ ችግር ውስጥ የሚያልፉ መሆናቸውን ይገልጻሉ።

ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ነጥቦች እንደምንረዳው የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ለትምህርታቸው ውጤታማነት የራሳቸው ጥረት የጎላ ድርሻ ይኖረዋል። ስለዚህ ለትምህርታቸው ሃላፊነት ወስደው በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጪ ቃላትን የመማር ብልሃትን መሰረት አድርገው በራሳቸው ጥረት ቃላትን በመደጋገም ታላሚውን ቋንቋ እንድማሩ ማጠናከር ይገባል።

### 2.7.4 የOxford ቃላት መማር ብልሃቶች አመዳደብ

ካሉት አከፋፈሎች ይህ የOxford (1990) አከፋፈል ሚዛን እንደሚደፋና በሌሎች ጥናቶች የቀረቡ የመማር ብልሃቶችን አካቶ የያዘ በምሳሌዎች አሰደግፎ የሚያቀርብ መሆኑን ምሁራን ይገልጻሉ። ከተሰጡት ምክናየቶች መካከልም ዝርዝር ብልሃቶችን በተዋረድ በማስቀመጥ በሁለት አብያት ክፍሎች ብቻ በመክፈልና በስሩም ንዑሳን ክፍሎችን በመዘርዘር፣በማብራራት ለመረዳት ቀላል መሆኑን ተመራጭ ያደርገዋል። በመሆኑም ይህ ጥናትም ትኩረት ያደረገው በ Oxford (1990) የቀረበውን አመዳደብ መሰረት በማድረግ ነው። ብልሃቶቹም ከዚህ በታች በዝርዝር ቀርበዋል።

#### 2.7.4.1 ቀጥተኛ ቃላትን የመማር ብልሃቶች

እንደ Oxford (1990፣37) አገላለጽ ተማሪዎች በግልጽ የታላሚውን ቋንቋ በትምህርቱ ሂደት እየተወያዩ የተለያዩ ተግባራትን እየሰሩ የተተኳሪውን ቋንቋ ቃላት እንዲለማመዱና እንዲማሩ በቀጥታ የሚረዷቸው ብልሃቶች ናቸው። በቀጥተኛ ብልሃቶች ስር የሚካተቱ ዋና ዋና ንዑስ ብልሃቶችም የትውስታ ብልሃቶች፣ አእምሯዊ ብልሃቶችና አካካሽ ብልሃቶች ናቸው።

##### 2.7.4.1.1 የትውስታ ብልሃቶች

ትውስታ የሚለው ቃል ስያሜው እንደ ሚያመለክተው ብልሃቶችን ተጠቅመው ተማሪው ቃላትን በአእምሮው መዝግቦ በመያዝና የረጅም ጊዜ ትውስታ በመፍጠር በአስፈላጊው ጊዜ አስታውሶ ለመጠቀም የሚያግዙ ብልሃቶች ናቸው።እንደ Oxford (1990፣39) አገላለጽ

የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች አንዱ መሠረታዊ ችግር በአንድ ወቅት የተማሯቸውን ቃላት ወይም አገላለፆች በሌላ ጊዜ መርሳት ነው፡፡የትውስታ ብልሃቶችም የታላሚውን ቋንቋ ተማሪዎች የሚገጥማቸውን ችግር በብቃት እንዲቋቋሙ ይረዳቸዋል፡፡ የትውስታ ብልሃቶች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ካላቸው አላማ አኳያ ከአንደኛ ደረጃ በላይ ያሉ ተማሪዎች ብልሃቱን አልፎ አልፎ ይጠቀሙባቸዋል፡፡

በሌላ በኩልም Wong(2005፣248)ባደረጉት ጥናትና ምርምር የቋንቋ ተማሪዎች በተለይም የሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች የትውስታ ብልሃትን አጠቃቀም ከሌሎች ብልሃቶች ጋር በንጽጽር ስንመለከት ብልሃቱን ለመጠቀም ያላቸው ፍላጎት አነስተኛ ነው ብለዋል፡፡ የትውስታ ብልሃት የሚከተሉትን ዝርዝር ብልሃቶች እንደሚያካትት Brown(1994:141) Oxford(1990) በመጥቀስ ገልጸዋል፡፡

- አካላዊ ምላሽ መጠቀም፡- የእንግዳ ቃላትን ፍች በአካል እንቅስቃሴ በመጠቀም ማሳየት
- አዳዲስ ቃላትን በዐውድ ውስጥ ማስገባት ፡- አዳዲስ ቃላትን ትርጉም በሚሰጥ ቃላዊና ጽሑፋዊ የሃሳብ ልውውጥ ውስጥ መጠቀምና የተለያዩ ዐረፍተ ነገሮችን በመመስረት ከቃላቱ ጋር ለተከታታይ ረጅም ጊዚያት የመዝለቅ ብልሃት ነው፡፡
- በማቧደን፡- ከርዕሰ ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን እንግዳ ቃላትን ለማስታወስ በሚስማማ ትርጉም ባለው መልኩ ተመሳሳይ ይዘት ያላቸውን ቃላት በአንድነት በማቧደን ከአእምሮ ጋር በማያያዝ ለትውስታ እንዲፈጥሩ የማመቻቸት ብልሃት ነው፡፡
- ክለሳ ማካሄድ፡- ተማሪዎች በተወሰነ ጊዜ የተማሩትንና የተለማመዱትን ቃላት የረጅም ጊዜ ትውስታ ለመፍጠር በሚል ዓላማ በተለያዩ ጊዜያት ውስጥ የመከለስ ብልሃት ነው፡፡
- በትውስታ ውስጥ ድምጽን መወከል፡- የአድሱን ቃል ድምጽ በማንኛውም ቋንቋ ውስጥ ከሚያውቁት ተመሳሳይ ድምጽ ካለው ቃል ጋር በማያያዝ ታላሚውን ቃል ለመያዝ መሞከር
- ስነ ፍቻዊ ካርታ፡- የትርጉም ተያያዥነት ያላቸውን ውስን ቃላት በመካከላቸው ያለውን ግንኙነት ሊያሳይ በሚችል ስዕል ላይ መደርደር፡፡

- ስዕል መፍጠር:- የታላሚዎቹን ቃላት ከተጨባጭ ነገሮች (ቁሳቁሶች ፣ከስዕሎችና ቦታዎች ወዘተ) ማገኘት፡

- ማያያዝ:- አድሱን ቃል በአእምሮ ውስጥ ከተመዘገበ ነገር ጋር ማያያዝ ትርጉም ባለው መንገድ ግንኙነት በመፍጠር ለትውስታ ማመቻቸት፡፡

## 2.7.4.1.2 አዕምሮታዊ ብልሃቶች

አዕምሮታዊ ብልሃቶች ማለት ተማሪው የተተኳሪውን ቋንቋ ቃላት በግልጽ አእምሮውን በመጠቀም ተገንዝቦና ከራሱም አፍልቆ በመለማመድ እንዲማር የሚያስችሉት ብልሃቶች ናቸው፡፡ እንደ Rubin (1987፣23) አገላለጽ አእምሯዊ ብልሃቶች ተማሪዎች ተተኳሪውን ቋንቋ ሲለማመዱና ሲማሩ በግልጽ አእምሯቸውን በመጠቀም የሚያከናውኗቸው የአሰራር ስልቶች፣ የሚወስዷቸው እርምጃዎች ወይም ችግር ለማቅለል የሚጠቀሙባቸው ናቸው፡፡ ተማሪው በአእምሯዊ ብልሃቶች ስር በቀጥታ የሚጠቀሙባቸው ንዑሳን ብልሃቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- መተርጎም፦ በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት የቀረበውን አድስ ጽንሰሀሳብ የበለጠ ለመረዳት ጽንሰ ሀሳቡን ለመገንዘብ ሲያቅታቸው ወደ አፍ መፍቻ ቋንቋቸው ተርጉሞ የመረዳት ብልሃት ነው፡፡

- ምንጭ መጠቀም:- የቋንቋ ትምህርት ሂደቱን ለማጠናከር የሚጠቅሙ የማጣቀሻ ምንጮችን (ጋዜጦችን፣መዝገበ ቃላትን፣ራዲዮ፣ወዘተ. የመገልገል ብልሃት ነው፡፡

- ማሸጋገር:- ቀደም ሲል በአፍ መፍቻ ወይም በሌላ ቋንቋ የተማሩትን የቃላት ዕውቀት የታላሚውን ቋንቋ ቃላት ትርጉም ለመገንዘብ በቀጥታ ተግባራዊ የማድረግ ብልሃት ነው፡፡

- ድግመ ቅንብር:- ሰለ ቃላት ትምህርት በአዲስ መልክ በማቀናጀት ትርጉም የሚሰጡ ዐረፍተ ነገሮችን መመስረት፣ ደጋግሞ መልመጃዎችን መስራት፡፡

- ማስታወሻ መያዝ:- ከተለያዩ መጽሕፍቶች የሚያገኙትን የእንግዳ ቃላት ፍቺና አጠቃቀም በአንድ ማስታወሻ ደብተር መዝግቦ በመያዝ ማጥናትና መለማመደ ነው፡፡

- ምሰላ፦ እንግዳ ቃላትና ጽንሰ ሀሳቦችን በቀላሉ ለመያዝና የረጅም ጊዜ ትውስታ ለመፍጠር ከሚታወቅ ተጨባጭ ነገር (ለምሳሌ የተለያዩ ፊልሞች፣ ስዕል፣ ዕቃ) ጋር በማያያዝ አዕምሯዊ ስዕል የመፍጠር ስልት ነው፡፡

ድምጸችን በመደበኛነት መለማመድ :- የንበት፣ የመጥበቅ፣ የመላላት፣ወዘተ. ልምምድ ማድረግ፤ በአንድ አይነት ወይም በተመሳሳይ ፊደል በተገነቡ ነገር ግን በንበት የሚለያዩ ቃላት ላይ ልምምድ ማድረግ፤

- ከዚህ በላይ ከምሁራኑ ሃሳብ ለመረዳት እንደተቻለው አዕምሮታዊ ብልሃቶች ተማሪዎች አንድን ነገር እንደት እንደሚሰሩ፣ እንደሚረዱ፣ እንደሚያስታውሱና አዕምሯዊ ምስል እንደሚከስቱ የሚያመላክት የአዕምሮ ስራ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡

### 2.7.4.1.3. አካካሽ ብልሃቶች

አካካሽ ብልሃቶች የታላሚውን ቋንቋ መሰረት በማድረግ ተማሪዎች በቃላት ዕውቀት ማነስ ምክንያት በተግባቦት ሂደት የሚደርስባቸውን ችግር ለመቋቋም የሚገለገሉባቸው ብልሃቶች ናቸው፡፡ Oxford (1990፡47) እንደገለጹት አካካሽ ብልሃቶች የተማሪው የቃላት ዕውቀት ክምችት እጦትን ለማካካስ የሚያግዙ መንገዶች ናቸው፡፡ ለቃላት ትምህርት የበለጠ ተገቢነት ያለው አካካሽ ብልሃት የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ ከአውድ የመገመት ብልሃት ነው፡፡

እነዚህ ብልሃቶች ተማሪው ሁለት የተለያዩ ፍንጮችን (መረጃዎችን) ማለትም ስነልሳናዊ (በቋንቋው ያለንን እውቀት) እና ኢ-ስነልሳናዊ ፍንጮችን በመጠቀም የአዳዲስ ቃላትን ትርጉም ለመገመት የሚረዱት ናቸው፡፡ ስነልሳናዊ ፍንጭ መጠቀም ማለት ለምሳሌ በንባባብ ወይም በማዳመጥ የሚያጋጥሙ አዳዲስ ቃላትን የቃል ክፍላቸውን በመለየት፣ ቅድመና ድህረ ግንድ ቅጥያን በመለየት፣ ተመሳሳይ ወይም ተቃራኒ ፍቻቸውን በመፈለግ የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ ከአውድ በመገመት መረዳት ማለት ሲሆን ኢ-ስነልሳናዊ ፍንጭ (እውቀት) በመጠቀም ማለት ስለርዕሰ ጉዳዩ ያለንን የቀደመ /ዳራዊ እውቀትን ወይም አጠቃላይ እውቀትን መሰረት በማድረግ የአዳዲስ ቃላት ፍቺ ከአውድ በመገመት የመረዳት ብልሃት ነው፡፡

### 2.7.4.2 ኢ-ቀጥተኛ ብልሃቶች

Oxford (1990:37) በዚህ ክፍል የሚመደቡ ብልሃቶች ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ለቃላት እውቀት መሻሻል የሚደግፉ ናቸው፡፡ የተማሪውን ዘወትር የታላሚውን ቋንቋ ተግባራት በግልጽ

መከናወንን የሚጠይቁ አይደሉም። ነገር ግን በተለያዩ መንገዶች ለቃላት ትምህርታቸው ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር የትምህርታቸውን ሂደት ለመምራትና ለማስማማት የሚያግዟቸው ብልሃቶች ናቸው። በዚህ ስር የሚካተቱ ዋና ዋና ንዑስ ብልሃቶችም (ልዕለአእምሯዊ፣ ስሜት-ነኪ ቁጥጥርና ማህበራዊ ብልሃቶች) ናቸው።

### 2.7.4.2.1 ልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶች

እነዚህ ብልሃቶች ተማሪው ትምህርቱን በዕቅድ ለመምራት፣ የትምህርቱን አካሄድና አሰራሩን ለመከታተል፣በአጠቃላይ ያሳየውን ለውጥና የትምህርቱን ውጤት ለመገምገም የሚጠቀምባቸው ብልሃቶች ናቸው (Oxford, 1990)። ልዕለ አእምሯዊ ብልሃቶች ተማሪዎች እንግዳ ቃላትን በቀላሉ ለመልመድና ለመማር ተገቢ የሆኑ የቃላት መማር ብልሃቶችን መምረጥ እንዲችሉ ይረዳቸዋል። ስለዚህ እነዚህ ብልሃቶች ተማሪዎች የቀረጹትን አላማ ለማሳካት፣ የተጠቀሙባቸውን ብልሃቶች ውጤታማነት በመገምገም የወደፊት የመማር አቅጣጫቸውን የሚወስኑበት በመሆኑ በተገቢ ሁኔታ እንዲጠቀሙበት ማስቻል ተገቢ ነው (Oxford 1990; Schmitt, 2000)።

ከምሁራኑ ሃሳብ ለመረዳት እንደተቻለው ልዕለ አዕምሯዊ ብልሃት ተማሪዎች በአዕምሯዊ ሂደት ውስጥ በራሳቸው የሚማሩበትን መንገድ የሚያስተካክል እውቀትንና የግንዛቤ ሂደትን የሚቆጣጠር መሆኑን መገንዘብ ተችሏል።

Brown (1994:142) Oxford (1990)ን በመጥቀስ በልዕለ አእምሯዊ ብልሃቶች በተማሪው የሚከናወኑ ተግባራት የሚባሉትን ከዚህ በታች ጠቅሰዋል።

- አላማና ግብ፦ ተማሪው ከቃላት ትምህርት ምን እንደሚጠብቅ አስቀድም የራስን አላማና ግብ መጣል ነው።
- ትኩረት መስጠት፡- ለቃላት ትምህርት ትኩረት ሰጥቶ ለመማር አስቀድሞ መወሰንና በራስ ግምገማ ተገቢ የቃላት ተግባራትን መርጦ ትኩረት ለመስጠት መወሰን ነው።
- ማቀድ፡- ለቃላት ትምህርት የራስን ግብና አላማ ማስቀመጥ፣ ከቃላት ትምህርቱ ምን እንደሚጠብቅ /እንደምትጠብቅ አስቀድሞ የማቀድ ብልሃት ነው።

- ራስን መገምገም ፦ በትምህርቱ ሂደት ተማሪው የራሱን የለመዳ ሂደት ከሌሎች ውጤታማ ከሆኑ ለማጆች ጋር በማስተያየት የራስን ሁኔታ የሚገመገምበት ነው፡፡

- ችግርን መለየት፦ በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት ለለመዳው ውጤታማነት የሚያግዘው የትምህርቱ ዋና አላማ ምን እንደሆነና በትምህርቱ ሂደት ለለመዳው እንቅፋት የሆኑ ችግሮች ካሉ ለይቶ በማጣራት ለመፍትሄ የሚዘጋጅበት ነው፡፡

- የልምምድ አጋጣሚዎችን ለማግኘት መጣር፡- የተገኘውን አጋጣሚ ሁሉ ተፈጥሮኣዊ በሆነ መንገድ ለመለማመድ መጠቀም፡፡
- ቋንቋን በምን መልኩ መማር እንደሚቻል መገንዘብ፡- የተለያዩ መጽሃፍትን በማንበብ ወይም ከሰዎች መረጃዎችን በማሰባሰብ ቋንቋን እንደት መማር እንደሚቻል ጥሩ ግንዛቤ መጨበጥ፡፡
- ማደራጀት፡- በቃላት ትምህርት አመቺ ተፈጥሮአዊ አካባቢ ሁኔታ መፍጠር፣ ለቃላት ትምህርት ወይም ጥናት ፕሮግራም ማዘጋጀት፡፡

### 2.7.4.2.2. ስሜት ነክ ቁጥጥር ብልሃቶች

ስሜት ነክ ብልሃቶች ከተማሪው ስሜት፣ ዝንባሌና መነቃቃት ጋር የተያያዙ ናቸው ፡፡ ተማሪው በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት የሚያድርበትን የፍርሃትና የጭንቀት ስሜት እንዲሁም አሉታዊ ዝንባሌ ለመቋቋም (ለመቆጣጠር) የሚጠቀማቸው ብልሃቶች ናቸው፡፡ Oxford (1990:141) ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች የሁለተኛ ቋንቋ ቃላትን በሚማሩበት ወቅት የሚያጋጥማቸውን የስሜትና የመነቃቃት ችግር በብቃት ይቋቋማሉ፡፡ በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጭ ከቋንቋው ተናጋሪዎች ጋር በሚፈጥሩት ግንኙነት የቋንቋው እውቀት ማነስና ለኀብረተሰቡ ባህል አዲስ መሆን በመማር ፍላጎትና በንቃት የመሳተፍ ስሜት ላይ በተወሰነ ደረጃ ጫናና የስሜት መረበሽ ማሳደራቸው የማይቀር ቢሆንም ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች በውስጣቸው የተፈጠረውን የመረበሽ ስሜት ለመቋቋም ይጥራሉ፡፡ ራሳቸውን እንደ አንድ የቋንቋ ተማሪ በመቁጠር በተተኳሪው ቋንቋ ፣ በህብረተሰቡና በባህሉ ላይ ቀና አመለካከት ይፈጥራሉ፡፡ እነዚህን ባህርያትም አስቀድሞ በመለየት ስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃትን በተገቢው መንገድ ወደ መጠቀም ይሄዳሉ፡፡ በዚህ ስር የሚካተቱ ዋና ዋና ብልሃቶችም የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ራስን ማዝናናት፦ በቃላት ትምህርት ወቅት የድካም የመሰላቸት ስሜት ለመቀነስ አካልና አእምሮን ዘና ማድረግ

- ራስን መሸለም፡- በቃላት ትምህርት ውጤታማ ሲሆኑ ራስን መሸለም፤ ለምሳሌ በቃላት ፈተና ጥሩ ውጤት ሲያገኙ ራስን ማድነቅ

- አዎንታዊ ገለፃ መስጠት፡- ለራስ እውቀት ጥሩ ግምትና አዎንታዊ መግለጫ መስጠት፣ በተለይም ከባድ የቃላት ተግባራትን ከመስራት በፊት የራስን ችሎታ ማድነቅ

- ሀላፊነትን፡- በትምህርቱ ሂደት መሳሳት እንደሚኖር በማመን ከባድ የቃላት ተግባራትን ስሜትን ተቆጣጥሮ ለማከናወን ኀላፊነትን ተቀብሎ መሳተፍ ለምሳሌ በሐሳብ ልውውጥ ሂደት ተገቢ ቃላትን መጠቀም ስለማልችል እሳሳታለሁ የሚል ስጋትን አስወግዶ ያለ ፍርሃት በንቃት መሳተፍ

- ስሜትን ማጋራት፡- በቃላት ትምህርት ላይ ያደረብንን ስሜት ለሌላ ማካፈል ለምሳሌ በትምህርቱ መደሰት አለመደሰትን፣ ከክፍል ጓደኞቹ ፣ ከመምህራን ወይም ከሌሎች ጋር መወያየት

### 2.7.4.2.3 ማህበራዊ ብልሃቶች

ተማሪዎች ቃላትን ሲማሩ ከአካባቢውና አብረው ከሚኖሩት ማህበረሰብ ጋር በመገናኘት ፣ በመግባባት፣ በመተባበርና በመስራት፣ ተጨማሪ ማብራሪያዎችን በመጠየቅ፣ ራሳቸውን በራሳቸው በማበረታታት ቋንቋውን የሚማሩበት ብልሃት ነው።

እንደ Oxford (1990) እንደ ገለጹት እነዚህ ብልሃቶች ተማሪው ከክፍል ጓደኞቹ ወይም ከሌሎች ሰዎች ጋር ማህበራዊ ተራክቦ በመፍጠር ቃላትን እንዲማር የሚረዱት ብልሃቶች ናቸው። ቋንቋን ለመማር የሌላ ሰው ተሳትፎ አስፈላጊ እስከ ሆነ ድረስ ተማሪዎችም ለቃላት ትምህርታቸው ውጤታማነት በጋራ ሊሰሩ ይገባል። በተማሪዎች የሚተገበሩ ማህበራዊ ብልሃቶች የሚከተሉት ናቸው።

- ባህላዊ ግንዛቤን ማዳበር፦ ስለታላሚው ቋንቋ ተናጋሪዎች ባህልና አኗኗር ያለን ግንዛቤ ማዳበር

- ከብጤ ጋር መተጋገዝ፦ የቃላትን ትምህርት ለጋራ አላማ ከክፍል ጓደኛ ጋር በቡድን በመስራት (በማጥናት) የቃላቱን ፍቺ በመለማመድ የቃላት ዕውቀትን የማሻሻል ብልሃትነው፡፡

- መጠየቅ፦ የአዳዲስ ቃላትን ትርጉም መምህራንን፣ የክፍል ጓደኛን ወይም ሌሎች ሰዎችን መጠየቅ፣ ወይም ስህተትን ማስተካከያ የእርምት ትብብር በመጠየቅ የቃላት እውቀትን የማዳበር ብልሃት ነው፡፡

- ራስን ማበረታታት፦ ተማሪው የቋንቋ ትምህርቱን በጥሩ ሁኔታ ባካሄደ ቁጥር እና ለመዳው ስኬታማ በሆነ መንገድ በተከናወነ ቁጥር ተማሪው ራሱን በመሸለምና በማነቃቃት ለቀጣይ ትምህርቱ ምቹ ሁኔታዎችን የሚያመቻችበት መንገድ ነው፡፡

ጠቅለል ባለመልኩ ከዚህ በላይ ከተለያዩ ምሁራን ሀሳብ በመነሳት ቃላትን የመማር ብልሃቶች ተማሪዎች የቃላት ትምህርታቸው ውጤታማነት በተለያየ መንገድ በመጠቀም ቃላትን እንዳውቁ ይረዳቸዋል፡፡ ይሁን እንጅ አፍፈትም ሆኑ ኢ- አፍፈት ተማሪዎች ብልሃቶቹን በተገቢው መንገድ በመገልገል የቃላት እውቀታቸውንና ተግባቦታዊ ብቃታቸውን ሊያዳብሩ ይችላሉ፡፡ በተለይ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች የOxford(1990)ን የቃላት መማር ብልሃቶች አከፋፈልን አንድ በአንድ ከተገለገሉባቸውና ተግባራዊ ካደረጓቸው የተሻለ የማዳመጥ ፣የመናገር፣የማንበብና የመጻፍ ክሂላቸው ዳብሮ በቃላት እውቀት ላይ ሰፊ ግንዛቤ እንድኖራቸው ያደርጋል፡፡

በሀገራችን አማርኛ ቋንቋ በትምህርትና በስራ ቋንቋነት ለረጅም ዘመናት በስፋት በማገልገሉና ብዙዎቹ የሀገራችን ስነጽሁፎች የተጻፉት በአማርኛ ቋንቋ በመሆኑ መድበለ ቃላቱ ሰፊ ነው፡፡ ይህን የቃላት ስብስብ ያለውን ቋንቋ ኢ- አፍፈት የሆኑ የአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎችን በመማርያ ክፍል ውስጥ መምህሩ በሚያቀርብላቸው የቃላት ትምህርት ብቻ የቃላት እውቀታቸው ወደ ተፈለገው ደረጃ ማድረስ አይቻልም፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች ቋንቋን የመማር ብልሃቶች በተለይም ቃላትን የመማር ብልሃቶች መሰረት አድርገው ቃላትን በራሳቸው ጥረት እንድማሩ ማበረታታት የቃላት እውቀታቸው ከፍ እንድል ያደርጋል፡፡

## 2.8 ቀደምት ተዛማጅ ጥናቶች

በዚህ ርዕስ ስር ለመቃኘት እንደተሞከረው ከዚህ ጥናት ጋር በርዕሱ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ግንኙነት ያላቸው ጥናቶች ተገኝተዋል፡፡ በመሆኑም በሀገራችን ውስጥ በቃላት አተገባበር ፣በቃላት መማር ብልሃቶች ዙርያ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያነት የተሰሩ ጥናቶች አሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል ንጋቱ (2000) "በሲዳምኛ  ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዋች የአማርኛ ቃላትን ሲማሩ የሚጠቀሙባቸው ቃላትን የመማር ብልሃቶች ፍተሻ" በሚል ርዕስ ጥናት ያቀረቡ ሲሆን የጥናቱ አላማ የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን ሲማሩ የሚገለገሉባቸውን የመማር ብልሃተቶች ማጥናት ነው፡፡ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹም የጽሁፍ መጠይቅ በዋናነት፣ቃለ መጠይቅ በአጋዥነት ተጠቅመዋል፡፡  የጥናቱ ውጤትም ተማሪዋቹ የአማርኛ ቃላትን የመማር ብልሃቶች አጠቃቀም በብቃት ላይ የተመሰረተ አለመሆኑን ያመላክታል፡፡

ይህ ጥናት በንጋቱ ከተካሄደው ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ከርዕሱ ጋርና ከመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹ ጋር ሲሆን ልዩነቱ ደግሞ ከአላማ፣ ከአፍመፍቻ ቋንቋ፣ ከትኩረት አቅጣጫ እና በአማራ ክልል በኦሮሚያ ብሔረሰብ ልዩ ዞን በደዋ ጨፋ ወረዳ በዚህ ርዕስ ዙርያ  ስላልተጠና ከቦታ አንጻር ይለያል፡፡

ሌላው ጥናት እሸቱ አጋ (1997)"በአድስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ ሶስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ያተኮረ የቃላት ትምህርት የክፍል ውስጥ አቀራረብ ግምገማ" በሚል ርዕስ ጥናት ያካሄዱ ሲሆን ከጥናቱ የተገኘው አብዛኞቹ መምህራን የቃላት ትምህርትን በክፍል ውስጥ ሲያቀርቡ የተለያዩ አውዶችን አለመጠቀም፣በቅድመ ንባብ ጊዜ አዳዲስ ቃላትን አለማስተዋወቃቸው፣ቃላትን ከቋንቋ ክሂሎች ጋር በማቀናጀት አለማቅረባቸው እንዲሁም በቃላት አጠቃቀም ላይ አለማተኮራቸው የታዩ ድክመቶች ሲሆኑ ይህም የተማሪዎችን የመማር ተነሳሽነት ዝቅ እንደሚያደርገው በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡

ይህ ጥናት ከላይ ከቀረበው ከእሸቱ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው በምዕራፍ ሁለት በሚቀርቡት አንዳንድ ጽንሰሀሳባዊ ማብራሪያዎች  ሲሆን ልዩነቱም  በዋነኝነት  የተማሪዎችን  የቃላት መማር  ብልሃቶች መለየትና መተንተን በመሆኑ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ይህ ጥናት

የመረጃ መሰብሰቢያ መሳርያዎቹ  የጽሁፍ መጠይቅና ቃለ መጠይቅ እንዲሁም  የጥናቱ ተተኳሪዎች አማርኛ ቋንቋን እንደ ሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች በመሆናቸው ይለያል፡ ፡

ደረበ ሙሉ (1999) "በትግርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቃላት ትምህርት አቀራረብ ፍተሻ" በሚል ርዕስ ጥናት ያቀረቡ ሲሆን የጥናቱ አላማ  የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቃላትን ትምህርት እንደት እንደሚያቀርቡ መፈተሽ ነው፡፡ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹም ምልከታና የጽሁፍ መጠይቅ ሲሆን የተከተለው የአጠናን ዘዴ አይነታዊና አሃዛዊ ምርምር ነው፡፡ የጥናቱ ውጤትም መምህራን ቃላትን ሲያስተምሩ የተለመዱትን የቃላት ማስተማሪያ ዘዴዎች አዘውትረው እንደሚጠቀሙና የቃላት መማር ብልሃቶችን ባጣመረ መልኩ ስለማያቀርቡ አቀራረቡ ተማሪዎችን አሳታፊ አለመሆኑና የተማሪዎች የቃላት ችሎታም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ በጥናታቸው አረጋግጠዋል፡፡

ይህ ጥናት በደበበ ከተከሄደው ጥናት ጋር የሚያመሳስለው በቃላት ትምህርት አቀራረብ የሁለተኛ ቋንቋ መማር ብልሃቶችን ስለሚመረምርና በዋነኝነት የሚያተኩረው በቃላት መማር ብልሃቶች በመሆኑ ነው፡፡

ይርጋ (1993)"አፋቸውን በከፍኛ የፈቱ ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች አማርኛ ሲማሩ የሚገለገሉባቸው ቋንቋን የመማር ብልሃቶች እና የመምህራን ግንዛቤ አሰሳ"በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ አላማ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች ቋንቋን ሲማሩ የሚገለገሉባቸው የመማር ብልሃቶችና የቋንቋ መምህራን በነዚህ ብልሃቶች ዙርያ ያላቸውን የግንዛቤ ሁኔታ መመርመርና ማጥናት ነው፡፡ በጥናቱ ያገኙት ውጤትም "ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች"ይገለገሉባቸዋል የተባሉ ስድስቱም አይነት ዋና ዋና የቋንቋ ብልሃቶቸ ከሞላ ጎደል በጥቅም ላይ የሚውሉ መሆኑን፣ የቋንቋ መምህራኑ በተማሪዎቻቸው የመማር ብልሃቶች ዙርያ ግንዛቤ የለላቸው በመሆኑ በተማሪዎቹ ቋንቋ የመማር ስልት የትምህርት አቀባበል ሂደትና በመምህራኑ የማስተማር አቀራረብ ሂደት መካከል አለመጣጣም ያለ መሆኑን ነው፡፡

ይህ ጥናት ከይርጋ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ቋንቋን የመማር ብልሃቶችን በመዳሰስ ተቀራራቢነት ቢኖረውም ከቃላት መማር ብልሃቶች አንጻር የተጠና ስለሆነ ይለያል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የይርጋ ጥናት ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎችን ብቻ ትኩረት ያደረገ ሲሆን ይህ ጥናት ግን በኢ-አፍፊት ተማሪዎች ላይ ትኩረት ያደረገ በመሆኑ ይለያል፡፡

አፈወርቅ (2008) "በጋሞ ጎፋ ዞን ምዕራብ አባያ ወረዳ ሁለተኛ ደረጃ መሰናዶ ትምህርት ቤት የሚማሩ አፈፊትና ኢ-አፈፊት የሆኑ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን ሲማሩ የሚጠቀሙባቸው ቃላት የመማር ብልሃቶች ትንተና" በሚል ርዕስ ጥናት ያካሄዱ ሲሆን የጥናቱ አላማም አፍፊትና ኢ-አፍፊት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ቃላትን ለመማር የሚገለገሉባቸውን ብልሃቶች መተንተን ነው፡፡ የጥናቱ ግኝትም ኢ-አፍፊት ተማሪዎች ከአፍፊቶቹ የተሻለ የቃላት መማር ብልሃት አጠቃቀም እንዳላቸው አሳይቷል፡፡

ይህ ጥናት ከአፈወርቅ ጋር የሚያመሳስለው በቃላት መማር ብልሃቶች ሲሆን ልዩነቱ ደግሞ ይህ ጥናት ኢ-አፍፊቶቹን ብቻ ትኩረት አድርጎ ሲያጠና የአፈወርቅ ግን በንጽጽር ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ብልሃቶችን አብዝቶ መጠቀም ለሁለተኛ ቋንቋ ጠቀሜታ እንዳለው ያመላከተ በመሆኑ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎቹ ተመሳሳይ ይሁኑ እንጅ በጥያቄዎቹና በአካሄድ ላይ ምንም ተዛምዶ የላቸውም፡፡ በመሆኑም ከትኩረት አቅጣጫ፣ ከአላማና ከቦታ አኳያ ይህ ጥናት ይለያል፡፡

ተክላይ (2000) "በትግርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የስምንተኛና የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ንባብ ጊዜ የንባብ ብልሃት አጠቃቀምና የመምህራን ግንዛቤ ተጣጥም ፍተሻ" በሚል ርዕስ ጥናት ያካሄዱ ሲሆን በቋንቋ ችሎታቸው በከፍተኛ፣ በመካከለኛና ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ተተኳሪ ተማሪዎች ከንባብ ብልሃት አጠቃቀማቸው ጋር ተጣጥሞ ያለው መሆን አለመሆኑን መመርመርና የአማርኛ መምህራኑ የንባብ ብልሃት ግንዛቤ ከተማሪዎች የንባብ ብልሃት አጠቃቀም ጋር ተጣጥሞ ያለው መሆን አለመሆኑን በሚል አላማ ጥናት አካሂደዋል፡፡ በጥናቱም ያገኙት ውጤት በቋንቋ ችሎታቸው በተለያየ ደረጃ የሚገኙ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች የንባብ ብልሃትን በብዛት በመጠቀም በቋንቋ ችሎታቸው ካገኙት ደረጃ ጋር ተጣጥሞ በማሳየት ረገድ ከአስረኛ ክፍል ተሽለው መገኘታቸውና የመምህራኑ የንባብ ብልሃት ግንዛቤም ከተማሪዎች የንባብ ብልሃት አጠቃቀም ጋር ያለው ተጣጥሞ ዝቅተኛ መሆኑን ነው፡፡

ይህ ጥናት ከተክላይ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው የቋንቋ መማር ብልሃቶችን በመዳሰስ ተቀራራቢነት ሲኖረው ልዩነቱ ደግሞ በአንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሚገኙ በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች በቃላት መማር ብልሃቶች ላይ ያተኮረ ነው፡፡ የተክላይ ጥናት ግን በንባብ ላይ ያተኮረ በመሆኑ ይለያል፡፡

በላይነሽ (2002) "በኦሮሚያ ክልል የመቱ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን ለመማር የሚገለገሉባቸው የመማር ብልሃቶች ፍተሻ" በሚል ርዕስ ሲሆን የጥናቱ አላማም አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን ለመማር የሚገለገሉባቸውን ብልሃቶች መፈተሽ ነው፡፡ የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ የጽሁፍ መጠይቅና ቃለ መጠይቅ ሲሆኑ የተሰበሰቡት መረጃዎች ተተንትነው የተገኘው ውጤትም ተጠኚዎቹ ቃላትን ሢማሩ ቃላትን የመማር ብልሃት አጠቃቀማቸው ዝቅተኛ መሆኑን በጥናታቸው አሳይተዋል፡፡

ይህ ጥናት ከበላይነሽ ጋር የሚያመሳስለው በቃላት መማር ብልሃቶች ሲሆን ልዩነቱ ደግሞ ብልሃቶችን አብዝቶ መጠቀም ለሁለተኛ ቋንቋ ጠቀሜታ እንዳለው ያመላከተ በመሆኑ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎቹ ተመሳሳይ ይሁኑ እንጅ በጥያቄዎቹና በአካሄድ ላይ ምንም ተዛምዶ የላቸውም፡፡ በመሆኑም ከትኩረት አቅጣጫ፣ከአላማና ከቦታ አኳያ ይህ ጥናት ይለያል፡፡

በተጨማሪም ብሩክታዊት (2001)"በመቀሌ ከተማ በሚገኙ በሶስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ የመንግስት ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል የቃላት ትምህርት አተገባበር ፍተሻ" በሚል ርዕስ ጥናት አካሂደዋል፡፡ የጥናቱ ዋና አላማ የቃላት ትምህርት የክፍል ውስጥ አቀራረብ ከዘመናዊ የቃላት ትምህርት አመለካከት አንጻር በምን አይነት ደረጃ ላይ እንደሚገኝ መመርመር ነው፡፡ የመረጃ መሰብሰቢያዎቹም ምልከታ፣የጽሁፍ መጠይቅና የሰነድ ፍተሻ ሲሆን የጥናቱ ዘዴም አይነታዊና አሃዛዊ ምርምርን የተከተለ ነው፡፡

ይህ ጥናት ከብሩክታዊት ጥናት ጋር የሚያመሳስለው በምዕራፍ ሁለት በሚቀርቡ አንዳንድ ጽንሰ ሐሳባዊ ማብራሪያዎች እና በጽሁፍ መጠይቅ ሲሆን ልዩነቱ ደግሞ የብሩክታዊት ጥናት ትኩረት በቃላት ትምህርት አተገባበር ላይ ሲሆን ያሁኑ ጥናት ግን በተማሪዎች የቃላት

መማር  ብልሃት አጠቃቀም ላይ ያተኮረ ነው፡፡ እንዲሁም የአሁኑ ጥናት በክፍል ደረጃ፣በጥናቱ ቦታ፣ዘመንና በአላማ የተለየ ነው፡፡

ባጠቃላይ እነዚህ ከላይ የተገለጹት ጥናታዊ ስራዎች ከዚህ ጥናት ጋር የሚለያዩበትና የሚመሳሰሉበት ጉዳዮች የተገለጹ ቢሆንም አንዳንዶቹ በጥናቱ መነሻነትም ሆነ በማጣቀሻ ምንጭነት አስተዋጽኦ ማበርከታቸው መዘንጋት የሌለበት ጉዳይ ነው

# ምዕራፍ ሦስት

# የጥናቱ ንድፍና ዘዴ

## 3.1 የጥናቱ ንድፍ

ይህ ጥናት የሚካሄደው በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን ሲገለገሉ የቃላት መማር ብልሃት አጠቃቀምን ለመተንተን ነው፡፡ በመሆኑም ይህን አላማ ማሳካት ይቻል ዘንድ አጥኚው ገላጭ የምርምር ዘዴን መርጧል፣ ዘዴውን በመጠቀም ተማሪዎች የሚጠቀሟቸውን ብልሃቶች ምን እንደሚመስሉ ከተለያዩ ምንጮች ያገኛቸውን መረጃዎች መሰረት በማድረግ በገለጻ ስልት ቀርቧል፡፡

## 3.2. የናሙና አመራረጥ

### 3.2.1. የክልልና የወረዳ የናሙና አመራረጥ

አጥኚው ይህን ጥናት ለማካሄድ በአማራ ክልል የሚገኘውን የኦሮሚያ ብሔረሰብ ልዩ ዞን ደዋ ጨፋ ወረዳን በአመች የናሙና ዘዴ (Convenience sampling) ተመርጧል፡፡ ዞኑና ወረዳው የተመረጠበት ምክንያት አጥኚው ካለው ወቅታዊ ሁኔታዎች የገንዘብና የጊዜ እጥረት አኳያ በወረዳው እያስተማረ የሚያጠናው በመሆኑና በዚሁ ልዩ ዞን ለአስር አመት ያህል በማስተማር ስራ በመቆየቱ ተጠኚዎችን በቅርብ ማገኘት ስለሚችል ነው፡፡

### 3.2.2 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

በደዋ ጨፋ ወረዳ ውስጥ ከሚገኙ አራት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል በአመቺ የናሙና አመራረጥ ዘዴ የሩፍሴ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተተኳሪ ሆኗል፡፡ ትምህርት ቤቱን ለመምረጥ ከወረዳው ትምህርት ቢሮ በተገኘው መረጃ መሠረት በደዋ ጨፋ ወረዳ ውስጥ 4 የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መኖራቸው ታውቋል፡፡ በዚሁ መሰረት በወረዳው ካሉት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል አንድ ትምህርት ቤት በአመቺ ናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመርጧል፡፡ ለዚህ ምክንያቱ የተመረጠው ትምህርት ቤት ለገጠሩ ነዋሪ አማካኝ ቦታ ላይ የተሰራ በመሆኑ እና የኦሮምኛ ቋንቋ አፈፊት ተማሪዎች የሚማሩበት ትምህርት ቤት በመሆኑ ነው፡፡ የተመረጠው ትምህርት ቤት ሩፍሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው፡፡ አመራረጡም የአመቺ ናሙና ዘዴ በመጠቀም ከሩፍሴ ሁለተኛ ደረጃ

ትምህርት ቤት 10ኛA፣ B ፣ C እና D በአጠቃላይ አራት ምድቦች ተመርጠው በጥናቱ ውስጥ ታቅፈዋል፡፡

ለጥናቱ መረጃ የሚሰበሰብበት ትምህርት ቤት ተለይቶ ከታወቀ በኋላ ተከታዩ ተግባር የክፍል ደረጃ አመራረጥና ተተኳሪ ተማሪዎችን መምረጥ ነው፡፡

### 3.2.3 የክፍል ደረጃ አመራረጥ

ለዚህ ጥናት የአስረኛ ክፍል በአላማ ተኮር የንምና ዘዴ ተመርጧል፡፡ አስረኛ ክፍል የተመረጠበት ምክናየት የክፍል ደረጃው አጠቃላይ የሁለተኛ ደረጃ አማካይ ላይ በመሆኑ በዚህ ደረጃ ላይ ያለውን የቃላት መማር ብልሃት አጠቃቀም እና የተግባቦት ሁኔታቸውን በጥልቀት በማየትና በማሰብ ነው፡፡ ከተጠቀሰው የክፍል ደረጃ ዝቅ ለማለት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ብቃታቸው አናሳ በመሆኑና ትክክለኛ መረጃ መስጠት ስለማይችሉ ነው፡፡ የ11ኛ እና 12ኛ ክፍል ተማሪዎችን ተጠኚ ያልተደረገበት ምክንያት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ስለሚማሩ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ስለማይሰጥ ነው፡፡

### 3.2.4 የተማሪዎች የናሙና አመራረጥ

የተማሪዎቹ አመራረጥ የተወሰነው በናመናነት በተመረጠው ትምህርት ቤት ውስጥ በ2015 ዓ.ም በመደበኛነት በ10ኛ ክፍል ተመዝግበው ከሚማሩ ተማሪዎችና የሚማሩበትን ምድቦች ብዛት መሠረት በማድረግ በአመቺ ናሙና ዘዴ ተመርጠዋል፡፡ ይህ ዘዴ የተመረጠው ለሁሉም ተማሪዎች እኩል የመመረጥ እድል ስለሚሰጣቸው ነው፡፡ በዚሁ መሠረት በሩፍሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከአራቱም ምድቦች በኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎች በሁለት የመማሪያ ክፍል ተለይተው የሚማሩ በመሆናቸው መጀመሪያ የተማሪውን ቁጥር መለየት ነው፤ከዚህ አንፃር በተገኘው መረጃ መሠረት በአራቱም ምድቦች የሚማሩ ተማሪዎች ወንድ 110፣ ሴት 86 በድምሩ 196 ናቸው፡፡ ከነዚህ ተማሪዎች ውስጥ 10ኛA ወንድ 24፣ ሴት 14 በድምሩ 38 እና 10ኛB ወንድ 22፣ ሴት 10 በድምሩ 32 በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ናቸው፡፡

ከነዚህ ተማሪዎች ወንድ 46፣ ሴት 24 በድምሩ 70 ተማሪዎችን በአመቺ ናሙና ዘዴ ሁለቱንም ክፍል በማካተት እንዲመረጡ ተደርጓል በአጠቃላይ 70 ተማሪዎች ለጥናቱ ተተኳሪ በመሆን ተመርጠዋል፡፡

## 3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ቀደም ሲል እንደተገለጸው የዚህ ጥናት ትኩረት የተማሪዎችን የቃላት መማር ብልሃት መለየትና መተንተን ነው፡፡ የጥናቱ ተሳታፊ ከሆኑት ተማሪዎች የሚሰበሰቡት መረጃዎች አስተማማኝ ይሆኑ ዘንድ የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያዎች መጠቀም አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡ ፡ ጥቅም ላይ የዋሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በዋነኝነት የጽሁፍ መጠይቅ ሲሆን በአጋዥነት ደግሞ ቃለ መጠይቅ ናቸው፡፡

### 3.3.1 የጽሑፍ መጠይቅ

ይህ ጥናት መረጃዎችን ለመሰብሰብ የoxford (1990) የቃላት መማር ብልሃቶች መሰረት ያደረጉ 30 የጽሑፍ መጠይቆች ተዘጋጅተዋል፡፡ ይህም ማለት የቃላት መማር ብልሃት አከፋፈል ሞደሉን ወደ አማርኛ በመመለስ ነው፡፡ የመጠይቆቹ አብይ ትኩረት የሚሆነው በአዕምሮታዊ፣ በትውስታ ፣አካካሽ፣ ልእለአዕምሮታዊ፣ ማህበራዊና ስሜትነክ ቁጥጥር ብልሃቶችን አካቶ የሚይዝ ነው፡፡ የቃላት መማር ብልሃቶችን አከፋፈልን መሠረት ያደረጉ መጠይቆችን በአጥኚው ከተዘጋጁ በኃላ 30 ጥያቄዎችን ተገቢነትና አስተማማኝነታቸውን ለመፈተሽ ጥናቱ ከመካሄዱ በፊት ከዘጠነኛ እስከ አስራሁለተኛ ክፍል የሚያስተምሩ ሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን፣ሁለተኛ ዲግሪ ያላት አንድ የአማርኛ ቋንቋ መምህርትና ሁለተኛ ዲግሪ ያለው አንድ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህራን እንዲያዩትና እንዲገመግሙት ተደርጓል፡፡

በመጨረሻም ለጥናቱ አማካሪ ቀርበው ተጨማሪ ማሻሻያና አስተያየት ከተሰጡባቸው በኃላ የተገኘውን መረጃ መሰረት በማድረግ መሻሻል ያለባቸው ተሻሽለው፣ መወገድ ያለባቸው ተወግደውና የአሻሚነት ባህሪ የታየባቸውን በማብራራት ግልጽ የማድረግ ተግባራት ተከናውኗል፡፡ ከዚያም በባለ ሙያ ቅድመ መረጃ ስብሰባ የሙከራ ጥናት ተደርጎባቸውና ተፈትሸው ከተረጋገጡ በኂላ ለመረጃ ስብሰባ ውለዋል፡፡ የጽሑፍ መጠይቁ አቀራረብ የቃላት መማር ብልሃቶቹን የሚገልጹ ሀሳቦችን በአራት አማራጭ መልሶች ማለትም ሁልጊዜ፣አንዳንድ ጊዜ፣ አልፎ አልፎና በጭራሽ የሚሉ አማራጮችን በማቅረብ ተተኳሪ ተማሪዎች አንዱን ብቻ መርጠው እንድሞሉ የሚጠይቅ ነው፡፡

### 3.3.2 ቃለ መጠይቅ

ቃለ መጠይቁ የሚቀርበው ለተማሪዎች ሲሆን አላማውም በጽሁፍ መጠይቁ የተገኙትን መረጃዎች ትክክለኛነት ለማረጋገጥና ተጠኚዎቹ ስለቃላት መማር ልምዳቸው አስመልክተው በሚሰጡት ማብራሪያ ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ ቃላትን የመማር ብልሃቶች መሰረት ያደረጉ አስር ጥያቄዎች በመጀመርያ በአጥኚው ከተዘጋጁ በኂላ ከዚያም ሁለተኛ ድግሪ ያለው አንድ የእንግሊዘኛ መምህር፣ሁለተኛ ድግሪ ያላት አንድ የአማርኛ ቋንቋ መምህርትና የመጀመሪያ ድግሪ ያላቸው ሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እንድገመግሙትና አስተያየት እንድሰጡ ተደርጓል፡፡ ከዚያም ለጥናቱ አማካሪ ቀርበው ተጨማሪ ማሻሻያ ተደርጎባቸው መወገድ ያለባቸው ተወግደውና ተሻሽለው ከተዘጋጁ በኂላ ከሁለቱም ክፍሎች የጽሁፍ መጠይቁን ከሚሞሉት መካከል በነሲብ ናሙና በመጠቀም ከ10ኛ"A" ክፍል ሰባት እና ከ10ኛ"B " ሰባት በጥቅሉ አስራ አራት ተማሪዎችን ቃለ መጠይቅ ማድረግ ተችሏል፡፡የቃለመጠይቁን መረጃ አወሳሰድ በተመለከተ ተተኳሪ ተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቁን ሞልተው ከጨረሱ በኂላ ወዳውኑ ከአስረኛ "A"ሰባትና ከአስረኛ"B" ሰባት ተማሪዎች ተመርጠው ቃለመጠይቅ እንድሰጡ ተደርጓል ፡፡ ምክናየቱም ከጽሁፍ መጠይቁ ጋር ተያያዥነት ያላቸው መጠይቆች ስለሆኑ በቀላሉ አስታውሰው መረጃ እንድሰጡ ተፈልጎ ነው፡፡

## 3.4 የመረጃ አተናተን ዘዴ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ቃላትን የመማር ብልሃት አጠቃቀማቸውን መለየትና መተንተን ነው፡፡ ይህን አላማ ከግብ ለማድረስ በጽሁፍ መጠይቅ አማካኝነት የተገኙ መረጃዎችን በማካተት ቃላትን የመማር ብልሃቶች ማለትም አዕምሮታዊ ፣ አካካሽ፣ ትውስታ ፣ ልዕለ አዕምሮታዊ ፣ ስሜት ነክ ቁጥጥርና ማህበራዊ ብልሃቶችን ያካተተ በማድረግ ከተሳታፊዎቹ የተገኙትን መረጃዎች ከተመዘገቡ በኂላ ለትንታኔ ከመቅረባቸው በፊት መልሶቹ በትክክል መሞላታቸው ተጣርቷል፡፡ መረጃዎቹም ለትንተና በሚያመች መልኩ ኮድ ተደርገው በውጤት መመዝገቢያ ሰንጠረዥ ላይ እንዲሰፍሩ ተደርጓል፡፡ መረጃዎቹ እንደየባህሪያቸው ተለይተውና አስፈላጊው ማጣራት ተደርጎባቸው በቁጥርና በመቶኛ በመጠቀም ገላጭ የትንተናን ዘዴ በዋናነት.፣በአጋዥነት አሃዛዊን በመጠቀም በቃለ መጠይቅ አማካኝነት ከተሰበሰቡ መረጃዎች ጋር እየተደጋገፉ ተተንትነዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃ ትንተና እና የውጤት ማብራሪያ

## 4.1, የቀጥኛ ብልሃቶች ትንተና

### 4.1.1 የትውስታ ብልሃቶች ውጤት ትንተና

ከላይ በምዕራፍ ሁለት ስር በተዛማጅ ጽሁፍ ክለሳ ውስጥ ጥናቶች ለማሳየት እንደሞከሩት "የትውስታ ብልሃቶች ተማሪው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርቱን ሲማር ያገኛቸውን ሀሳቦች በአዕምሮው መዝግቦ በመያዝ የረጅም ጊዜ ትውስታ በመፍጠር፣ በአስፈላጊው ጊዜ አስታውሶ መጠቀም እንዲችል የሚያግዙ ብልሃቶች ናችው" (Oxford 1990) ።

ከዚህ በታች ከ1-6 የቀረቡት በጽሁፍ መጠይቁ የተካተቱ ጥያቄዎች የትውስታ ብልሃቶችን ማለትም በመቦደን፣ በማያያዝ፣ ድምጽን በመወከል፣ ምስል በመፍጠር፣ በንግግር ወይም በጽሁፍ በማስገባት መለማመድና በድርጊት በማሳየት የትውስታ ብልሃት አጠቃቀምን ለመለየት ቀርበዋል። ከዚህም በተጨማሪ በጽሁፍ መጠይቁ የተገኙትን መረጃዎች ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ተያያዥነት ያላቸው ቃለ መጠይቆች ለተጠኚ ተማሪዎች ቀርበዋል።

**ሰንጠረዥ1:- ማቧደንን የሚጠይቁ የትውስታ ብልሃቶች ላይ ያሳዩት አጠቃቀም**

| ተቁ | ብልሃቶች | የተጠኚ ተማሪዎች ምላሽ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁልጊዜ | | አንዳንድ ጊዜ | | አልፎ አልፎ | | በጭራሽ | |
| | | በቁጥር | በ % | በቁጥር | በ % | በቁጥር | በ % | በቁጥር | በ % |
| 1 | የአማርኛቃላትን ከተማርኩ በሁዋላ ለማስታወስ፣በቃል ክፍላቸው ለምሳሌ ስምችን በአንድ ወገን፣ግሶችንና ቅጽሎችን በሌላ ወገን እመድባቸዋለሁ | 10 | 14.3 % | 11 | 15.7 % | 31 | 44.3 % | 18 | 25.7% |
| 2 | ተመሳሳይና ተቃራኒ ትርጉም ያላቸውን ቃላት በአንድ ላይ እመድባቸዋለሁ:: | 13 | 18.6 % | 9 | 12.8 % | 26 | 37.1 % | 22 | 31.4% |

**ተራ ቁጥር 1** ተጠኚ ተማሪዎች እንግዳ ቃላትን በቀላሉ ለመማርና ለማስታወስ በቃል ክፍላቸው የመመደብ ብልሃታቸውን ለመለየት ጥያቄ ቀርቦላቸዋል፡፡ ከዚህ በላይ በቀረበው ሰንጠረዥ 1 እንደሚያመለክተው 31(44.3%) ተጠኚዎች ንግግሮችን ሲያዳምጡ ወይም የተለያዩ ጽሁፎችን ሲያነቡ የሚያጋጥማቸውን አዳዲስ ቃላት አልፎ አልፎ በቃል ክፍላቸው እንደሚቦድኑ ምላሽ ሲሰጡ፣ 18(25.7%) ተማሪዎች ብልሃቱን በጭራሽ እንደማይጠቀሙ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ 11(15.7%) ተጠኚዎች እንግዳ ቃላትን በቀላሉ ለማስታወስ በቃል ክፍላቸው ለመመደብ አንዳንድ ጊዜ የሚጠቀሙ ሲሆን፣ 10(14.3%) ተማሪዎች ደግሞ ሁልጊዜ እንደሚጠቀሙ መረጃው ይጠቁማል፡፡

**ተራ ቁጥር** 2 ኢ-አፍፊት ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን ለመማርም ሆነ ለማስታወስ ቃላቱን በፍች ተመሳሳይነትና ተቃራኒነት የማደራጀት ብልሃት እንደሚጠቀሙ ተጠይቀው 26(37.1%) ተማሪዎች ብልሃቱን አልፎ አልፎ ሲጠቀሙ፣ 22(31.4%) ተማሪዎች በጭራሽ ብልሃቱን የማይጠቀሙ ናቸው፡፡ በአንጻሩ 13(18.6%) ተጠኚዎች በፍች ተመሳሳይና ተቃራኒ ቃላትን በማደራጀት ሁልጊዜ እንደሚጠቀሙ ሲገልጹ፣ 9(12.8%) ተማሪዎች ደግሞ ብልሃቱን አንዳንድ ጊዜ እንደሚጠቀሙ መረጃው ያመለክታል፡፡

ከዚህ በላይ በቀረበው የጽሁፍ መጠይቅ ለመረዳት እንደተቻለው ተጠኚ ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን ለማስታወስ በሚመቻቸው ትርጉም ባለው መልኩ ተመሳሳይ ይዘት ያላቸውን ቃላት በአንድነት በማቧደንና የቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ይዘት ያላቸውን በማደራጀት ከአዕምሮአቸው ጋር በማያያዝ ለትውስታ የማመቻቸት ብልሃታቸው ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም አብዛኞቹ ተማሪዎች ብልሃቶቹን አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙበት የትንተናው ውጤት ያሳያል፡፡

**ሰንጠረዥ 2፦** ማያያዝና በድርጊት ማሳየትን በሚጠይቁ ብልሃቶች ላይ ያሳዩት አጠቃቀም

| ተ ቁ | ብልሃቶች | የተጠኚ ተማሪዎች ምላሽ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁልጊዜ | | አንዳንድ ጊዜ | | አልፎ አልፎ | | በጭራሽ | |
| | | በቁጥር | በ % | በቁጥር | በ % | በቁጥር | በ % | በቁጥር | በ % |
| 3 | አዳዲሶቹን ቃላት ካየሁዋቸው ቦታ ጋር (ለምሳሌ፦መጽሀፍ፣ሰሌዳ፣ቪድዮቤት፣ ወዘተ.) ጋር አያይዤ ለማስታወስ እሞክራለሁ | 8 | 11.4 % | 15 | 21.4 % | 30 | 42.9 % | 17 | 24.3 % |
| 4 | አዳዲስ የአማርኛ ቃላትን ከስዕሎች ጋር አያይዤ ለማስታወስ እሞክራለሁ | 9 | 12.8 % | 13 | 18.6 % | 27 | 38.6 % | 21 | 30% |
| 5 | አዳዲስ ቃላትን ለማስታወስ እንዲችል ዓረፍተነገር እሰራባቸዋለሁ | 6 | 8.6% | 17 | 24.3 | 32 | 45.7 % | 15 | 21.4 % |
| 6 | አዲስ የተማርኩትን ቃል የድርጊት ሲሆን እለማመዳለሁ ለምሳሌ "ሮጠ" የሚለውን ቃል በመሮጥ ወይም እየሮጥኩ እለማመዳለሁ | 11 | 15.7 % | 19 | 27.1 % | 31 | 44.3 % | 9 | 12.8 % |

**ተራ ቁጥር 3** አዳዲስ ቃላትን በቀላሉ ለማስታወስ ተጠኚ ተማሪዎች ቃላቱን ከተገኙበት ቦታጋር በማያያዝ የትውስታ ብልሃታቸውን ተጠይቀው 30(42.9%) ተማሪዎች አልፎ አልፎ ከቦታ ጋር በማያያዝ እንደሚጠቀሙ ሲገልጹ፣ 17(24.3% ) ተጠኚዎች በጭራሽ አንጠቀምም ብለው ገልጸዋል ። በሌላ በኩል ደግሞ 15(21.4% ) ተማሪዎች አንዳንድ ጊዜ የሚገለገሉ ሲሆን፣ 8(11.4% ) ተማሪዎች ደግሞ ብልሃቱን ሁልጊዜ እንደሚገለገሉ መረጃው ይጠቁማል።

**ተራ ቁጥር 4** አዳዲስ የአማርኛ ቃላትን በቀላሉ ለመማርና ለማስታወስ ተማሪዎች ቃላትን ከስዕሎች ጋር እንድያይዙ ተጠይቀዋል። በሰንጠረዥ2 እንደሚያመለክተው 27(38.6%)ተጠኚዎች ብልሃቱን ከስዕሎች ጋር በማያያዝ አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ ሲገልጹ፣ 21(30% ) ተማሪዎች ደግሞ በጭራሽ ብልሃቱን እንደማይጠቀሙ ምላሽ ሰጥተዋል፡

፡ በሌላ መልኩም 13(18.6% )ተማሪዎች አንዳንድ ጊዜ ሲጠቀሙ፣ 9(12.8%) ተማሪዎች ደግሞ ብልሃቱን ሁልጊዜ እንደሚጠቀሙ መረጃው ያመላክታል፡፡

**ተራ ቁጥር** 5 ተማሪዎች እንግዳ ቃላትን ለመማርና ለማስታወስ እንድችሉ የተለያዩ ዓረፍተ ነገሮችን እንድመሰርቱ ተጠይቀዋል፡፡ ከላይ በሰንጠረዥ 2 እንደሚያመለክተው 32(45.7% ) ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን አልፎ አልፎ እንደሚሰሩ፣ 17(24.3% ) ተማሪዎች ደግሞ አንዳንድ ጊዜ ብልሃቱን እንደሚጠቀሙ፣ 15(21.4% ) ተማሪዎች በጭራሽ እንዳልተጠቀሙ ሲገልጹ፣ 6(8.6% )ተማሪዎች ደግሞ ሁልጊዜ እንደሚሰሩ ያመላክታል፡፡

**ተራ ቁጥር** 6 ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን ለመማር ይረዳቸው ዘንድ አካላዊ ምላሽ በመስጠት ይለማመዱ እንደሆነ ተጠይቀዋል፡፡ ከላይ በሰንጠረዡ እንደሚያመለክተው 31(44.3%) ተማሪዎች አልፎ አልፎ የአካል እንቅስቃሴ በማደረግ ሲጠቀሙ፣ 19(27.1% ) ተማሪዎች ደግሞ ብልሃቱን አንዳንድ ጊዜ እንደሚጠቀሙ ገልጸዋል፡፡ በሌላ መልኩም 11(15.7% )ተማሪዎች ብልሃቱን ሁልጊዜ እደሚጠቀሙ ሲገልጹ፣ 9(12.8%) ተማሪዎች ደግሞ ብልሃቱን በጭራሽ እንደማይጠቀሙ መረጃው ያመላክታል፡፡

ከዚህ በላይ ከተጠኚ ተማሪዎች የተገኘውን መረጃ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ “ የአማርኛ ቃላትን ከተማራችሁ በኋላ ቃላትን ለመማርና ለማስታወስ የምትጠቀሟቸው ስልቶች ምን ምን ናቸው? እንደትስ ትጠቀማላችሁ?” የሚል ቃለ መጠይቅ ለ14 ተተኳሪ ተማሪዎች ቀርቧል፡፡ ለቃለ መጠይቁም 6 ተማሪዎች ቃላትን ለመማርና ለማስታወስ ተመሳሳይና ተቃራኒ ቃላትን በማደራጀት፣ በቃል ክፍላቸው በመመደብ ፣እማሪያዊና ፍካሪያዊ ፍቺን በማደራጀትና በአካል እንቅስቃሴ በማሳየት ደስ ባላቸው ጊዜ አንዳንድ ጊዜ እንደሚጠቀሙ ምላሽ ሲሰጡ፣ ሌሎች 8 ተማሪዎች ደግሞ ምንም አይነት ስልት አንጠቀምም ነገር ግን የፈተና ጊዜ ቃላቱን እናነበዋለን በማለት መልሰ ሰጥተዋል፡፡ በመሆኑም ተጠኚ ተማሪዎች የቃላት ትምህርትን ግብ ለማሳካት አዘውትረው የተለያዩ ብልሃቶችን ያለመጠቀም ችግር እንዳለባቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ እነዚህ በትውስታ ብልሃቶች ስር የተዘረዘሩት መጠይቆች ስንመለከት ተማሪዎች እንግዳ ቃላትን ለመማርና ለማስታወስ ይቀላቸው ዘንድ በሚመቻቸው መልኩ በማቧደን፣ ተመሳሳይና ተቃራኒ ቃላትን በአንድነት በማደረጀት፣ ቃላትን ከቦታጋር በማያያዝና በድርጊት በማሳየት 177(252.9%) ጊዜ በመደጋገም እነዚህን ብልሃቶች አልፎ

አልፎ የሚጠቀሙባቸው ሲሆኑ፣ 101(145.6%) ያህልጊዜ ደግሞ ከላይ የተጠቀሱትን ብልሃቶች ደጋግመው በጭራሽ የማይጠቀሙ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ 84(119.9%) ያህል ጊዜ ብልሃቱን አንዳንድ ጊዜ በማቧደን፣ በማያያዝና በድርጊት በማሳየት በድግግሞሽ እንደሚገለገሉ ሲገልጹ፣ 57(81.4%) ጊዜ በመደጋገም ብልሃቶቹን ሁልጊዜ እንደሚገለገሉባቸው ከትንተና ውጤቱ መረዳት ተችሏል፡፡ ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች የትውስታ ብልሃት አጠቃቀማቸው ዝቅተኛ መሆኑን መረጃው ያመለክታል፡፡

በምዕራፍ ሁለት ንዑስ ርእስ 2.7.4.1.1 እንደተጠቀሰው Oxford (1990) የትውስታ ብልሃቶች ለቋንቋ ትምህርት ካላቸው ሚና አኳያ ከአንደኛ ደረጃ በላይ ያሉ ተማሪዎች ብልሃቶቹን አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ ጥናቱ ለማረጋገጥ ሞክሯል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ Wong (2005:248) እንደገለጹት የቋንቋ ተማሪዎች በተለይም የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የትውስታ አጠቃቀምን ከሌሎቹ ብልሃቶች ጋር በንጽጽር ስንመለከት ብልሃቱን ለመጠቀም ያላቸው ፍላጎት አነስተኛ መሆኑን በጥናታቸው አመልክተዋል፡፡ በዚህ ጥናትም አብዛኞቹ ተጠኚዎች የትውስታ ብልሃታቸው አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ ከትንተናው መረዳት ተችሏል፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት ከሁለቱ ምሁራን ጽንሰሀሳብ ጋር የሚደጋገፍና የሚስማማ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

### 4.1.2 የአዕምሮታዊ ብልሃቶች ትንተና

አዕምሮታዊ ብልሃቶች ተማሪው የተተኳሪውን ቋንቋ ቃላት በቀጥታ አዕምሮውን በመጠቀም ተረድቶና ከራሱም አፍልቆ በመለማመድ እንዲማር የሚያስችሉ ብልሃቶች ናቸው፡፡ Rubin (1987:23) እንደገለጹት አእምሮታዊ ብልሃቶች ተማሪዎች ታላሚውን ቋንቋ ሲማሩ በቀጥታ የሚተገብሯቸው የአሰራር መንገዶች እና የሚወስዷቸው ርምጃዎች ችግርን ማቅለያዎች ናቸው፡፡

ከተራ ቁጥር 7-17 የቀረቡት መጠይቆችን ከተጠኚዎች መረጃ የተገኘውን በርዕስ በርዕስ በመከፋፈል በሰንጠረዥ መልኩ በማደራጀት ተተንትነዋል፡

ሰንጠረዥ3:- መደጋገምን በሚጠይቁ የአዕምሮታዊ ብልሃቶች ላይ ያሳዩት አጠቃቀ

| ተ.ቁ | ብልሃቶች | የተጠኚ ተማሪዎች ምላሽ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁልጊዜ | | አንዳንድ ጊዜ | | አልፎ አልፎ | | በጭራሽ | |
| | | በቁጥር | በ % | በቁጥር | በ % | በቁጥር | በ % | ቁጥር | በ % |
| 7 | የተማርኳቸውን አዳዲስ ቃላት እርስበርሳቸው በማቀናጀት(በአዲስ መንገድ እንደገና በማቀናበር ዓረፍተነገሮችን እየመሰረትኩ እለማመዳለሁ | 7 | 10 | 12 | 17.1 | 42 | 60 | 9 | 12.9 |
| 8 | አዳዲስ ቃላቶች ሲያጋጥሙኝ ምስል ከሳች በሆነ መንገድ እየደጋገምኩ አጠናለሁ | 11 | 15.7 | 9 | 12.8 | 37 | 52.8 | 13 | 18.5 |
| 9 | አዳዲስ የአማርኛ ቃላትን ለማስታወስ ደጋግሜ እናገራቸዋለሁ ወይም እጽፋቸዋለሁ | 9 | 12.9 | 14 | 20 | 40 | 57.1 | 7 | 10 |
| 10 | በቴፕ ቀድቼ በማዳመጥና በአእምሮየ ውስጥ ደጋግሜ በማመላለስ አጠናለሁ | 12 | 17.1 | 7 | 10 | 35 | 50 | 16 | 22.8 |

**ተራ ቁጥር** 7 ተማሪዎች የተማሯቸውን አዳዲስ ቃላት በማቀናጀት እና በአዲስ መልኩ እያቀናበሩ አረፍተነገር እየመሰረቱ እንዲለማመዱ ተጠይቀው 42(60% ) ተማሪዎች አረፍተነገር በመመስረት አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ ሲገልጹ፣ 12(17.1%) ተጠኚዎች ደግሞ አንዳንድ ጊዜ እንደሚጠቀሙ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በሌላ በኩል 9(12.9%) ተጠኚዎች ብልሃቱን በጭራሽ እንደማይጠቀሙ ሲገልጹ፣ 7(10%) ተማሪዎች ደግሞ ሁልጊዜ አረፍተነገር እየመሰረቱ እንደሚገለገሉ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከተተኳሪ ተማሪዎች የተገኘውን መረጃ ትክክለኛነት ለማሳየት "የአማርኛ ቋንቋ ጽሁፎችን ስታነቡ የምታገኟቸውን አዳዲስ ቃላት ትርጉም በሚሰጡ ዓረፍተነገሮች ውስጥ በማስገባት ጭውውት፣ ንግግር ወይም ምልልስ እያደረጋችሁ ትለማመዳላችሁ?" ይህን ማድረጋችሁ ለምንድን ነው? የሚል ቃለ መጠይቅ ለ14 ተማሪዎች ቀርቦ 8 ተማሪዎች ጭውውት፣ ምልልስ የምናደርገው ለመዝናናት እንጅ ብልሃቱን ለመጠቀም ሆን ብለው ዓረፍተ ነገር እየሰሩ ልምምድ እንደማያደርጉ ሲገልጹ፣ 6 ተማሪዎች ደግሞ ከጓደኛና ከመምህራን ጋር አንዳንድ ጊዜ ንግግር፣ ጭውውት በማድረግ እንደሚለማመዱ ምላሽ

ሰጥተዋል፡፡

ከዚህ የምንረዳው ተማሪዎቹ የቃላት እውቀታቸውን ለማዳበር ከጓደኞቻቸው ጋር ጭውውት፣ንግግርና ምልልስ በማድረግ አዘውትረው ልምምድ እንደማያደርጉና ለመዝናናት ብቻ አስበው ልምምድ እንደሚያደርጉ መረጃው ያሳያል፡፡ በመሆኑም አዳዲስ ቃላትን ትርጉም በሚሰጡ ዓረፍተነገሮች እያስገቡ ልምምድ ካላደረጉ የአማርኛ ቋንቋ የቃላት እውቀታቸው ሊዳብር አይችልም፡፡

**ተራ ቁጥር** 8 አዳዲስ ቃላት ሲያጋጥማቸውምስል ከሳች በሆነ መንገድ እየደጋገሙ እንዳጠኑ ተጠይቀዋል፡፡ ከላይ በሰንጠረዥ 3 እንደሚያመለክተው 37(52.8% ) ተማሪዎች አዳዲስ ቃላት ሲያጋጥማቸው ምስል በመፍጠር እየደጋገሙ አልፎ አልፎ ሲገለገሉ፣ 13(18.5%) ተጠኚዎች ደግሞ በጭራሽ እንደማይጠቀሙ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በሌላ በኩል 11(15.7%) ተጠኚዎች ብልሃቱን ሁል ጊዜ እንደሚጠቀሙ ሲገልጹ፣ 9(12.8%) ተማሪዎች ደግሞ ብልሃቱን አንዳንድ ጊዜ እንደሚጠቀሙ ገልዋል፡፡

ከዚህ ለመረዳት እንደሚቻለው አብዛኞቹ ተማሪዎች አዳዲስ የተማሩትን ቃላት ተጨባጭ በሆኑና በአዕምሮ ውስጥ ስዕል ሊፈጥሩ የሚችሉ ብልሃቶችን አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ መርጃው ያሣያል፡፡ በመሆኑም የአብዛኞቹ ተማሪዎች የብልሃት አጠቃቀማቸው የዳበረ ሆኖ አልተገኘም፡፡

**ተራ ቁጥር** 9 አዳዲስ የአማርኛ ቃላትን ለማስታወስ ደጋግመው እንደሚናገሩና እንደሚፅፉ ጥያቄ ቀርቦላቸዋል፡፡ ከሰንጠረዡ 3 እንደሚያመለክተው 40 (57.1%) ተማሪዎች የተማሯቸውን ቃላት አልፎ አልፎ በማቀናጀት ደጋግመው እንደሚናገሩና እንደሚፅፉ ሲገልጹ፣ 14(20%) ተጠኚዎች አንዳንድ ጊዜ እንደሚለማመዱ አሳይተዋል፡፡ በአንፃሩ 9(12.9%) ተማሪዎች የተማሩትን አዳዲስ ቃላት ሁል ጊዜ እየተናገሩና እየፃፉ ሲለማመዱ፣ 7(10%) ተማሪዎች ደግሞ በጭራሽ ብልሃቱን አንጠቀምበትም በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው ተማሪዎች አዳዲስ የአማርኛ ቃላትን በማቀናጀት በመፃፍና በማለት እንዳልተለማመዱ መረጃ ያመለክታል፡፡

**ተራ ቁጥር** 10 ተማሪዎች አዳዲስ የአማርኛ ቃላትን ለማወቅ በቴፕ እየቀዱ እንዲያዳምጡ በአእምሯቸው ደጋግመው በማመላለስ እንዳጠኑ ተጠይቀዋል፡፡ ከላይ በሰንጠረዡ ለመረዳት እንደተቻለው 35(50%) ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን በቴፕ በማዳመጥና በአእምሮቸው በማመላለስ አልፎ አልፎ ሲጠቀሙ 16(22.8%) ተማሪዎች ደግሞ በጭራሽ ብልሃቱን እንደማይጠቀሙ ገልጸዋል፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ 12 (17.1%) ተማሪዎች ሁልጊዜ በቴፕ ቀድተው በማዳመጥና በአእምሯቸው በማመላለስ

ሲጠቀሙ፣ 7(10) ተማሪዎች ደግሞ አንዳንድ ጊዜ ብቻ እናዳምጣለን በማለት ገልጸዋል ፡፡

ባጠቃላይ ከዚህ በላይ በቀረበው ሰንጠረዥ ለመረዳት እንደተቻለው ተጠኚ ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ተግባራት ደጋግሞ የመስራት፣ የመለማመድ ፣ አዳዲስ ቃላትን በቀላሉ ለመያዝ ከሚታወቅ ተጨባጭ ነገር ጋር በማያያዝ ስዕል የመፍጠርና በቴፕ ቀድቶ በማዳመጥ በአዕምሮ የማመላለስ ብልሃታቸው በብቃት ላይ የተመሰረተ አይደለም፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በቃለ መጠይቁ የተገኘው መረጃም ይህንኑ ያጠነክራል፡፡

ሰንጠረዥ 4:- ምንጭን መጠቀም በሚጠይቁ ብልሃቶች ላይ ያሳዩት አጠቃቀም መረጃ ትንተና

| ተቁ | ብልሃቶች | የተጠኝ ተማሪዎች ምላሽ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁልጊዜ | | አንዳንድጊ ዜ | | አልፎ አልፎ | | .በጭራሽ | |
| | | በቁጥር | በ % | በቁጥር | በ % | በቁጥር | በ % | በቁጥር | በ % |
| 11 | ንግግር ሳዳምጥ ወይም ሳነብ ያጋጠሙኝን ቃላት ፍች ለማወቅ መዝገበ ቃላት እጠቀማለሁ | 6 | 8.5 | 15 | 21.4 | 46 | 65.7 | 3 | 4.3 |
| 12 | ፍችውን ሊነግሩኝ የሚችሉ ሰዎችን እንደ መምህራን፣ ጓደኞቼን፣ ወዘተ. እጠይቃለሁ | 23 | 32.8 | 21 | 30 | 17 | 24.3 | 9 | 12.8 |

**ተራ ቁጥር** 11 ተማሪዎች ንግግር ሲያዳምጡና የተለያዩ ጽሁፎችን ሲያነቡ ያጋጠማቸውን አዳዲስ ቃላት ለማወቅ መዝገበ ቃላት መጠቀምና አለመጠቀማቸውን ለመፈተሽ ጥያቄ ቀርቦላቸዋል፡፡ ከላይ ከሰንጠረዥ 4 እንደሚታየው 46(65.7%) ተማሪዎች የአዳዲስ ቃላትን ፍች አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ ሲያሳዩ፣ 15(21.4%) ተማሪዎች አንዳንድ ጊዜ መዝገበ ቃላት እንደሚጠቀሙ ገልጸዋል፡ ፡ በሌላ መልኩ ደግሞ 6(8.5%) ተማሪዎች ሁልጊዜ ሲጠቀሙ፣ 3(4.3%) ተማሪዎች ደግሞ በጭራሽ ብልሃቱን እንደማይጠቀሙ መርጃው ያመለክታል ፡፡

**ተራ ቁጥር** 12፡-ተማሪዎች አዳዲስ ቃላት ሲያጋጥማቸው ፍቻቸውን የሚያውቁ ሰዎችን፣ መምህራንንና ጓደኞቻቸውን እንዲጠይቁ ጥያቄ ቀርቦላቸዋል፡፡ ከሰንጠረዥ 4 ለማየት እንደተሞከረው 23(32.8%) ተማሪዎች ሁል ጊዜ ሲጠቀሙ፣ 21(30%) ተማረዎች ደግሞ አንዳንድ ጊዜ እንደሚጠቀሙ ሲገልጹ፣ 17(24.3%) ተማሪዎች አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ፣ 9(12.8%) ተማሪዎች ደግሞ ብልሃቱን በጭራሽ

እንደማይጠቀሙ ገልጸዋል፡፡

ተማሪዎች አዳዲስ የአማርኛ ቃላት ሲያጋጥማቸው መምህራንን፣ ጓደኞቻቸውን በመጠየቅ የቃላት ብልሃት አጠቃቀማቸውን ማሻሻል ይቻላል፡፡ በመሆኑም አብዛኞቹ 23(32.8%) ተማሪዎች ሁልጊዜ እንደሚጠቀሙ መረጃው ያመለክታል፡፡ ከተተኳሪ ተማሪዎች የተገኘውን መረጃ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ "የአማርኛ ቋንቋ የቃላት እውቀታችሁን ለማዳበር ጥረት አድርጋችኋል? ምላሻችሁ አዎን ከሆነ ምንምን ተግባራት አከናወናችሁ?" የሚል ለ14 ተማሪዎች ተመሳሳይ ቃለ መጠይቅ ቀርቦላቸው 8 ተማሪዎች አዎን አዳዲስ ቃላትን መምህራንን በመጠየቅ፣ ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር በቡድን በመወያየት የቃላት እውቀታቸውን ለማዳበር ጥረት እንደሚያደርጉ ሲገልጹ፣3 ተማሪዎች ደግሞ እኛ የምንፈልጋቸውን ቃላት በመምረጥ የክፍል ጓደኛን አንዳንድ ጊዜ በመጠየቅ ጥረት እንደሚያደርጉ ምላሽ ሲሰጡ፣ 2 ተማሪዎች ደግሞ ምንም አይነት ጥረት እንደማያደርጉ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከዚህ በላይ በቀረቡት የቃለመጠይቅና የጽሁፍ መጠይቅ መረጃዎች ለመረዳት እንደተቻለው ተተኳሪ ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ቃላት ሲማሩና ሲለማመዱ እንግዳ ቃላት ሲያጋጥማቸው ከመጽሐፍትና መዝገበ ቃላት ከመፈለግ ይልቅ የቃሉን ፍች የሚያውቁ ሰዎችን ጠይቀው መረዳት እንደሚችሉ ከትንተናው መረዳት ተችሏል፡፡ ይህም ተጠኚዎቹ እንግዳ ቃላት ሲያጋጥማቸው መምህራንን፣ ጓደኞቻቸውን በመጠየቅ ጥረት የሚያደርጉ ከሆነ የቃላት እውቀታቸው ይዳብራል፡፡

*ሰንጠረዥ* 5 ፡- ***መተርጎምንና ንበትን መለማመድ በሚጠይቁ ብልሃቶች ላይ ያሳዩት አጠቃቀም***

| **ተቁ** | **ብልሃቶች** | **የተጠኚ ተማሪዎች ምላሽ** | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | **ሁልጊዜ** | | **አንዳንድጊዜ** | | **አልፎ አልፎ** | | **.በጭራሽ** | |
| | | **በቁጥር** | **በ %** | **በቁጥር** | **በ %** | **በቁጥር** | **በ %** | **በቁጥር** | **በ %** |
| **13** | አዲስ ያወኩትን ቃል ወደ ኦሮምኛ ቋንቋ በመተርጎም ለምሳሌ “ነብር” የሚለውን ቃል “ቄሬንሳ” በማለት እተረጉማለሁ | 29 | 14.4 | 21 | 30 | 18 | 25.7 | 2 | 2.8 |
| **14** | በአጻጻፍ አንድ ሆነው በንበት በሚለያዩ ቃላት (ለምሳሌ፣ ጠብቀውና ላልተው በሚነበቡ) ላይ ልምምድ አደረጋለሁ | 5 | 7.1 | 16 | 22.9 | 45 | 64.3 | 4 | 5.7 |

**ተራ ቁጥር 13** ተማሪዎች አዳዲስ የአማርኛ ቃላት ሲያጋጥማቸው ወደ አፍመፍቻ ቋንቋቸው ተርጉመው እንዳውቁ ተጠይቀዋል፡፡ ከላይ ከሰንጠረዥ 5 ለመረዳት እንደተሞከረው 29(14.4%) ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን ወደ ኦሮምኛ ቋንቋ በመተርጎም ሁልጊዜ እንደሚጠቀሙ ሲገልጹ፣ 21(30%) ተማሪዎች አንዳንድጊዜ እንደሚጠቀሙ፣ 18(25.7%) ተማሪዎች ወደ ኦሮምኛ ቋንቋ በመተርጎም አልፎ አልፎ ሲጠቀሙ፣ 2(2.8%) ተማሪዎች ብልሃቱን በጭራሽ እንደማይጠቀሙ ገልጸዋል፡፡ ከዚህ ሃሳብ መረዳት እንደሚቻለው አብዛኞቹ 29(14.4%) ተማሪዎች ያጋጠማቸውን አዳዲስ የአማርኛ ቃላት ወደ አፍ መፍቻ ቋንቋቸው ተርጉመው እንደተረዱ መገንዘብ ይቻላል::

**ተራ ቁጥር 14** ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን በአፃፃፍ አንድ ሁነው በንበት በሚለያዩ ቃላት አጥብቀውና አላልተውበማንበብ ልምምድ እንዲያደርጉ ተጠይቀዋል፡፡ ከላይ በሰንጠረዥ 5 ለማየት እንደተቻለው 45(64.3%) ተማሪዎች ቃላትን በማጥበቅና በማላላት አልፎ አልፎ እንደሚያነቡ ሲገልጹ፣ 16(22.9%) ተማሪዎች ደግሞ አንዳንድ ጊዜ እንደሚጠቀሙ ገልጸዋል፡፡ በሌላ መልኩም 5(7.1%) ተማሪዎች ሁልጊዜ እንደሚጠቀሙ ሲገልጹ፣ 4(5.7%) ተማሪዎች በጭራሽ ብልሃቱን እንደማይጠቀሙ መረጃው ያመለክታል፡፡

ከላይ ከሰንጠረዡ ለመረዳት እንደተቻለው ተጠኚ ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ቃላት ሲማሩና ሲለማመዱ በተመሳሳይ ፊደል በተገነቡ ነገር ግን በንበት በሚለያዩ ቃላት በማጥበቅና በማላላት ልምምድ ከማድረግ ይልቅ ተማሪዎቹ ቃሉን ይዘው አቻ ፍች ወዳለው አፍ መፍቻ ቋንቋ በመተርጎም እንደሚለማመዱ ከትንተና ውጤቱ መረዳት ተችሏል።

**ሰንጠረዥ 6 ፡- ማስታወሻ መውሰድን፣ ትኩረት ቃል ድምቅታንና ተፈጥሮአዊ ልምምድን የሚጠይቁ ብልሃቶች ላይ ያሳዩት አጠቃቀም**

| ተ.ቁ. | ብልሃቶች | የተጠኝ ተማሪዎች ምላሽ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁልጊዜ | | አንዳንድጊዜ | | አልፎ አልፎ | | በጭራሽ | |
| | | በቁጥር | በ % | በቁጥር | በ % | በቁጥር | በ % | በቁጥር | በ % |
| 15 | አዳዲስና ለእኔ ጠቃሚ ናችው ብየ የምገምታቸውን ቃላት በልዩ ማስታወሻ ደብተሬ አደራጅቼ እይዛለሁ | 7 | 10 | 18 | 25.7 | 44 | 62.8 | 1 | 1.4 |
| 16 | መጽሀፍትን፣ ጋዜጦችን ወጎችንና መጽሔቶችን በማነብበት ጊዜ የሚያጋጥሙኝን እንግዳ ወይም አዳዲስ ቃላትን ከስራቸው በማስመርና ምልክት በማድረግ ካለፍኩ በሁዋላ በመጨረሻ ፍቻቸውን እፈልጋለሁ | 3 | 4.3 | 12 | 17.1 | 49 | 70 | 6 | 8.5 |
| 17 | የቃላት እውቀቴን ለማዳበር በሚል አላማ የራዲዮ፣ የቴሌቪዥን ፕሮግራም እከታተላለሁ | 6 | 8.5 | 10 | 14.3 | 52 | 74.3 | 2 | 2.8 |

**ተራ ቁጥር 15** ተማሪዎች አዳዲስና ጠቃሚ ናቸው ብለው የሚገምቷቸውን ቃላት ማስታዎሻ መያዝና አለማያዛቸውን ለመፈተሽ ተጠይቀዋል። ከላይ በሰንጠረዥ 6 ለማየት እንደተቻለው 44(62.8%) ተማሪዋች አልፎ አልፎ ማስታወሻ እንደሚይዙ ሲገልጹ፣ 18(25.7%) ተማሪዎች ጠቃሚ ናቸው ብለው ያሰቧቸውን ቃላት አንዳንድ ጊዜ ማስታወሻ እንዲይዙ ገልጸዋል። በአንፃሩ 7(10%) ተማሪዎች ሁልጊዜ ማስታወሻ እንደሚይዙ ሲገልጹ፣ 1(1.4%) ተማሪዎች በጭራሽ እንደማይጠቀሙ ገልጸዋል።

**ተራ ቁጥር 16** ተማሪዎች የተለያዩ መፅሃፎችን በሚያነቡበት ወቅት የሚያጋጥማቸውን አዳዲስ ቃላት ከስራቸው በማስመር ወይም ምልክት በማድረግ ፍቻቸውን የመፈለግ ብልሃት አጠቃቀማቸውን የሚመለከት መረጃ ለማገኘት ጥያቄ ቀርቦላቸዋል፡፡ ከላይ በሰንጠረዥ 6 ለማየት እንደተቻለው 49(70%) ተማሪዎች ሲያነቡ የሚያጋጥሟቸውን ቃላት በማስመር አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ ምላሽ ሲሰጡ፣ 12(17.1%) ተማረዎች አንዳንድ ጊዜ እንደሚጠቀሙ፣ 6(8.5%) ተማሪዎች ብልሃቱን በጭራሽ እንደማይጠቀሙ፣ 3(4.3%) ተማሪዎች ደግሞ ፅሁፎችን ሲያነቡ በማስመር ወይም ምልክት በማድረግ ሁልጊዜ እንደሚጠቀሙ መረጃው ያመለክታል፡፡

የተለያዩ ፅሁፎችን ማለትም መፅሃፍትን፣ ጋዜጦችን፣ መፅሄቶችን በሚያነቡብት ጊዜ ያጋጠማቸውን አዳዲስ ቃላት የሚያሰምሩ እና ምልክቶችን የሚጠቀሙ ከሆነ የቃላት ብልሃት አጠቃቀማቸው እንዲሻሻል ያግዛቸዋል፡፡ ነገር ግን አብዛኞቹ 49(70%) ተማሪዎች ብልሃቱን የሚጠቀሙት አልፎ አልፎ እንደሆነ ከጥናቱ ውጤት መረዳት ተችሏል፡፡

ከተተኳሪ ተማሪዎች የተገኘውን መረጃ ትክክለኛነት ለማሳየት “የአማርኛ ቃላት እውቀታችሁን ለማዳበር ከመማሪያ ክፍል ውጭ ምን ምን ጽሁፎችን ታነባላችሁ? የምታነቡት አንዳንድ ጊዜ ወይስ ሁልጊዜ? ለምን?” የሚል ለ14 ተማሪዎች ቃለ መጠይቅ ቀርቦላቸው 9 ተማሪዎች ግጥም፣ መጽሔቶችን ድብርትን ለማስወገዲና ለመዝናናት አንዳንድ ጊዜ እንደሚያነቡ ሲገልጹ፣ 5 ተማሪዎች ደግሞ ከመማሪያ ክፍል ውጭ ምንም አይነት መጽሐፍ እንደማያነቡና ተንተባትበው ሲያነቡ ሰዎችን ስለሚፈሩ ምንም ጽሁፎን እንደማያነቡ ገልጸዋል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች የአማርኛ ቃላት እውቀታቸውን ለማሳደግ በሚል አላማ ሳይሆን ድብርታቸውን ለማስወገድ የተለያዩ መጽሃፍቶችን፣ልቦለዶችን፣ ግጥሞችን የሚያነቡት አዘውትረው ሳይሆን አንዳንድ ጊዜ መዝናናትን ብቻ በማሰብ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ደግሞ የቃላት እውቀታቸው ሊዳብር እንደማይችል ይታሰባል፡፡

**ተራ ቁጥር 17** ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን ለማወቅ በሚል አላማ የራዲዮ፣ የተሌቪዥን ፕሮግራሞችን በመከታተል ብልሃታቸውን ለመፈተሽ ጥያቄ ቀርቦላችዋል፡፡ ከላይ በሰንጠረዥ 6 ለማየት እንደተቻለው 52(74.3%) ተማሪዎች ራዲዮና ቴሌቪዥን በመከታተል አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ ምላሽ ሲሰጡ፣ 10(14.3%) ተማሪዎች ደግሞ አንዳንድ ጊዜ እንደሚጠቀሙ

ገልጸዋል፡፡ በሌላ መልኩ 6(8.5%)ተማሪዎች ሁል ጊዜ እንደሚከታተሉ ሲገልጹ፣ 2(2.8%) ተማሪዎች ደግሞ ብልሃቱን በጭራሽ እንደማይጠቀሙ መረጃው ያመለክታል፡፡ ከተተኳሪዎቹ የተገኘውን የጽሁፍ መጠይቅ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ለ14 ተማሪዎች ተያያዥነት ያላቸው ቃለ መጠይቅ ቀርበው 11ተማሪዎች ራዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣ፊልሞችን፣ድራማዎችን ለመዝናናት አንዳንድ ቀን እንደሚከታተሉ ምላሽ ሲሰጡ፣ 3 ተማሪዎች በጭራሽ እንደማይከታተሉ ከሰጡት መልስ መረዳት ተችሏል፡፡

ጠቅለል ባለመልኩ ሲታይ ተጠኚ ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ቃላት ሲማሩና ሲለማመዱ አዳዲስ ወይም አንግዳ ቃላት ሲያጋጥማቸው ወደ አፍመፍቻ ቋንቋቸው እንደሚተረጉሙ፣ የተለያዩ ምንጮችን እንደሚጠቀሙ፣ ማስታወሻ እንደሚይዙ፣ንበትን እንደሚለማመዱ፣ ቃላትን በማስመር፣ በማቅለምና ተፈጥሮዊ ልምምድን የሚሹ አዕምሮታዊ ብልሃቶችን እንደሚጠቀሙ ተጠይቀው 425(607%) ያህል ጊዜ በመደጋገም እነዚህን ብልሃቶች አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙበት ሲገልጹ፣155(221.3%) ጊዜ ደግሞ አንዳንድ ጊዜ ደጋግመው እንደሚገለገሉባቸው ገልጸዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ 118(141.3% ) ያህል ጊዜ ሁልጊዜ አዳዲስ ቃላት ሲያገኙ ብልሃቶቹን በተደጋጋሚ እንደሚጠቀሙ ሲገልጹ፣ 72(102.5%) ያህልጊዜ ደጋግመው ብልሃቶቹን በጭራሽ እንደማይገለገሉበት ከትንተና ውጤቱ መረዳት ተችሏል ፡፡ በተመሳሳይ መልኩም በቃለመጠይቁ የተሰበሰበው መረጃ ብልሃቶቹን ያዳበሩ አለመሆናቸውን ያሳያል፡፡ ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች የአዕምሯዊ ብልሃት አጠቃቀማቸው ዝቅተኛ መሆኑን መረጃው ያመለክታል፡፡

### 4.1.3 የአካካሽ ብልሃቶች ትንተና

እነዚህ ብልሃቶች ተማሪዎች በቃላት እውቀት ማነስ ምክንያት በተግባቦትሂደት የሚያጋጥማቸውን ችግር ለመቋቋም የሚጠቀሙባቸው ብልሃቶች ናቸው፡፡

**ሰንጠረዥ 7 :- የአካካሽ ብልሃቶች ጥቅል ትንተና**

| ተቁ | ብልሃቶች | የተጠኚ ተማሪዎች ምላሽ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁልጊዜ | | አንዳንድ ጊዜ | | አልፎ አልፎ | | .በጭራሽ | |
| | | በቁጥር | በ % | በቁጥር | በ % | በቁጥር | በ % | በቁጥር | በ % |
| 18 | አዳዲስ ቃላት ፍቺ ለመረዳት የህይወት ልምዴን ወይም አጠቃላይ እውቀትን በመጠቃቀም የቃላትን ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ በመፈለግና የቃል ክፍሉን በመመልከት ከአገባባቸው እገምታለሁ | 35 | 50 % | 18 | 25.7 % | 6 | 8.5 % | 11 | 15.7 % |
| 19 | መጽሀፍ ጋዜጣ ሳነብ የሚያጋጥሙኝን አዳዲስ ቃላት ከአገባባቸው ለመገመት እሞክራለሁ | 38 | 54. 3% | 20 | 28.5 % | 9 | 12.8 % | 3 | 4.3 % |
| 20 | የፊት ለፊት ንግግር ሳዳምጥ አዳዲስ ቃላት ሲያጋጥሙኝ ፍቻቸውን ከተናጋሪው የአካል እንቅስቃሴ (ለምሳሌ ጥቅሻ፣ ፈገግታ፣ መኮሳተር፣ እጅ ማወራጨት ) ለመገመት እሞክራለሁ | 28 | 40 % | 24 | 34.3 | 13 | 18.5 % | 5 | 7.1 % |

**ተራቁጥር** 18 ተማሪዎች የተለያዩ ጽሁፎችን በሚያነቡበት ወቅት ያጋጠማቸውን አዳዲስ ቃላት ለማወቅ ከህይወት ልምዳቸው ወይም ከአጠቃላይ እውቀት በመጠቀም ከአገባባቸው ፍቻቸውን እንዲገምቱ ጥያቂ ቀርቦላቸዋል፡፡ ከላይ ከሰንጠረዥ 7 እንደሚያመለክተው 35(50%)ተማሪዎች በንባብ ሂደት ያጋጠማቸውን አዳዲስ ቃላት ከአገባባቸው ፍቻቸውን እንዲገምቱ ሁልጊዜ እንደሚጠቀሙ ሲገልጹ፣ 18(25.7% )ተማሪዎች ደግሞ አንዳንድ ጊዜ እንደሚጠቀሙ፣ 11(15.7%) ተማሪዎች ብልሃቱን በጭራሽ እንደማይጠቀሙ ምላሽ ሲሰጡ፣ 6(8.5% )ተማሪዎች ደግሞ አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ መረጃው ያመላክታል፡፡

**ተራቁጥር**19 መጽሐፍ፣ ጋዜጣ ስታነቡ አዳዲስ ቃላትን ከአገባባቸው ለመገመት ትሞክራላችሁ የሚል ጥያቄ ተጠይቀው 38(54.3% ) ተማሪዎች ሁልጊዜ ከአገባባቸው ፍቻቸውን ሲገልጹ፣

20(28.5% ) ተጠኚዎች መጽሐፍትና ጋዜጣን ሲያነቡ ከአገባባቸው ፍቻቸውን አንዳንድ ጊዜ የሚጠቀሙ ናቸው። በሌላ መልኩም 9(12.8%)ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን ከአገባባቸው አልፎአልፎ እንደሚገለገሉ ምላሽ ሲሰጡ፣ 3(4.3 %)ተጠኚዎች ደግሞ ብልሃቱን በጭራሽ የማይጠቀሙ መሆናቸውን መረጃው ያመለክታል። ከተተኳሪ ተማሪዎች የተገኘውን መረጃ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ " የተለያዩ ጽሁፎችን፣ የሰዎችን ንግግር ስታዳምጡ ፍቻቸውን የማታውቋቸውን አዳዲስ ቃላት ስታገኙ ምን አይነት ዘዴ ትጠቀማላችሁ? ሁልጊዜ ወይስ አንዳንድጊዜ የምትጠቀሙት?" የሚል ለ14 ተማሪዎች ቃለ መጠይቅ ቀርቦላቸው 10 ተማሪዎች አዳዲስ ቃላቶችን በመለየት ሁልጊዜ ከአገባባቸው እንደሚገምቱ ሲገልጹ፣ 4 ተማሪዎች ደግሞ የማያውቁትን ቃላት አንዳንድ ጊዜ ከአገባባቸው ፍቹን እንደሚፈልጉ መልስ ሰጥተዋል።

ከዚህ በላይ በጽሁፍ መጠይቅና በቃለ መጠይቅ አማካኝነት በተገኘው መረጃ ተጠኚ ተማሪዎች ከሰዎች ንግግር በሚያዳምጡበት ወቅት አዳዲስ ቃላት ሲያጋጥማቸው ዘወትር ከአገባባቸው በመገመት ፍቻቸውን እንደሚረዱ መረጀው አመላክቷል።

**ተራ ቁጥር 20** ተጠኚዎች የፊትለፊት ንግግር ሲያዳምጡና አዳዲስ ቃላት ሲያጋጥማቸው ከሰዎች የአካል እንቅስቃሴን በማየት ብልሃቱን እንደሚገምቱ ጥያቄ ቀርቦላቸዋል። ከላይ ከሰንጠረዥ 7 ለማየት እንደሚቻለው 28(40% ) ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን ለማወቅ ከአካል እንቅስቃሴ በመገመት ሁልጊዜ ሲጠቀሙ፣ 24(34.3% )ተማሪዎች የቃሉን ፍች በአካል እንቅስቃሴ አንዳንድ ጊዜ እንደሚገምቱ ገልጸዋል። በሌላ በኩል ደግሞ 13(18.5% ) ተጠኚዎች ብልሃቱን አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ ሲገልጹ፣ 5(7.1% )ተማሪዎች በጭራሽ ብልሃቱን እንደማይጠቀሙ መረጃው ያመላክታል።

በአጠቃላይ ከ18-20 በቀረቡት የጽሁፍ መጠይቆች ተጠኚ ተማሪዎች ያጋጠማቸውን አዳዲስ ቃላት ፍች ለመረዳት ከአገባባቸው በመመርመር ፍቻቸውን የመገመት ብልሃትን አብዛኞቹ ተማሪዎች እንደሚጠቀሙበት መረጃው ያመለክታል። Oxford (1990፣ 47) እንዳስረዱት አካካሽ ብልሃቶች የቃላት እውቀት ክምችት እጦትን ለማካካስ የሚረዱ ብልሃቶች ናቸው። ለቃላት ትምህርት የበለጠ ተገቢነት ያለው አካካሽ ብልሃት የአዳዲስ ቃላትን ፍች ከአውድ የመገመት ብልሃት ነው። እነዚህ ብልሃቶች ተማሪው ሁለት የተለያዩ ፍንጮችን ወይም

መረጃዎችን ማለትም ስነልሳናዊና ኢ-ስነልሳናዊ ፍንጮችን በመጠቀም የአዳዲስ ቃላትን ትርጉም ለመገመት የሚረዱ ናቸው፡፡

## 4.2. ኢ-ቀጥተኛ የመማር ብልሃቶች መረጃ ትንተና

### 4.2.1 የልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶች ትንተና

ልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶች ተማሪው የትምህርቱን አካሄድና አሰራሩን ለመቆጣጠር፣ በአጠቃላይ ያሳየውን ለውጥና የትምህርቱን ውጤት ለመገምገም የሚጠቀምባቸው ብልሃቶች ናቸው Oxford (1990)::

ከዚህ በታች ከተራ ቁጥር 21-24 ያሉት የጽሁፍ መጠይቆች የልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶች መረጃ ትንተናን የሚመለከቱ ናቸው፡፡

**ሰንጠረዥ 8** :- ልዕለ አዕምሮታዊ መረጃ ትንተና

| ተቁ | ብልሃቶች | የተጠኚተማሪዎች ምላሽ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁልጊዜ | | አንዳንድ ጊዜ | | አልፎ አልፎ | | በጭራሽ | |
| | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 21 | የቃላት እውቀቴን ለማሳደግ የአማርኛ ቃላትን ትኩረት ሰጥቼ በዓላማ ለመማር እንድሁም ለመለማመድ እቅድ አዘጋጃለሁ | 7 | 10 % | 11 | 15.7 % | 29 | 41.4 % | 23 | 32.8 % |
| 22 | የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን የምማርበትን (ከቃላት ትምህርቱ የምጠብቀውን) የራሴን አላማና ግብ አዘጋጃለሁ | 4 | 5.7 % | 8 | 11.4 % | 31 | 44.3 % | 27 | 38.6 % |
| 23 | የአዳዲስ ቃላትን ፍች ለመረዳት የተከተልኩት መንገድ ትክክለኛ ወይም የተሳሳተ መሆኑን በማረጋገጥ ስህተቴን በራሴ እለያለሁ | 2 | 2.8 % | 14 | 20% | 35 | 50 % | 19 | 27.1 % |
| 24 | በቃላት ትምህርት ጊዜ በየወቅቱ ማሻሻል አለማሻሻሌን ለማረጋገጥ ራሴን እገመግማለሁ | 6 | 8.5 % | 11 | 15.7 % | 27 | 38.6 % | 26 | 37.1 % |

**ተራ ቁጥር 21** ተጠኚዎች የቃላት እውቀታቸውን ለማሳደግ የአማርኛ ቃላትን ትኩረት ሰጥተው በአላማ ለመማርና ለመለማመድ እቅድ እንደሚያዘጋጁ ተጠይቀው 29(41.4% )ተማሪዎች የቃላት እውቀታቸውን ለማሳደግ በአላማ ለመማርና ለመለማመድ አልፎ አልፎ

እቅድ እንደሚያዘጋጁ ምላሽ ሲሰጡ፣ 23(32.8%) ተጠኚዎች ደግሞ የቃላት እውቀታቸውን ለማሳደግ በጭራሽ እንደማይጠቀሙ ገልጸዋል፡፡ በሌላ መልኩም 11(15.7%) ተማሪዎች አንዳንድ ጊዜ እንደሚጠቀሙ ሲገልጹ፣ 7(10%) ተማሪዎች ደግሞ ሁልጊዜ እቅድ በማውጣት እንጠቀማለን በማለት  ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከተተኳሪ ተማሪዎች የተገኘውን መረጃ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ" የቃላት እውቀታችሁን ለማዳበር አዳዲስ ቃላትን የምታጠኑበት ፕሮግራም አውጥታችኋል? የምታጠኑት በየዕለቱ ነው ወይስ በየሳምንቱ?" የሚል ለ14 ተጠኚ ተማሪዎች ተመሳሳይ ቃለ መጠይቅ ቀርቦላቸው 9 ተማሪዎች ለቃላት ትምህርት ምንም አይነት ፕሮግራም እንደማያወጡ ምላሽ ሲሰጡ፣ 5 ተማሪዎች ደግሞ ለፈተና ቀን ብቻ እንደሚያጠኑ መልስ ሰጥተዋል፡፡

**ተራ ቁጥር** 22.ተተኳሪ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን ሲማሩ ከቃላት ትምህርት የሚጠብቁትን  የራሳቸውን አላማና ግብ አንዳዘጋጁ ተጠይቀው 31(44.3%) ተጠኚዎች ከቃላት ትምህርት የሚጠብቁትን ውጤት አልፎ አልፎ አላማና ግብ እንደሚያዘጋጁ ምላሽ ሲሰጡ፣ 27(38.6%) ተማሪዎች ደግሞ ለቃላት ትምህርት በጭራሽ ብልሃቱን እንደማይጠቀሙ መረጃው ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩልም 8(11.4% )ተጠኚዎች አንዳንድ ጊዜ እንደሚጠቀሙ ሲገልጹ፣ 4(5.7%)ተማሪዎች ደግሞ ሁልጊዜ ብልሃቱን እንደሚጠቀሙ መረጃው ያመለክታል፡፡

**ተራ ቁጥር** 23.ተጠኚ ተማሪዎች ቃላትን ለመረዳት የተከተሉት መንገድ ትክክለኛ ወይም የተሳሳተ መሆኑን ለማረጋገጥ ስህተታቸውን በራሳቸው እንዲለዩ ተጠይቀው 35(50%)ተጠኚዎች የአዳዲስ ቃላትን ፍች ለመረዳት የተከተሉት መንገድ ትክክለኛ ወይም ስህተት መሆናቸውን አልፎ አልፎ እንደሚያረጋግጡ ምላሽ ሲሰጡ፣ 19(27.1%)ተማሪዎች በጭራሽ ብልሃቱን እንደሚጠቀሙ ገልጸዋል፡፡ በሌላ በኩል 14(20%) ተማሪዎች አንዳንድ ጊዜ ራሳቸውን እንዲቆጣጠሩ ሲገልጹ፣ 2(2.8%) ደግሞ ሁልጊዜ ብልሃቱን እንደሚጠቀሙ ገልጸዋል፡፡

**ተራ ቁጥር** 24 ተማሪዎች የቃላት ትምህርት በሚማሩበት ጊዜ አዳዲስ ቃላትን ለማወቅ መሻሻል አለማሻሻላቸውን ለማረጋገጥ ራሳቸው እንዲገመግሙ ተጠይቀው 27(38.6%) ተጠኚዎች ለአዳዲስ ቃላት እውቀት መሻሻልና አለመሻሻላቸውን አልፎ አልፎ ራሳቸውን ሲገመግሙ ፣26(37.1%) ተማሪዎች ደግሞ በጭራሽ እንደማይገመግሙ ገልጸዋል፡፡ በአንጻሩ

11(15.7%) ተጠኚዎች አንዳንድ ጊዜ ብልሃቱን ሲጠቀሙ ፣6(8.5%) ተማሪዎች ደግሞ ሁልጊዜ ብልሃቱን እንደሚጠቀሙ ገልጸዋል።

ከተተኳሪ ተማሪዎች የተገኘውን መረጃ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ከጽሁፍ መጠይቁ ጋር ተያያዥነት ያለው ለ14 ተጠኚዎች ቃለ መጠይቅ ቀርቦላቸው 8 ተማሪዎች በፈተናም ይሁን በተግባቦት ሂደት የቃላት እውቀታቸውን መሻሻል አለመሻሻሉን እንዳልገመገሙ ሲገልጹ፣ 6 ተማሪዎች ደግሞ በክፍል ፈተና፣ ከተማሪዎች ጋር ከፍተኛተግባቦት ሲፈጥሩ የቃላት እውቀታቸው መሻሻሉንና አለመሻሻሉን እንደገመገሙ ገልጸዋል።

በከዚህ በላይ በቀረቡት የጽሁፍ መጠይቆች ለመረዳት እንደተቻለው ተማሪዎች የልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶችን ማለትም እቅድ የማውጣት፣ አላማና ግብ የመጣል፣ራስን የመቆጣጠርና ራስን የመገምገም ብልሃቶችን በተደጋጋሚ እንደሚጠቀሙባቸው ተጠይቀው 122(174.3%)ያህል ጊዜ እነዚህን ስልቶች በመደጋገም አልፎአልፎ እንደሚጠቀሙ ሲገልጹ፣ 95(135.6%) ጊዜ ደጋግመው ብልሃቶችን በጭራሽ እንደማይገለገሉ ምላሽ ሰጥተዋል። በሌላ በኩል ደግሞ 44(62.8%) ያህልጊዜ ደጋግመው ብልሃቶቹን አንዳንድ ጊዜ እንደሚጠቀሙ ሲገልጹ፣ 19(27%) ጊዜ ደግሞ ሁልጊዜ ብልሃቶቹን በመደጋገም እንደሚጠቀሙበት ከመረጃው መረዳት ተችሏል። በቃለመጠይቁም የተሰበሰበው መረጃ ይህንኑ ያጠናክራል። ስለዚህ ተጠኚ ተማሪዎች በልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃት ስር የቀረቡትን ብልሃቶች በብቃት እንዳልተጠቀሟቸው ከትንተናው መረዳት ተችሏል።

በምዕራፍ ሁለት በክለሳ ድርሳናት ለመግለጽ እንደተሞከረው ልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶቸ ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን በቀላሉ ለመማር ተገቢ የሆኑ የቃላት መማር ብልሃቶችን መምረጥ እንዲችሉ ያግዛቸዋል። ስለዚህ እነዚህ ብልሃቶች ተማሪዎች የቀረጹትን አላማ ለማሳካት፣ የተጠቀሙባቸውን ብልሃቶች ውጤታማነት በመገምገም የወደፊት የመማር አቅጣጫቸውን የሚወስኑበት በመሆኑ በተገቢው ሁኔታ እንዲጠቀሙበት ማስቻል ተገቢ ነው (Oxford 1990, Schmitt 2000)::

### 4.2.2 የስሜት ነክ ቁጥጥር መረጃ ትንተና

በምዕራፍ ሁለት በክለሳ ድርሳናት ስር ለመግለጽ እንደተሞከረው ስሜት ነክ ቁጥጥር ብልሃት ተማሪው በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት የሚያድርበትን የፍርሃትና የጭንቀት ስሜት እንድሁም አሉታዊ ዝንባሌ ለመቋቋም (ለመቆጣጠር) የሚጠቀሟቸው ብልሃቶች ናቸው። እንደ Oxford

(1990፣141) ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች የሁለተኛ ቋንቋ ቃላትን በሚማሩበት ወቅት የሚያጋጥማቸውን የስሜትና የመነቃቃት ችግር በብቃት ይቋቋማሉ፡፡ በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጭ ከቋንቋው ተናጋሪዎች ጋር በሚፈጥሩት ግንኙነት የቋንቋው እውቀት ማነስና ለህብረተሰቡ ባህል አዲስ መሆን በመማር ፍላጎት በንቃት የመሳተፍ ስሜት ላይ በተወሰነ ደረጃ ጫናና የስሜት መረበሽ ማሳደራቸው የማይቀር ቢሆንም ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች በውስጣቸው የተፈጠረውን የመረበሽ ስሜት ለመቋቋም ይጥራሉ፡፡

**ሰንጠረዥ 9 ፡-የስሜት ነክ ቁጥጥር ብልሃቶች ትንተና**

| ተቁ | ብልሃቶች | የተጠኚ ተማሪዎች ምላሽ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁልጊዜ | | አንዳንድ ጊዜ | | አልፎ አልፎ | | በጭራሽ | |
| | | በቁጥር | በ % | በቁጥር | በ % | በቁጥር | በ % | በቁጥር | በ % |
| 25 | የቃላት ትምህርት ወይም ጥናት ከመጀመሬ በፊት አወንታዊ በሆነ መንገድ (ለምሳሌ ቀልድ ፈጥሬ ሊሆን ይችላል) አካልና አእምሮየን አዝናናለሁ | 8 | 11.4 % | 13 | 18.5 % | 41 | 58.5 % | 8 | 11.4 % |
| 26 | የቃላትን መልመጃዎች ከመስራቴ በፊት በተለያየ ዘዴ ራሴንአዝናናለሁ | 14 | 20% | 18 | 25.7 % | 34 | 48.5 | 4 | 5.7 % |
| 27 | በቃላት ትምህርት ውጤታማ ስሆን ለምሳሌ የቃላት እውቀቴ መሻሻሉን ሳውቅ፣ወይም በቃላት ፈተና የተሻለ ውጤት ሳመጣ እራሴ በራሴ አደንቃለሁ | 12 | 17.4 % | 22 | 31.4 % | 33 | 47.1 % | 3 | 4.3 % |
| 28 | የቃላት ትምህርት ስማር ለአዳዲስ ቃላት የምሰጣቸው ፍችዎች ትክክል ላይሆኑ ቢችሉም በትምህርት ሂደት መሳሳት ያለ በመሆኑ ያለምንም ፍርሃት ሙከራየን እቀጥላለሁ | 4 | 5.7 % | 25 | 35.7 % | 36 | 51.4 % | 5 | 7.1 % |

**ተራቁጥር 25.** የቃላት ትምህርት ወይም ጥናት ከመጀመራቸው በፊት አወንታዊ በሆነ መንገድ ቀልድ ፈጥረው አካልና አዕምሯቸውን እንዲያዝናኑ ተጠይቀው 41(58.5%) ተማሪዎች የተለያዩ ቀልዶችን ፈጥረው አልፎ አልፎ እንደሚዝናኑ ምላሽ ሲሰጡ፣ 13(18.5%) ተማሪዎች ደግሞ አንዳንድ ጊዜ ቀልዶችን ፈጥረው ይዝናናሉ፡፡ በሌላ በኩል 8(11.4%) ተማሪዎች ሁልጊዜ እየተዝናኑ ሲማሩ፣ 8(11.4%) ተማሪዎች ደግሞ በጭራሽ ብልሃቱን እንደማይጠቀሙ ከሰንጠረዥ5 መረዳት ተችሏል፡፡

**ተራ ቁጥር 26** ተጠኚ ተማሪዎች የቃላት መልመጃ ከመስራታቸው በፊት በተለያየ ዘዴ ራሳቸውን እንዳዝናኑ ተጠይቀዋል፡፡ ከሰንጠረዥ 9 ለመረዳት እንደተቻለው 34(48.5%) ተጠኚዎች ራሳቸውን የተለያየ ዘዴ ፈጥረው አልፎ አልፎ እንደሚዝናኑ ሲገልጹ፣ 18(25.7%) ተማሪዎች ደግሞ አንዳንድ ጊዜ እንደሚዝናኑ ገልጸዋል፡፡ በሌላ በኩልም 14(20%) ተማሪዎች ሁልጊዜ እየተዝናኑ መልመጃዎችን እንደሚሰሩ ምላሽ ሲሰጡ፣ 4(5.7%) ተማሪዎች ደግሞ በጭራሽ እንደማይዝናኑ መረጃው ያመለክታል፡፡

**ተራ ቁጥር 27.** ተማሪዎች በቃላት ትምህርት ውጤታማ ሲሆኑና የተሻለ ውጤት ሲያመጡ ራሳቸውን እንደሚያደንቁና እንደማያደንቁ ለመፈተሽ ተጠይቀው 33(47.1% ) ተማሪዎች በቃላት ትምህርት ውጤታማ ሲሆኑ አልፎ አልፎ ራሳቸውን እንደሚያደንቁ፣ 22(31.4%)ተማሪዎች ደግሞ አንዳንድ ጊዜ እንደሚያደንቁ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በሌላ መልኩ 12(17.4% )ተጠኚዎች ሁልጊዜ እየተዝናኑ እንደሚማሩ ሲገልጹ፣ 3(4.3%) ተማሪዎች ደግሞ በጭራሽ ብልሃቱን እንደማይጠቀሙ ገልጸዋል ፡፡ ከተተኳሪ ተማሪዎች የተገኘውን መረጃ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ከጽሁፍ መጠይቁ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ለ14 ተጠኚዎች ቃለ መጠይቅ ቀርቦላቸው 5 ተማሪዎች "አዎን" በቃላት ፈተና ጊዜ ጥሩ ውጤት ሲያመጡ ራሳቸውን በመሸለምና በማበረታታት እንደሚያደንቁ ምላሽ ሲሰጡ፣ 3 ተማሪዎች ደግሞ አናደንቅም ግን ውስጣችንን ደስ ይለናል፣ 6 ተማሪዎች ደግሞ ምንም አይነት ተሳትፎ ስለማያደርጉ ራሳቸውን እንደማያደንቁ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

**ተራ ቁጥር 28** ተጠኚ ተማሪዎች የቃላት ትምህርት ሲማሩ ለአዳዲስ ቃላት የሚሰጧቸው ፍችዎች ትክክል ሳይሆኑ ሲቀሩ ያለምንም ፍርሃት ሙከራቸውን እንደሚቀጥሉ ተጠይቀዋል፡፡ ከሰንጠረዥ 9 እንደሚያመለክተው 36(51.4%) ተማሪዎች አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ ሲገልጹ፣ 25(35.7%)ተማሪዎች አንዳንድ ጊዜ እንደሚጠቀሙ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በሌላ

መልኩ ደግሞ 5(7.1%) ተማሪዎች በጭራሽ እንደማይጠቀሙ ሲገልጹ፣ 4(5.7%) ተማሪዎች ደግሞ ሁል ጊዜ እንደሚጠቀሙ ገልጸዋል፡፡

ከላይ በተራቁጥር 25 -28 የቀረቡት መጠይቆች ስሜት ነክ ቁጥጥር ብልሃቶችን አስመልክተው ለተማሪዎች ቀርበው በተገኘው መረጃ መሰረት እንደሚያመለክተው ተተኳሪ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን ሲማሩ የሚጠቀሟቸው ብልሃቶች አነስተኛ እንደሆነ መረጃው ያመለክታል፡፡

### 4.2.3 የማህበራዊ ብልሃቶች መረጃ ትንተና

በምእራፍ ሁለት እንደተገለጸው ማህበራዊ ብልሃት ተማረዎች ቃላትን ሲማሩ ከአካባቢውና አብረው ከሚኖሩት ማህበረሰብ ጋር ለመገናኘት፣ በመግባባት በመተባበርና በመስራት፣ ተጨማሪ ማብራሪያዎችን በመጠየቅና እራሳቸውን በራሳቸው በማበረታታት ቋንቋውን የሚማሩበት ብልሃት ነው፡፡

**ሰንጠረዥ 10 :-** የማህበራዊ ብልሃቶች ጥቅል መረጃ ትንተና

| ተ ቁ | ብልሃቶች | የተጠኚ ተማሪዎች ምላሽ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁልጊዜ | | አንዳንድ ጊዜ | | አልፎ አልፎ | | በጭራሽ | |
| | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 29 | የቃላት ችሎታየን ለማሻሻል ከክፍል ጓደኞቼ ጋር በመሆን በቡድን እወያያለሁ | 14 | 20% | 28 | 40 % | 24 | 34.3 % | 4 | 5.7 % |
| 30 | ስለ አማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ባህልና የአኗኗር ስርዓት ለማወቅ የቴሌቪዥን፣ ሬዲዮ ፕሮግራም እከታተላለሁ | 7 | 10% | 18 | 25. 7% | 37 | 52.8 | 8 | 11. 4% |

**ተራ ቁጥር** 29 ተጠኚ ተማሪዎች የአማርኛ ቃላት ችሎታቸውን ለማሻሻል ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር በቡድን እንደሚወያዩ ጥያቄ ቀርቦላቸው28(40%) ተማሪዎች አንዳንድ ጊዜ ከጓደኞቻቸው

ጋር እየተወያዩ እንደሚሰሩ ሲገልጹ፣ 24(34.3%) ተጠኚዎች ደግሞ የቃላት ትምህርታቸውን ለማሻሻል አልፎ አልፎ በቡድን እንደሚማሩ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ 14(20%) ተማሪዎች ሁል ጊዜ እየተወያዩ እንደሚማሩ ሲገልጹ፣ 4(5.7%) ተማሪዎች በጭራሽ እንደማይወያዩ ገልጸዋል፡፡

**ተራ ቁጥር 30** ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ባህል እና የአኗኗር ስርዓት ለማወቅ ቴሌቪዥን፣ ራዲዮ ፕሮግራሞችን እንደሚከታተሉ ተጠይቀው37(52.8%) ተማሪዎች ቴሌቪዥን፣ራዲዮ አልፎ አልፎ እንደሚከታተሉ ሲገልጹ፣ 18(25.7%) ተማሪዎች ደግሞ አንዳንድ ጊዜ እንደሚከታተሉ ሲገልጹ፣ 8 (11.4%) ተማሪዎች በጭራሽ እንደማይከታተሉ፣ 7(10%) ተማሪዎች ደግሞ ራድዮና ቴሌቪዥን ሁልጊዜ እንደሚከታተሉ መልስ ሰጥተዋል፡፡

በአጠቃላይ ማህበራዊ ብልሃቶችን አስመልክቶ ለተተኳሪ ተማሪዎች የቀረቡት የጽሁፍ መጠይቆች በተገኘው መረጃ መሰረት ተማሪዎች ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር በቡድን መወያየት፣ የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎችን ባህልና የአኗኗር ስርዓት ለማዳበር የሚያግዙ ብልሃቶችን የመጠቀም ብቃታቸው ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ምክንያቱም አብዛኞቹ ተማሪዎች የቃላት ችሎታቸውን ለማዳበር ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር ሲወያዩ፣ ሲጠይቁና የማህበረሰቡን ባህልና ስርዓት ለማወቅ የተለያዩ ፕሮግራሞችን ሲከታተሉ አልተስተዋለም፡፡

## 4.3 የውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች የቃላት መማር ብልሃቶችን መለየትና መተንተን ነው፡፡ ይህን ዋና አላማ መሰረት በማድረግ የተለያዩ ንኡሳን አላማዎች ተነድፈው ምላሽ አግኝተዋል ፡፡ በመሆኑም በምዕራፍ አራት ስር የቃላት መማር ብልሃቶችን በቀጥተኛ እና በኢቀጥተኛ ስር በመከፋፈል በጽሁፍ መጠይቅና በቃለ መጠይቅ የተሰበሰበውን መረጃ ከተለያዩ ምሁራን ሀሳብ ጋር በማያያዝ ለማቅረብ ተችሏል፡፡

ከጥናቱ ግኝት ስንነሳ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን ሲገለገሉ የሚጠቀሙት የቃላት መማር ብልሃት አጠቃቀማቸው አብዛኞቹ ተማሪዎች በብቃት እንደማይጠቀሙ የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡

ይህ ጥናት የትውስታ ብልሃቶችን በተመለከተ ተጠኚ ተማሪዎች ከቀረቡላቸው ስድስት ብልሃቶች ማለትም በቃል ክፍላቸው መቦደን፣ ተቃራኒና ተመሳሳይ ቃላትን ማደራጀት፣ከቦታ ጋር ማያያዝ፣ ምስል መፍጠር፣ በድርጊት ማሳየት የሚሉ ጥያቄዎች ቀርበውላቸው ሁሉንም የትውስታ ብልሃቶች አብዛሀኛዎቹ ተማሪዎች አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙበት ከትንተናው ውጤት መረዳት ተችሏል፡፡ ይህን የትንተና ውጤት በምናይበት ጊዜ ከበላይነሽ (2002) እና ከንጋቱ(2000) ጥናትም በትውስታ ብልሃቶች ስር ከቀረቡላቸው ስምንት ብልሃቶች ዝቀተኛ አጠቃቀም እንዳላቸው የትንተናው ውጤት አረጋግጧል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በምዕራፍ ሁለት በክለሳ ድርሳናት እንደተገለጸው Oxford (1990)የትውስታ ብልሃቶች ለቋንቋ ትምህርት ካላቸው ሚና አኳያ ከአንደኛ ደረጃ በላይ ያሉ ተማሪዎች አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙባቸው ለማየት ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ Wong(2005) ባደረጉት ጥናትና ምርምር የቋንቋ ተማሪዎች ማለትም የሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች  የትውስታ ብልሃት አጠቃቀምን ከሌሎች ብልሃቶች ጋር ሲነጻጸር ብልሃቱን ለመጠቀም ያላቸው ፍላጎት ዝቅተኛ እንደሆነ ለማየት ተችሏል፡፡ ይህ ጥናትም በቃል ክፍላቸው መቦደን፣ ተቃራኒና ተመሳሳይ ቃላትን ማደራጀት፣ከቦታ ጋር ማያያዝ፣ ምስል መፍጠር፣ በድርጊት ማሳየት የሚሉ ጥያቄዎች ቀርበውላቸው ሁሉንም የትውስታ ብልሃቶች አብዛሀኛዎቹ ተማሪዎች አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙበት  በጥናቱ ውጤት ትንተና ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም ከሁለቱ ምሁራን ጥናታዊ ግኚት ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የዚህ ጥናት ተሳታፊ ተማሪዎች ከቀረበላቸው 11 የአዕምሮታዊ ብልሃት ጥያቄዎች ውስጥ ሁለቱን ማለትም ሰዎችን የመጠየቅና የመተርጎም ብልሃትን በብቃት ሲገለገሉ ሌሎቹን ብልሃቶች ማለትም መለማመድ፣ መዝገበ ቃላት መጠቀም፣ ማስታወሻ መያዝ፣ መደጋገም፣ በአዕምሮ ማመላለስ፣ መጻፍ፣ ማዳመጥ፣ትኩረት ቃል ድምቅታ ብልሃቶችን አብዛኞቹ ተማሪዎች በብቃት እንዳልተጠቀሙ ከሰንጠረዥ ሶስት እስከ ስድስት ላይ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህን የትንተና ውጤት በምናይበት ጊዜ ከንጋቱ (2000) የጥናት ውጤት ጋር ተቃርኖ ያሳያል፡ ፡ ምክናየቱም ንጋቱ በሲዳምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ከአዕምሮታዊ ብልሃቶች ከቀረቡላቸው 8 ብልሃቶች በአብዛኛው በብቃት እንደሚጠቀሙና ሁልጊዜ በመደጋገም እንደሚጠቀሙ በጥናቱ ውጤት ተረጋግጧል፡፡

በዚህ ጥናት ለተተኳሪ ተማሪዎች ከቀረበላቸው ሶስት አካካሽ ብልሃቶች ውስጥ ከአገባባቸው መገመትና ከአካል እንቅስቃሴ የመገመት ብልሃቶችን አብዛኞቹ ተጠኚዎች ሁልጊዜ በመደ.ጋገም እንደሚጠቀሙ መረጃው ያመለክታል። ይህን የትንተና ውጤት በምናይበት ጊዜ ከንጋቱ (2000) እና ከአፍወርቅ(2008) የጥናት ውጤት ጋር የሚስማማ ሆኖ ተገኝቷል። ምክናየቱም ሁለቱም ባካሄዱት ጥናት ተተኳሪ ተማሪዎች የቀረበላቸውን አካካሽ ብልሃቶች ሙሉ በሙሉ በብቃት እንደተጠቀሙበት በጥናቱ ውጤት ማረጋገጥ ተችሏል።

በምዕራፍ ሁለት በክለሳ ድርሳናት እንደተጠቀሰው Oxford (1990፣ 47) እንዳስገነዘቡት አካካሽ ብልሃቶች ተማሪዎች በቂ የቃላት እውቀት ክምችት እጦትን ለማካካስ የሚረዱ ብልሃቶች ናቸው ። ለቃላት ትምህርት የበለጠ ተገቢነት ያለው አካካሽ ብልሃት የአዳዲስ ቃላትን ፍች ከአውድ የመገመት ብልሃት ነው። እነዚህ ብልሃቶች ተማሪው ሁለት የተለያዩ ፍንጮችን(መረጃዎችን) ማለትም ስነ ልሳናዊና ኢ-ስነልሳናዊ መረጃዎችን በመጠቀም የአዳዲስ ቃላትን ትርጉም ለመገመት የሚረዱ ናቸው። በመሆኑም ይህ ጥናት ከምሁራኑ ሀሳብ ጋር የተስማማ ነው።

በዚህ ጥናት ተተኳሪ ተማሪዎች ልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶችን በተመለከተ የተገኘው ውጤት እንዳመለከተው የጽሁፍ መጠይቅ የተደረገላቸው አዳዲስ ቃላትን ሲማሩ እቅድ እንደማያወጡ፣ አላማና ግብ እንደማያዘጋጁ፣ ስህተታቸውን በራሳቸው እንደማይለዩና እንደማይገመግሙ ከሰንጠረዥ8 ለመገንዘብ ተችሏል። ይህ ውጤት ከንጋቱ (2000)፣ ከበላይነሽ (2002) የጥናት ውጤት ማለትም ተማሪዎቹ የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን የሚማሩበት መንገድ ልእዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶችን በብቃት መጠቀም እንዳልቻሉ ከሚያስረዳው የጥናት ውጤት ጋር ተመሳሳይነት ያሳያል።

ልእለ አዕምሮታዊ ብልሃቶች ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን በቀላሉ ለመማር ተገቢ የሆኑ የቃላት መማር ብልሃቶችን መምረጥ እንዲችሉ ያግዛቸዋል። ስለዚህ እነዚህ ብልሃቶች ተማሪዎች የቀረጹትን አላማ ለማሳካት፣ የተጠቀሙባቸውን ብልሃቶችን ውጤታማነት በመገምገም የወደ ፊት የመማር አቅጣጫዎችን የሚወስኑበት በመሆኑ በተገቢው ሁኔታ እንድጠቀሙበት ማስቻል ተገቢ ነው Oxford (1990)፣ Schmiit (2000)። በመሆኑም ይህ ጥናት ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት የምሁራን ሀሳብ ጋር የተቃረነ ሁኖ ተገኝቷል።

በዚህ ጥናት ስሜት ነክ ብልሃቶችን የተመለከቱ ጥያቄዎች ቀርበው ተጠኚ ተማሪዎች ሶስቱንም ብልሃቶች በብቃት እንደማይጠቀሙ የጥናቱ ውጤት ትንተና አረጋግጧል፡፡ በመሆኑም ከOxford (1990) ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች የሁለተኛ ቋንቋ ቃላትን በሚማሩበት ወቅት የሚያጋጥማቸውን የስሜትና የመነቃቃት ችግር በብቃት ይቋቋሙታል በማለት ከገለጸው ሀሳብ ጋር የሚቃረን ነው፡፡

በዚህ ጥናት ተተኳሪ ተማሪዎች ማህበራዊ ብልሃቶችን በተመለከተ በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተገኘው ውጤት እንዳሳየው የጽሁፍ መጠይቅ የተደረገላቸው ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን ሲማሩ ከሌሎች ጋር ተባብሮ በጥንድ በቡድን መስራት እንዳልቻሉና የተለያዩ ምንጮችን እንደማይከታተሉ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በመሆኑም ይህ የጥናት ግኝት ከ Omalley እና Chamot (1990)፣ Oxford (1990) ተማሪዎች ቋንቋን ሲማሩ ከሌሎች ጋር በመተባበር፣ በመተጋገዝ፣ ተጨማሪ ማብራሪያዎችን በመጠየቅ እንድሁም ከሌሎች ሰዎች ጋር ማህበራዊ ተራክቦ በመፍጠር ቃላትን እንድማሩ የሚረዱ ናቸው ከሚለው ሃሳብ ጋር ይህ ጥናት የሚቃረን ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በአጠቃላይ የዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ግኝት እንዳሳየው በቀጥተኛና በኢ-ቀጥተኛ የቃላት መማር ብልሃት አይነቶች ውስጥ የሚካተቱ ንኡሳን ብልሃቶች (በተለይ በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ውስጥ ትኩረት የተደረገባቸው) ተጠኚ ተማሪዎች የቃላት አጠቃቀም ብቃታቸው የተወሰኑትን ብልሃቶች ቢያዳብሩም አብዛኞቹ ተማሪዎች በብቃት እንደማይጠቀሙ ከመረጃው መረዳት ተችሏል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና አስተያየት

## 5.1. ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት አብይ አላማ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን ለመማር የሚጠቀሙባቸውን የቃላት መማር ብልሃቶች መለየትና መተንተን ነበር። በዚህ አብይ አላማ ስር በጥናቱ መጨረሻ ላይ ምላሽ ያገኛሉ ተብለው የታሰቡትን የጥናቱ ዝርዝር አላማዎች ተጠቅሰዋል። እነሱም፡-

1. ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን በሚማሩበት ጊዜ የትኞቹን ብልሃቶች በተደጋጋሚ አብዝተው እንደሚጠቀሙ መለየት

2. በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በራሳቸው የአማርኛ ቃላትን የሚማሩበትን መንገድ ቃላትን የመማር ብልሃቶች በብቃት መጠቀም ላይ የተመሰረተ መሆን ወይም አለመሆኑን መመርመር

3. የተለያዩ ብልሃቶችን አብዝቶ መጠቀም ለሁለተኛ ቋንቋ መማር ያለውን ጠቀሜታ መመርመር የሚሉ ዝርዝር አላማዎች ይዞ የተካሄደ ጥናት ነው። ጥናቱ ትኩረት ያደረገው በአማራ ክልል በኦሮሚያ ብሔረሰብ ልዩ ዞን በደዋ ጨፋ ወረዳ በሩፍሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ በፈቱ 70 የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በአመቺ ንሞና በተመረጡ ተጠኚዎች ላይ ነው። ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የተመረጠው ዋነኛው መሳርያ የጽሁፍመጠይቅ ነው። የጽሁፍመጠይቁ የተዘጋጀው የተማሪዎችን የቃላት መማር ብልሃት አጠቃቀም መሰረት ያደረጉ 30 ጥያቄዎች በአጥኚው፣ በአማርኛ ቋንቋ መምህራንና በጥናቱ አማካሪ አስተያየት ከተሰጠባቸው በኋላ ነበር። በጽሁፍ መጠይቆች አማካኝነት የተገኙ መረጃዎችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በአጋዥ የመረጃ መሳሪያነት ያገለገለው ቃለመጠይቅ ነው።

የቃላት መማር ብልሃቶችን የሚገልጹ የጽሁፍመጠይቆች በሰንጠረዥ መልኩ ተደራጅተው እንዲታዩ በማድረግ በቃለመጠይቅ ከተገኙ መረጃዎች ጋር እርስበርሳቸው እየተደጋገፉ በአይነታዊ የመረጃ አተናተን ዘዴና በገለጻ ዘዴ ትንተና ተደርጓል፡፡

ከውጤት ትንተናው መረዳት እንደተቻለው ተማሪዎቹ የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን የሚማሩበት መንገድ አብዛኞቹ ተጠኚዎች ቃላትን የመማር ብልሃታቸው ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል ፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው ተጠኚ ተማሪዎች ከመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጭ አብዛኞቹን ብልሃቶች በራሳቸው ጥረት ልምምድ እንደማያደርጉና የራሳቸው አስተማሪዎች እንዳልሆኑ መገንዘብ ተችሏል፡፡ በዚህ መሰረት እያንዳንዱንየቃላት መማር ብልሃቶች ከተጠኚ ተማሪዎች የተገኘው የትንተና ውጤት በሚከተለው መልኩ ቀርቧል፡፡

በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ተተኳሪ ተማሪዎች በትውስታ ብልሃት ስር ከሚካተቱ ብልሃቶች ማለትም የማቧደን፣ ከቦታ ጋር ማያያዝን፣ ምስል በመፍጠር በድርጊት ማሳየትንና በንግግር ወይም በጽሁፍ በማስገባት መለማመድን በተሰበሰበው መረጃ መሰረት አብዛኞቹ ተማሪዎች አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ በጥናቱ ውጤት ተረጋግጧል፡፡ ተጠኚ ተማሪዎች ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን የቃላት መማር ብልሃቶች በብቃት አለመጠቀማቸው ለእያንዳንዱ ብልሃት በመማርያ ክፍል ውስጥ ሲማሩ ልምምድ ካለማድረግና ትኩረት ካለመስጠት ይሆናል፡፡

በአዕምሮታዊ ብልሃቶች ስር የሚካተቱትን በተመለከተ ተጠኚ ተማሪዎች (ቃላትን መደጋገም፣ በአዕምሮ ማሰላሰልና ማዳመጥን፣ ምንጭመጠቀምን፣ መተርጎምን፣ ንበትን መለማመድ፣ ማስታወሻ መውሰድን፣ ትኩረትቃል ድምቅታንና ተፈጥሯዊ ልምምድን መሰረት ያደረጉ ጥያቄዎች ቀርበውላቸው ሁለቱን ብልሃቶች ማለትም ወደ አፍመፍቻ ቋንቋ መተርጎምንና የቃላትን ፍች ከመምህራንና ከጓደኞቻቸው ጠይቀው በመረዳት አብዛኞቹ ተማሪዎች ሁልጊዜ እንደሚጠቀሙ ከትንተና ውጤቱ መረዳት ተችሏል፡፡ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ሌሎቹን ብልሃቶች ግን አብዛኛው ተማሪ አልፎአልፎ እንደሚገለገሉ መረጃው ይጠቁማል፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ ተጠኚ ተማሪዎች በቀረበላቸው የጽሁፍ መጠይቅና ቃለመጠይቅ መረጃ አብላጫው ተማሪ በአዕምሮታዊ ብልሃቶች ላይ ያሳዩት የቃላት አጠቃቀም ብቃት ዝቅተኛ መሆኑን መረጃው አሳይቷል፡፡

አካካሽ ብልሃቶችን በተመለከተ በተጠኚ ተማሪዎች ላይ በተካሄደው ምርመራ ተማሪዎቹ የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን የሚማሩበት ስልት በብቃት ላይ የተመሰረተ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ምክንያቱም አካካሽ ብልሃቶች ተማሪዎች በቃላት እውቀት ማነስ ምክንያት በተግባቦት ሂደት የሚያጋጥማቸውን ችግር ለመቋቋም የሚጠቀሙባቸው ናቸው፡፡ ስለሆነም በአካካሽ ብልሃቶች ስር ከአገባባቸው መገመትና ከተናጋሪው የአካል እንቅስቃሴ መገመትን የሚመለከቱ ሶስት ጥያቄዎች ለተማሪዎች ቀርበውላቸው አብዛኞቹ ቃላትን ከአገባባቸው በመገመትና ከሰዎች የአካል እንቅስቃሴ በመገመት ሁልጊዜ እንደሚጠቀሙ የትንተናው ውጤት ያስረዳል፡፡

በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶችን በተመለከተ በተተኳሪ ተማሪዎች ላይ በተካሄደው ምርመራ ተጠኚዎች የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን የሚማሩበት ስልት ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎቹ በልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶች ስር በተመደቡ ማለትም አላማናግብ ማስቀመጥ፣ ራስን መቆጣጠርና መገምገም፣ እቅድ ማዘጋጀትና ስህተትን በራስ መለየት ነበሩ፡፡ በጽሁፍ መጠይቁና በቃለመጠይቁ በተገኘው መረጃ መሰረት አብዛኞቹ ተማሪዎች አልፎአልፎ ብልሃቶቹን እንደሚጠቀሙ የትንተናው ውጤት ያሳያል፡፡

ስሜትነክ ብልሃቶችን በተመለከተ በተጠኚ ተማሪዎች ላይ በተካሄደው ምርመራ ተማሪዎቹ የአማረኛ ቃላትን የሚማሩበት መንገድ በብቃት ላይ የተመሰረት ሆኖ አልተገኘም ፡፡ ምክንየቱም ተማሪዎቹ የቃላት ትምህርትን ለማወቅ ራስን ማዝናናት፣ ራስን ማድነቅ፣ ንቁተሳታፊነት የሚባሉትን የስሜት ነክ ቁጥጥር ብልሃቶችን ትኩረት ሰጥተው ሲጠቀሙ አልታዩም፡፡ በመሆኑም እነዚህን ብልሃቶች አብዛኞቹ ተጠኚዎች አልፎአልፎ እንደሚገለገሉባቸው የትንተናው ውጤት ያሳያል፡፡

በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ውስጥ ማህበራዊ ብልሃቶችን በተመለከተ ማለትም በቡድን ማወያየትን፣ ባህላዊ እውቀትን ማዳበርን የሚጠይቁ አጠቃቀሞችን ለተጠኚ ተማሪዎች ቀርበው አብላጫው ተማሪ እነዚህን ብልሃቶች አልፎአልፎ እንደሚጠቀሙበት ከትንተና ውጤቱ መረዳት ተችሏል፡፡

ምክንያቱም በተሰበሰበው መረጃ መረዳት እንደተቻለው ተማሪዎቹ የቃላት እውቀታቸውን ለማሳደግ ከጓደኞቻቸው ጋር ቡድን ፈጥረው ልምምድና የማህበረሰቡን ባህል፣ ወግና የአኗኗር ዘይቤ ለማወቅ ያላቸው ፍላጎት የዳበረ አለመሆኑን ያሳያል፡፡

በእያንዳንዱ ንዑስ አላማ የተገኘው ውጤትም እንደሚከተለው ለማጠቃለል ተችሏል፡፡

የመጀመርያው ዓላማ ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን በሚማሩበት ጊዜ የትኞቹን ብልሃቶች በተደጋጋሚ አብዝተው እንደሚጠቀሙ መለየት የሚል ነበር፡፡ የተገኘው ውጤት እንዳሳየው ተማሪዎቹ በትውስታ ስር ከቀረቡላቸው ስድስት ብልሃቶች አብዛኞቹ 177(252.9% )ያህልጊዜ በመደጋገም አልፎ አልፎ ሲጠቀሙ፣ከአዕምሮታዊ ብልሃቶች ስር ደግሞ መተርጎምንና መጠየቅን ሁልጊዜ ሲጠቀሙ፣ አብዛኞቹን ብልሃቶች 425(607%)ያህል ጊዜ ብልሃቱን በመደጋገም አልፎ አልፎ ተጠቅመዋል፡፡ በአንጻሩ ደግሞ አካካሽ ብልሃቶችን በተመለከተ አብላጫው 101(144.3%)ያህል ጊዜ ደጋግመው ሁልጊዜ እንደተጠቀሙት ሲገልጹ፣ ልዕለአዕምሮታዊ ብልሃቶችን ደግሞ 122(174.2%) ያህልጊዜ ደጋግመው አልፎአልፎ እንደሚጠቀሙ መረጃው ያመለክታል፡፡ በተመሳሳይ መልኩም በስሜትነክ ቁጥጥር ብልሃቶች ስር ከቀረቡላቸው ሶስት ብልሃቶች አብዛኞቹ ተማሪዎች 144(205.5%) ጊዜ በመደጋገም አልፎ አልፎ ሲጠቀሙ፣ማህበራዊ ብልሃቶችን በተመለከቱ ደግሞ 61(87.1%) ያህል ጊዜ አልፎአልፎ በመደጋገም በብቃት እንደማይጠቀሙ ከትንተናው መረዳት ተችሏል፡፡ በመሆኑም ተጠኚ ተማሪዎች በተደጋጋሚ አብዝተው የሚጠቀሙት አካካሽ ብልሃቶችን ሲሆን ሌሎቹን ብልሃቶች ግን ሁልጊዜ በመደጋገም አብዝተው እንደማይጠቀሙባቸው ውጤቱ ያሣያል፡፡

ሁለተኛው ዓላማ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች በራሳቸው የአማርኛ ቃላትን የሚማሩበትን መንገድ ቃላትን የመማር ብልሃቶች መጠቀም አለመጠቀማቸውን መመርመር ነበር፡፡ ይህን አላማ በተመለከተ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው የተማሪዎቹ የትውስታ፣የአዕምሮታዊ፣የልዕለ አዕምርታዊ፣ስሜትነክና ማህበራዊ ብልሃቶችን ሲገለገሉ በብቃት ላይ የተመሰረተ እንዳልሆነ ያሳያል፡፡ ነገርግን የአካካሽ ብልሃት አጠቃቀማቸው በብቃት ላይ የተመሰረተ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሶስተኛው ዓላማ ደግሞ የተለያዩ ብልሃቶችን አብዝቶ መጠቀም ለሁለተኛ ቋንቋ መማር ያለውን ጠቀሜታ መመርመር ነበር፡፡ ይህን አላማ በተመለከተ የተገኘው መረጃ

እንደሚያመለክተው ተማሪዎች አብዛኛዎቹን ብልሃቶች በብቃት ባያዳብሩም የተወሰኑትን ብልሃቶች(የመተርጎም፣የመጠየቅ) አዕምሯዊ ብልሃቶችንና ከአካካሽ ብልሃቶች(ከአገባባቸው መገመት፣ከአካል እንቅስቃሴ የመገመት) ብልሃቶችን በብቃት እንደተገለገሉበት መረጃው ያሳያል፡፡ በመሆኑም ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች እነዚህን ብልሃቶች በመጠቀማቸው ቋንቋን ለመማር መንገድ እንደከፈተላቸውና በተግባቦት ሂደት የችሎታ ማነስ ቢኖር የማካካሻ ዘዴ ተጠቅመው እንደተገለገሉ ከትንተና ውጤቱ መረዳት ተችሏል፡፡

ጠቅለል ባለመልኩ ሲታይ በዚህ ጥናት ውስጥ የተማሪዎቹ የቃላት አጠቃቀም የሚማሩበት መንገድ ከስድስቱ የቃላት መማር ብልሃቶች ለአካካሽ ብልሃቶች ብቻ ትኩረት ሰጥተው እንደሚማሩና ቀሪዎቹን ብልሃቶች ልምምድ እንዳላደረጉ በጽሁፍ መጠይቅና በቃለመጠይቅ በተሰበሰበው መረጃ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

## 5.2 መደምደሚያ

ይህ ጥናት ከተነሳበት አብይ አላማ አንጻር ሲታይ የሩፍሴ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህረት ቤት የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን ሲገለገሉ የሚጠቀሟቸው የቃላት መማር ብልሃቶችን ለመመርመር ሲሆን፤ በዚህም መሰረት በጥናቱ በጥልቀት ከታዩ ትንተናዎችና ከውጤቱ በመነሳት ከዚህ በታች በአጭሩና በግልጽ ለመደምደም ተሞክሯል፡፡

ይህ ጥናት ያተኮረባቸው የኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎች አሁን ካሉበት የክፍል ደረጃ አንጻር ሲታይ ቢያንስ ለደረጃቸው የሚመጥን የቃላት መማር ብልሃት አጠቃቀማቸው የተሻለ እንደሚሆን ይታሰባል፡፡ በመሆኑም ጥናቱ ሊመለከታቸው የሚገቡ ዝርዝር አላማዎች፡- በመጀመሪያ ተማረዎቹ የአማርኛ ቃላትን በሚማሩበት ጊዜ የትኞቹን ብልሃቶች በተደጋጋሚ አብዝተው እንደሚጠቀሙ መለየት፣ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በራሳቸው የአማርኛ ቃላትን የሚማሩበትን መንገድ ቃላትን የመማር ብልሃቶች በብቃት መጠቀም ላይ የተመሰረተ መሆን ወይም አለመሆኑን መመርመር እና የተለያዩ ብልሃቶችን አብዝቶ መጠቀም ለሁለተኛ ቋንቋ መማር ያለውን ጠቀሜታ መመርመር የሚሉ ዝርዝር አላማዎች ይዞ የተካሄደ ጥናት ነው፡፡

ይህን አላማ በተመለከተ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ተጠኚ ተማሪዎች በተደጋጋሚ አብዝተው የሚጠቀሙት አካካሽ ብልሃቶችን ሲሆን ሌሎቹን ብልሃቶች ግን በመደጋገም አብዝተው እንደማይጠቀሙባቸው ውጤቱ ያሣያል፡፡

የተማሪዎቹ የትውስታ፣የአዕምሮታዊ፣የልዕለ አዕምርታዊ፣ስሜትነክና ማህበራዊ ብልሃቶችን ሲገለገሉ በብቃት ላይ የተመሰረተ እንዳልሆነ ሲያሳየን በአንጻሩ የአካካሽ ብልሃት አጠቃቀማቸው በብቃት ላይ የተመሰረተ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች እነዚህን ብልሃቶች በመጠቀማቸው ቋንቋን ለመማር መንገድ እንደከፈተላቸውና በተግባቦት ሂደት የችሎታ ማነስ ቢኖር የማካካሻ ዘዴ ተጠቅመው እንደተገለገሉ ከትንተና ውጤቱ መረዳት ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ቃላትን የመማር ብልሃት አጠቃቀማቸው ዝቅተኛ እንደሆነ ከጥናት ውጤቱ መረዳት የተቻለ ሲሆን ይህም ሲባል አብዛኞቹ የቃላት አጠቃቀም ብልሃታቸው በብቃት ላይ የተመሰረተ እንዳልሆነ ና ተማሪዎቹ የታላሚውን ቋንቋ ቃላት በትምህርት ቤት ውስጥም ሆነ ውጭ ከታችኛው የክፍል ደረጃ ጀምረው የተማሩትና የተለማመዱት አሁን ባሉበት የክፍል ደረጃም እየተማሩ ባሉበት ሁኔታ ውሰጥ መሆኑ የቃላት መማር ብልሃት አጠቃቀም ብቃታቸው የዳበረ አለመሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡

## 5.3 አስተያየት

የዚህን ጥናት ውጤት መሰረት በማድረግ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተጠኚ ተማሪዎች ለቃላት ትምህርት አጠቃቀም ውጤታማነት በተለያዩ መንገድ እገዛ የሚያደርጉት የቃላት መማር ብልሃቶችን በብቃት እንደማይገለገሉባቸው፤ ስለመማር ብልሃቶችም ያላቸው እውቀትና ልምድ የዳበረ አለመሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በመሆኑም ይህንን ክፍተት ለመሙላት የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ወይም የትምህርት ባለሙያዎች ልዩ ትኩረት ያደርጉባቸው ዘንድ የሚከተሉት አስተያየቶች ቀርበዋል፡፡

1. የሚመለከታቸው የአማርኛ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት፣ መርሃ ትምህርት ባለሙያዎች፣ የአማርኛ መማርያ መጻሕፍትና የመምህር መምሪያ አዘጋጆች የቃላት ትምህርትን ሲያዘጋጁ የቃላት መማር ብልሃቶችን በተመለከተ ስነ-ዘዴዎችን ቅርጸው እንደ አንድ የቃላት ትምህርት

ማቅረቢያ መንገድ ቢጠቀሙበትና ተግባራቱንም የቋንቋ መማር ብልሃቶችን በግልጽ ለመለማመድ የሚረዳ አቀራረብ ተከትለው ቢያዘጋጁ፣

2. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪዎቻቸውን የቃላት እውቀት ለማሻሻል አስፈላጊውን ዝግጅት በማድረግ በመማርያ ክፍል ውስጥና ውጭ ተማሪዎች በራሳቸው ጥረት እንዲሳተፉ ቃላትን የሚማሩበት መንገድ ቢያመቻቹላቸውና ክትትል ቢያደርጉ፣

3. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቃላት መማር ብልሃት ግንዛቤን በተመለከተ የልምድ ልውውጥ፣ ውይይቶች፣ ሲሚናሮች፣ አጫጭር ስልጠናዎች፣ሙያ ማሻሻያ የትምህርት እድሎች ያለማቋረጥ ቢሰጡ፣

4. ተማሪዎች የቃላት እውቀታቸውን ለማሻሻል ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሙሉ ፍላጎት ኑሯቸው በትምህርትቤት ውስጥም ሆነ ውጭ በራሳቸው ጥረት ልቦለዶችን፣ጋዜጣዎችን፣ መጽሔቶችን የተለያዩ አዝናኝ ግጥሞችን በማንበብና ራዲዮ በማዳመጥ የመማር ብልሃታቸውን ቢያዳብሩ፣

5. የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የቃላት ትምህርት ችሎታቸውን ለማዳበር ይረዳቸው ዘንድ የቃላት መማር ብልሃቶችን ምንምን እንደሆኑና በምን መልኩ መጠቀም እንዳለባቸው ትኩረት ሰጥተው በክፍል ውስጥም ሆነ ውጭ መማር ቢችሉ፣

6. የዚህ ጥናት ውጤት የቃላት መማር ብልሃቶችን መማር በአንድ የክፍል ደረጃ በሁለት የመማሪያ ክፍሎች ብቻ ተከናውኖ የተገኘ ከመሆኑ አኳያ ውስንነት ስለሚኖረው ሌሎች ተመራማሪዎች በቀሪዎቹ የክፍል ደረጃዎችና በርከት ባሉ የጥናት ተሳታፊዎች ረዘም ላለ ጊዜ በመስጠት ተጨማሪ ጥናት ቢያደርጉ፣

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱትን ሀሳቦች ተግባራዊ ማድረግ ከተቻለ ተማሪዎቹ የቃለት መማር ብልሃቶችን ለመለማመድ፣ እውቀትና ልምድ ለማዳበር፣ በቃላት ትምህርታቸው ላይ ውጤታማ ለመሆን የጎላ ድርሻ ይኖረዋል የሚል እምነት አለኝ፡፡

**ዋቢመጻህፍት**

በላይነሽ ደነቀ፡፡ (2002)፡፡ "በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛቃላትን ለመማር የሚገለገሉባቸውን የመማር ብልሃቶች ፍተሻ፡፡" የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት፣ አዲስ አበባ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

በላይነሽ ደነቀ፡፡ (2010)፡፡ «የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ማስልጠን ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የቃላት ችሎታ መዳበር ያለው አስተዋጽኦ በዘጠነኛ ክፍል ኦሮምኛ ቋንቋ ተማሪዎች ተተኳሪነት፡፡" ለዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ:: (ያልታተመ)፡፡

ባየ ይማም፡፡ (2000)፡፡ የአማርኛ ሰዋሰው፡፡ የተሻሻለ ሁለተኛ እትም፣ አዲስ አበባ፣ እሌኒ.ማ. ኃ.የተ.የግ. ማህበር፡፡

ብሩክታዊት ተስፋይ፡፡ (2001)፡፡ "በመቀሌ ከተማ በሚገኙ ሦስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ የመንግስት ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል የቃላት ትምህርት አተገባበር ፍተሻ፡፡" የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት፣ አዲስ አበባ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

ተክላይ ትዕዛዙ፡፡(2000)፡፡ "በትግርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ8ኛ ክፍልና የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ንባብ ጊዜ የንባብ ብልሃት አጠቃቀምና የመምህራን ተጣጥሞ ፍተሻ በአክሱም ከተማ አንደኛና ሁለተኛ መነሻነት" አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን በማስተማር ስነ-ዘዴ ትምህርት ለማስተርስ ድግሪ ማሙያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

ታደሰ ሲባም፡፡ (2004) ፡፡ "አማርኛ የማስተማር ስነዘዴ II" ለድህረ ምረቃ ድፐሎማ(Post Graduate Diploma inTeaching) መርሃ ግብር የተዘጋጀ ሞጁል ትምህርት ሚኒስተር ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

ንጋቱ አሰፋ፡፡ (2000) ፡፡ "በሲዳምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛን ቃላት ሲማሩ የሚጠቀሙባቸው ቃላትን የመማር ብልሃቶች ምርምራ፡፡"

የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት፣ አዲስ አበባ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

አፈወርቅ ይስሀቅ፡፡ (2008)፡፡ "በጋሞ ጎፋ ዞን ምዕራብ አባያ ወረዳ ሁለተኛ ደረጃ መሰናዶ ትምህርት ቤት የሚማሩ አፈፈትና ኢ-አፈፈት የሆኑ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን ሲማሩ የሚጠቀሙባቸው ቃላትን የመማር ብልሃቶች ትንተና፡፡" የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት፣ አዲስ አበባ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

እሸቱ አጋ፡፡ (1997)፡፡ "በአዲስ አበባ በሚገኙ ሶስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ያተኮረ የቃላት ትምህርት የክፍል ውስጥ አቀራረብ ግምገማ፡፡" የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት፣ አዲስ አበባ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

ደረበ ሙሉ፡፡ (1999)፡፡ " በትግርኛ ቋንቋ አፋቸውን ለፈቱ ዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቃላት ትምህርት አቀራረብ ፍተሻ፡፡" የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት፣ አዲስ አበባ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

ደረጀ ገብሬ፡፡ (2013)፡፡ መራሔ ንባብ ፡፡ አድስ አበባ፡፡ አፍሪካ ማተሚያ ቤት፡፡

ይርጋ ዓለም፡፡ (1993) ፡፡ "አፋቸውን በከፍኛ የፈቱ ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች አማርኛ ሲማሩ የሚገለገሉባቸው ቋንቋን የመማር ብልሃቶች እና የመምህራን ግንዛቤ አሰሳ " በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል አማርኛ በማስተማር (TeAm) ለሁለተኛ ድግሪ ማሙያ የቀረበ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

Atkin, J.et.al. (1995). Skills Development Methodology. Part I. Addis Ababa: Addis Ababa University Printing Press.

Bornay, N. (2011). Explicit Strategy Training in Vocabulary Learning for Beginning Spanish Students. International Review of Social Sciences and Humanities. Vo1. 4. Issue3.

Brown, H.D. (1994). Principles of Language Learning and Teaching: Cambridge. Cambridge University Prentice - Hall.

Catalon, R, M. J. (2003). Sex Differences in L2 Vocabulary Learning Strategies.International Journal of Applied Linguistics, 13(1), 54-77.

Cook, V. (1991). Second Language Learning and Teaching. London: A member of the Hodder Headline Group.

Cubukcu, F. (2007). An Investigation of Reading Strategies Employed by Trainee Teachers. GEMA Online Journal of Language Studies, Vol.7 (2) pp 95-110.

Ellis, R. (1994). The study of Second Language Acquisition Oxford: Oxford University Press.

Goethals, M. Rev (1994) "Rebecca L.Oxford: Language Learning Strategies: what every teacher should know new bury Hourse, 1990, "in ira Linguistics. Vol. 15No. 4 December 1994 Oxford: University Press.

Griffiths, C.(2004). Language Learning Strategies .Theory and Research .New Zealand,AIS St Helens ,Auckland, New Zealand,School of Foundations Studies.pp 1-25.

Harmer, J. (1991). The Practice of English Language Teaching. New York: Longman Group UK Limited.

Hedge, T. (2000). Teaching and learning in the language classroom. Oxford: Oxford University Press.

International Journal of Applied Linguistics, 13(1), 54-57.

He, Y.(2010) A study of Second Language Vocabulary Learning Strategies. The English Teaching Forum. Vol .38 Mum.4pp 12-15.

Hunt, A and Belgar, D. (2003).Current Research and Practice in Teaching. Vocabulary.in Richards, J and willi resnandya (Eds).Methodology in Language: An Anthology of current Practic. Cambridge: Cambridge University press, Vol.4 No.4 pp313-319.

Huttennen, Irma.(1996). "Learning to Learn" an overview Language Teaching :An International Abstracting Journal for Language Teachers: Teacher education and Researchers. Cambridge:Cambridge University Press. Vol.29.No 5; 2-4 pp.86-98.

Jurkovic, V. (2006). Vocabulary Learning Strategies in an ESP Context. TESOL Quarterly, 2 (1), 23-32

Ling, S. (2011). Investigation Chinese English Majors Use of Reading Strategies. A study on the Relationship Between Reading Strategies and Reading Acheivements .Sweden ,Tutor: Carita Lundmark .kvistianstad University. EN 2460 Level 1v English, School of Teaching Education.

Little, D. (1994).Words and their properties: Arguments for alexical Approch to pedagogical Grammer. Inodlin, T (Ed), perspective on pedagogical Grammer. Cambrige University press, 200-205.

Macaro, E. (2001). Learning Strategies in Foreign and Second Languge Class room. London: Continuum.

Mahdavi, M. (2014). Metacognitive Strategy Training and Vocabulary Learning in an Input- Poor Enviroment. International Journal of Multidispilinary and Current Research.Vol.2

McCarthy, M. (1990). Vocabulary: Oxford: Oxford University Press.

McCrostie, J. (2007).Exammining Learner Vocabulary Note Books. ELT Journal, 61(3), 24

Mukoroli, J. (2010). Effective Vocabulary Teaching Strategies for the English for.Acadamic Purposes ESL Class Room.

Nation, P. (1990). Teaching and Learning Vocabulary. New York: Newbury House Publisher.

Nation, P. (2000). Learning Vocabulary in Lexical Sets: Dangers and Guidelines.

Nation, P. (2001). Learning Vocabulary in Another Language. Cambridge: Cambridge University Press.

New York: Newbury House Publishers.

Nation, P. (2005). Teaching and learning vocabulary. In E. Hinkel (Ed.), Handbook and research in second language teaching and learning (pp. 581-595). New Jersey: Lawrence Erlbaum

Nyikos, M. and Fan, M.(2007). Areview of Research on Vocabulary Learning Strategies. In A. Cohen and Macaro (Eds.), Language Learner Strategies (pp.251-273).Oxford: Oxford University Press.

O'malley, J.M. and Chamot A.U. (1990). Learning Strategies in Second Language Acquisition. Cambridge: Cambridge University press.

Oxford, R. (1990). Language Learning Strategies: What Every Teacher Should Know.New York: New bury House Publishers.

Oxford, R. and R.C. Scarcella. (1994). ASecond Language Vocabulary learning Among Adults: State of the Art in Vocabulary Instruction. System.Vol.22, No. 2, pp.213-14.

Oxford, R. & Schramm, K. (2007). Bridging the gap between Psychological and Sociocultural Perspectives on L2 Learner Strategies. In Cohen, A. D., &

Macaro, E. (Eds.). (2007). Language Learner Strategies: Thirty years of Research and Practice. Oxford, UK: Oxford University Press.

Pemberton, R. (2003). Remembering vocabulary, V4. Hong Kong: Language Center,HKUST.Available:http://lc.ust.hk/~sac/advice/english/vocabulary/V4.htm

Pikulski,J. and Templeton Shane.(2004). Teaching and Developing Vocabulary: Key to Long-Term Reading Success.http://www.eduplace.com/state/author/pik/temp.pdf Retrieved 2Sep.2010.2:19pm.

Rajaee, M. (2013). The Effect of Strategy Training on the Vocabulary Development of ESL Learners in Public High Schools of Iran. Theory and Practice in Language Studies, Vol.3. No.11, pp.2061-2066.

Read, J. (2000). Assessiing Vocabulary. Cambridge: Cambridge University Press.

Rubin, J. (1987). Learner Strategies: Theoretical Assumption, Research History and Typology. In A. Wenden and J. Rubin (Eds.). Learner Strategies in Language Learning. (pp.107-160). Cambridge: Cambridge University Press.

Schmitt, N. (1997). Vocabulary Learning Strategies. In Schmitt N and Mc Carthy (Eds.). Vocabulary: Discriptive, Acquisition and Pedagogy pp. 199-228.

Schmitt, N. (2000). Vocabulary in Language Teaching. Cambridge: Cambridge University Press.

Ur, P. (1996). Acourse in Language Teaching: Practice and Theory: Cambridge Teacher Teraining and Development.United Kingdom at the University Press, Cambridge.

Vermeer, A. (2001). Breadth and Depth of Vocabulary in Relation to L1/ L2 Acquisition and Frequence of Input: Applied Psycholinguistics, 22, (2), 217-234.

Wharton Glenn. (2000). Language Learning Strategy of Bilingual Language Learner in sign. Language Learning: A Journal of Research in Language Study: University of Michigan. Black weel publisher, vol. 50 Nos.1-3 pp.203-243.

Wong.MSL.(2005).Language Learning Strategies and Language, Press.Self Efficacy investigating the relationship Malaysia. RELCJournal,36,245-269.http://dx.doi.org/10.1177.

# አባሪዎች

## አባሪ 1:- በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበ የጽሁፍ መጠይቅ

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

### የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ተግባቦት ኮሌጅ

### የአማርኛ ቋንቋ፣ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

ውድ ተማሪዎች:-

የዚህ ጽሁፋዊ መጠይቅ ዋና አላማ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋችሁን የፈታችሁ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን ስትማሩ የምትገለገሉባቸውን ቃላት የመማር ብልሃት አጠቃቀምን ለመተንተን ለሚካሄደው ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ ነው። ከእናንተ የሚገኘው መረጃ ለጥናቱ ከታሰበው ተግባር ውጭ የማይውል መሆኑን በቅድሚያ አረጋግጣለሁ። የምትሰጧቸው መልሶች በትክክል የእናንተን እውነተኛ ስሜትና እምነት የሚያንፀባርቅ እንዲሆኑ አደራ እላለሁ። በመሆኑም መጠይቁን በጥንቃቄ አንብባችሁ በመመርያው መሰረት ተገቢውን መልስ እንድትሞሉ በአክብሮት እየጠየኩ፣ለትብብራችሁም በቅድሚያ ከልብ አመሰግናለሁ።

<u>**ማሳሰቢያ፦**</u> 1. በመጠይቁ ላይ ስም መጻፍ አያስፈልግም

2.መጠይቁን ከጓደኛ ጋር በመወያየት መሙላት ወይም በሌላ ሰው ማስሞላት በሚሰበሰበው መረጃ ላይ ተጽዕኖ ስለሚያሳድር አይፈቀድም።

ክፍል አንድ ፦ የግል መረጃ መስጫ

ክፍል ...................................ምድብ(ሴክሽን)..................

እድሜ............................

ጾታ..................................

የአፍ መፍቻ ቋንቋ ................................

ክፍል ሁለት ፦ ቃላት የመማር ብልሃቶችን በተመለከተ የሚቀርብ የጽሁፍ መጠይቅ

መመርያ፦ ቀጥሎ አዳዲስ ቃላትን ለመማር የሚረዱ ብልሃቶች ላይ ያተኮሩ ሃሳቦች ቀርበዋል።እያንዳንዱን ሃሳብ በጥሞና አንብበህ(ሽ) የተጠቀሰውን ብልሃት አጠቃቀምህን(ሽን) አስመልክቶ ከቀረቡት ሁልጊዜ፣አንዳንድጊዜ፣አልፎአልፎ፣በጭራሽ ከሚሉት አማራጭ መልሶች መካከል አንዱን ብቻ በመምረጥ ከምርጫዎቹ ፊትለፊት በሚገኘው ሳጥን ውስጥ የ ''x'' ምልክት በማድረግ መልስ(ሽ)። ተማሪዎች ለእያንዳንዱ ሃሳብ ትክክል ወይም ስህተት መልስ የለውም። አንተ(ች) በታማኝነት መርጠህ(ሽ) የምትሰጠው/የምትሰጭው መልስ ነው ትክክለኛው መልስ ። ስለሆነም ይህ የክፍል ፈተና ስላልሆነ እውነተኛ የቃላት አጠቃቀምህን (ሽን) የሚገልጸውን መርጠህ( ሽ) መልስ (ሽ)።

በሰንጠረዡ የተመለከቱት ምርጫዎች የሚወክሉት

4. ሁልጊዜ እጠቀማለሁ

3. አንዳንድ ጊዜ እጠቀማለሁ

2. አልፎ አልፎ እጠቀማለሁ

1. በጭራሽ አልጠቀምም

| ተቁጥር | የቃላት መማር ብልሃቶችን የተመለከቱ ጥያቄዎች | ምርጫዎች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 1 | የአማርኛ ቃላትን ከተማርኩ በሁዋላ ለማስታወስ፣ በቃል ክፍላቸውለምሳሌ ስሞችን በአንድ ወገን፣ ግሶችንና ቅጽሎችን በሌላ ወገንእመድባቸዋለሁ። | | | | |
| 2 | መሳሳይና ተቃራኒ ትርጉም ያላቸውን ቃላት በአንድ ላይ እመድባቸዋለሁ:: | | | | |
| 3 | አዳዲሶቹን ቃላትካየሁዋቸው ቦታ ጋር (ለምሳሌ፦ መጽሀፍ ፣ ሰሌዳ፣ ቪድዮ ቤት፣ ወዘተ.) ጋር አያይዤ ለማስታወስ እሞክራለሁ | | | | |
| 4 | አዳዲስ የአማርኛቃላትንከስዕሎችጋርአያይዤለማስታወስእሞክራለሁ | | | | |
| 5 | አዳዲስ ቃላትን ለማስታወስ እንድችል ዓረፍተነገር እሰራባቸዋለሁ | | | | |
| 6 | አዲስ የተማርኩትን ቃል የድርጊት ሲሆን እለማመዳለሁ ለምሳሌ" ሮጠ"የሚለውን ቃል በመሮጥ ወይም እየሮጥኩ እለማመዳለሁ | | | | |
| 7 | የተማርኩቸውን አዳዲስ ቃላት እርስ በርሳቸው በማቀናጀት ወይም በአዲስ መንገድ እንደገና በማቀናበር ዓረፍተነገሮችን እየመሰረትኩ እለማመዳለሁ | | | | |
| 8 | አዳዲስ ቃላቶች ሲያጋጥሙኝ ምስል ከሳች በሆነ መንገድ እየደጋገምኩ አጠናለሁ | | | | |
| 9 | አዳዲስየአማርኛቃላትን ለማስታወስደጋግሜእናገራቸዋለሁወይምእጽፋቸዋለሁ | | | | |
| 10 | በቴፕ ቀድቼ በማዳመጥና በአእምሮየ ውስጥ ደጋግሜ በማመላለስ አጠናለሁ | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 11 | ንግግር ሳዳምጥ ወይም ሳነብ ያጋጠሙኝን ቃላት ፍቺ ለማወቅ መዝገበ ቃላት እጠቀማለሁ | | | | |
| 12 | ፍቹን ሊነግሩኝ የሚችሉ ሰዎችን እንደ መምህራን ፣ ጓደኞቼን፣ ወዘተ. እጠይቃለሁ | | | | |

| ተ.ቁ | የቃላት መማር ብልሃቶችን የተመለከቱ ጥያቄዎች | ምርጫዎች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 13 | አዲስ ያወኩትን ቃል ወደ ኦሮምኛ ቋንቋ በመተርጎም ለምሳሌ "ነብር" የሚለውን ቃል "ቄሬንሳ"በማለት እተረጉማለሁ | | | | |
| 14 | በአጻጻፍ አንድ ሆነው በንበት በሚለያዩ ቃላት (ለምሳሌ፣ጠብቀውና ላልተው በሚነበቡ) ላይ ልምምድ አደረጋለሁ | | | | |
| 15 | አዳዲስና ለእኔ ጠቃሚ ናቸው ብየ የምገምታቸውን ቃላት በልዩ ማስታወሻ ደብተሬ አደራጅቼ እይዛለሁ | | | | |
| 16 | መጽሀፍትን፣ጋዜጦችን፣ወጎችንናመጽሔቶችን በማነብበት ጊዜ የሚያጋጥሙኝን እንግዳወይም አዳዲስ ቃላትን ከስራቸው በማስመርና ምልክት በማድረግ ካለፍኩ በሁዋላ በመጨረሻ ፍቻቸውን እፈልጋለሁ | | | | |
| 17 | የቃላት እውቀቴን ለማዳበር በሚል አላማ የራዲዮ፣ የቴሌቪዥን ፕሮግራም እከታተላለሁ | | | | |
| 18 | በንባብ ሂደት (ለምሳሌ፣ ጋዜጣ፣ መጽሔት፣ መጽሀፍ፣ ወዘተ.) ሳነብ የሚያጋጥሙኝን አዳዲስ ቃላት ፍቺ ለመረዳት የህይወት ልምዴን | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ወይም አጠቃላይ እውቀትን በመጠቀም፣የቃላትን ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ በመፈለግና የቃል ክፍሉን በመመልከት ከአገባባቸው እገምታለሁ | | | | |
| 19 | መጽሀፍ፣ ጋዜጣ ሳነብ የሚያጋጥሙኝን አዳዲስ ቃላት ከአገባባቸው ለመገመት እሞክራለሁ | | | | |
| 20 | የፊትለፊት ንግግር ሳዳምጥ አዳዲስ ቃላት ሲያጋጥሙኝ ፍቻቸውን ከተናጋሪው የአካል እንቅስቃሴ (ለምሳሌ ፈገግታ፣ መኮሳተር፣ እጅ ማወራጨት ) ለመገመት እሞክራለሁ | | | | |
| 21 | የቃላት እውቀቴን ለማሳደግ የአማርኛ ቃላትን ትኩረት ሰጥቼ በአላማ ለመማር እንዲሁም ለመለማመድ እቅድ አዘጋጃለሁ | | | | |
| 22 | የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን የምማርበትን (ከቃላት ትምህርቱ የምጠብቀውን) የራሴን አላማና ግብ አዘጋጃለሁ | | | | |
| 23 | የአዳዲስ ቃላትን ፍች ለመረዳት የተከተልኩት መንገድ ትክክለኛ ወይም የተሳሳተ መሆኑን በማረጋገጥ ስህተቴን በራሴ እለያለሁ | | | | |
| 24 | በቃላት ትምህርትጊዜበየወቅቱ ማሻሻል አለማሻሻሌን ለማረጋገጥ ራሴን እገመግማለሁ | | | | |

| ተ.ቁ | የቃላት መማር ብልሃቶችን የተመለከቱ ጥያቄዎች | ምርጫዎች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 25 | የቃላት ትምህርት ወይም ጥናት ከመጀመሬ በፊት አወንታዊ በሆነ መንገድ (ለምሳሌ ቀልድ ፈጥሬ ሊሆን ይችላል) አካልና አእምሮየን አዝናናለሁ | | | | |
| 26 | የቃላትን መልመጃዎች ከመስራቴ በፊት በተለያየ ዘዴ ራሴንአዝናናለሁ | | | | |
| 27 | በቃላት ትምህርት ውጤታማ ስሆን ለምሳሌ የቃላት እውቀቴ መሻሻሉን ሳውቅ፣ወይም በቃላት ፈተና የተሻለ ውጤት ሳመጣ እራሴ በራሴ አደንቃለሁ | | | | |
| 28 | የቃላት ትምህርት ስማር ለአዳዲስ ቃላት የምሰጣቸው ፍችዎች ትክክል ላይሆኑ ቢችሉም በትምህርት ሂደት መሳሳት ያለ በመሆኑ ያለምንም ፍርሃት ሙከራየን እቀጥላለሁ | | | | |
| 29 | የቃላት ችሎታየን ለማሻሻል ከክፍል ጓደኞቼ ጋር በመሆን በቡድን እወያያለሁ | | | | |
| 30 | ስለአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ባህልና የአኗኗር ስርዓት ለማወቅ የቴሌቪዥን፣ ሬዲዮ ፕሮግራም እከታተላለሁ | | | | |

## አባሪ 2፡- ለአስረኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበ ቃለመጠይቅ

1. የአማርኛ ቃላትን ከተማራችሁ በሁዋላ ቃላትን ለመማርና ለማስታወስ የምትጠቀሟቸው ስልቶች ምን ምን ናቸው?እንደትስ ትጠቀማላችሁ?

2. የአማርኛ ቋንቋ የቃላት ዕውቀታችሁን ለማዳበር ጥረት አድርጋችኋል? ምላሻችሁ “አዎን” ከሆነ ምን ምን ተግባራት አከናወናችሁ?

3. የአማርኛ ቃላት እውቀታችሁን ለማዳበር ከመማሪያ ክፍል ውጭ ምን ምን የአማርኛ ጽሁፎችን ታነባላችሁ? የምታነቡት አንዳንድ ጊዜ ነው ወይስ ሁልጊዜ ነው? በይበልጥ የምታተኩሩት በየትኛው ላይ ነው? ለምን?

4. የአማርኛ ቋንቋ የቃላት እውቀታችሁን ለማዳበር ምን ምን ፐሮግራሞችን አዳምጣችሁ ታውቃላችሁ? የምታዳምጡት ሁልጊዜ ነው ወይስ አንዳንድ ቀን?

5. የተለያዩ መጽሀፎችን ስታነቡ፣ የሰዎችን ንግግር ስታዳምጡ ፍቻቸውን የማታውቋቸውን አዳዲስ ቃላት ስታገኙ ምን አይነት ዘዴ ትጠቀማላችሁ?

6. የቃላት እውቀታችሁ ለማዳበር አዳዲስ ቃላትን የምታጠኑበት ፐሮግራም አውጥታችኋል? የምታጠኑት በየዕለቱ ነው ወይስ በየሳምንቱ ነው?

7. የአማርኛ ቋንቋ ጽሁፎችን ስታነቡ የምታገኟቸውን አዳዲስ ቃላት ትርጉም በሚሰጡ ዐረፍተነገሮች ውስጥ በማስገባት ጭውውት ንግግር ወይም ምልልስ እያደረጋችሁ ትለማመዳላችሁ? ይህን ማድረጋችሁ ለምንድነው?

8. የቃላት እውቀታችሁን ለማሳደግ ከላይ ከተጠቀሱት አጋዥ ቃላትን የመማር ብልሃቶች በተጨማሪ የተጠቀማችሁባቸው ብልሃቶች አሉን ካሉ ምን ምን ናቸው?

9. የእናንተ የቃላት እውቀት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መሄድ አለመሄዱን ለማረጋገጥ ሞክራችሁ ታውቃላችሁ? በምን መልኩ ነው ማረጋገጥ የምትሞክሩት?

10. በክፍል ውስጥ በቃላት ትምህርት ንቁ ተሳትፎ ስታደርጉና ጥሩ ውጤት ስታመጡ ራሳችሁን ታደንቃላችሁ? እንዴት ነው የምታዴንቁት?

**ውድ የትምህርት ጊዜዎን ሰውተው ላደረጉልኝ ቀና ትብብር በድጋሜ**
**ከልብ የመነጨ ምስጋናየን አቀርባለሁ።**
**ያሲን አደም**

## አባሪ 3፡- በኦሮምኛ ቋንቋ የቀረበ የጽሁፍ መጠይቅ

Yuunivarsitii Addis Ababaa

Kolleejjii Qo'annaa Afaanota Hiyuumaanitii.Gaazeexessaa fi Waligaltee/Waligalumsaa/

Kutaa Barnoota Og-barruu fifiookloorii Afaan Amaariffaa

Gaaffi barreeffamaa Barattoota Kutaa Kudhan Tinguutamu

Barattoota:- Kaayyoon gaaffi baarreeffamaa kanaa inniguddaa barattoota Kutaa10ffaa afaan oromoon afaan dhalootaa Keessan tae jechoota afaan amaarifgaa barathuuirrataa Jechoota fayyadam tan qoorannoo malleen fayyadama jechootaa qoorachuuf adeemsiifamuKanaaf ragaassaabuuf yaadameeti Ragaan isiniraa argamu kun immoo faayidaa qoorannooKanaaf yaadameen ala akka hin Oolle nan mirkaneessa Deebii yommuu Lattan maalummaaficha xiiyyeeffannoodhaan duubbistanii, ajaja irratti hundaa uun deebii sirrii tae akka guuttan kabajiaan siniin gaafadha , Gargaarsa Keessaniif immoo baayeen galateeffadha .

Hubachisa:- 1 ,Gaafii barreeffamaa Kanarratti maqaa barreessuu hin barbaachisu.

2, Raqaa sassaa bamurratti rakkoo waan Uumuuf iriyaa waliin ta'anii gutuun,ykn guuchisiisuu hin Eeyyamamu.

Kutaa Tokko:- Ragaa dhuunfaa

Kutaa ……………………………………….Daree……………………………………

Umrii……………………………………….

Saala……………………………………………..

Afaan dhalootaa…………………………………………………

Kutaa Lammaffaa: - Gaaffii barreeffamaa mallen foyyadama jechotaa ilaallatu.

Seera:- Yaadoota malleen jechoota haraa barachuuf fayyada akkarmaa gaditti dhiyaataniiru.

Yaadoota jiran xiyyeeffannoon dubbistee itti fayyadama kee itaalchisee mala dhiyaate, yeroo hunda, yeroo tokko tokoo, darbeedarbee, goonkumaa jedhan keessaa tokko gafa firach uunsaanduqa Keennameerratti mallattoo"X" kaa uun deebii kenni Barattota yaadoota dhihaata yaadoota dhihaatan hundaaf deebii sirrii tae ykn deebii dogoon goraa ta e sirriin deebii ati amanamummaadhaan filattee guutte qofa, kanaafuu, daree keessaa waan hin taaneef fayy-qormaata adama jechaa kan kee isadhugaafilachuun deebisi,filannoowwan gabatee keessa kaa aman Kan ibsan:-

4, yeroo hunda Nan fayyadama

3, yeroo tokko tokoo Nan fayyadama

2, Darbee darbee Nan fayyadama

1, Goon kumaa hin fayyadamu

| Lakk | Gaaffilee malleen fayyadama jechootaa ilaallatu, | filannoowwan | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1 | Jechoota amaariffaa erga baradheen booda, jechoota garee garee isaaniitin fkn, maqaa garee tokkoon,maq-ibsootaafi xumuura garee kan biro waliin akkasumas,jechoota liika faallaafiwal-fakkaataa qaban bakka tokkonan ramada | | | | |
| 2 | Jechoota haraa iddoo isaaniitti arge waliin (fkn,kitaaba,gabatee,mana filmii fikik,f) warqabsiisee yaadachuu nan yaala | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 3 | Jechoota haraa baradhe duubbiidhaanifi barreeffamaan nan shaakala | | | | |
| 4 | Yeroo dubbisuurraffi fkn (kitaaba,gaazeexaa fibarree ffama adda addaa) yommuu dubbisu jechoota harraa na quunnaman hika fallaa fihiika war-fakkaataa barbaaduun, garee jechaa isaanii iraaluun akkasumas beekumsa kanaan dura qabu fayyadamuun hiika galuumsa isaanii nan tilmaama | | | | |
| 5 | Jechoota haraa afaan amaariffaa fakkii waliin war-qabsiisee yaadachuu nan yaala | | | | |
| 6 | Jechoota haraa yaada akka nadandeessisu hima ittin ijaara | | | | |
| 7 | Jecha haraa baradhe qochaan agarsiisuudhaan nan shaakala fkn (Jecha" fige" jedhu fiquudhaan nan shaakala) | | | | |
| 8 | Jechoota baradhe irra deddeebin irradeebin irradabi ee nan dubbisaykn nan yaadadha | | | | |
| 9 | Jechoota harra irra deddeebiin nan qo adha | | | | |
| 10 | Jechoota harra afaan amaariffaa yaadachuudhaaf irra deddeebisee nan dubbadhaa yknna barreessa | | | | |
| 11 | Teeppiidhaan waraabee dhaggeeffachuunii fisammuudhaa irradeddeebisee yaaduchuun nan qo adha | | | | |
| 12 | Dubbii dhaggeeffachuu fidubbisuurratti Jechoota na quunnaman hiika isaanii beekuu dhaaf galmee jechoota ykn dikshiiranii nan | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | fayyadama | | | | |
| 13 | Namoota irraa fkn (barsiisaa, hiriyaa,fik,k,f,)nan gaafadhan | | | | |
| 14 | Jecha haraa hiika jaa beeku gara afaan oromoffi fkn (‘’ነብር” kan jedhu qeerransa jechuun )nan hikan | | | | |
| 15 | Jechoota barree ffamaan tokko ta anii dubbisuurratti gar gar ta’an(laaffisanii fijaabeeffamanii duubbiifaman) irratti nan shaakala | | | | |
| 16 | Jechoota haraa ta’aniifi na fayyadajedhee yaadu yaadanno dhuunfaa kiyyarratti nan qabadha | | | | |
| 17 | Kitaaboota og-barruuleefi gaazeexaa adda addaa yommmuu dubbisu jechoota haraa na quunnaman jala sararuuni fimallattoo itti kaa uun, dhumarrattii hiika isaanii nan barbaada | | | | |
| 18 | Beekumsa kiyya cimsuuf jecha sagantaa reediyoo fitelevizyinii nan hordofa | | | | |
| 19 | Kitaabaa fi barruulee yommuu duubbisu jechoota haraa na quunnama akka galumsa isaaniitin tilmaamuuf nan yaala | | | | |
| 20 | Waliin dubbii yommuu dhaggeeffadhu jechoota haraa na quunnaman hiika isaanii sochii qaamaa (fkn :-fuuli isaani, dheekkamsa, gammachuufi harka sochoosuu)taasiisan irraa ka’ee tilmaamuufnan yaala | | | | |
| 21 | Dandetti kiyya cimsuuf jechoota amaariffaa | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | irratti xiyyeeffachuuii fi kaayyoo godhachuun shaakaluu dhuuf karoora qopheesseen jira | | | | |
| 22 | Kaayyoo fi galma jechoota afaan amaariffaa ittii baradhu nan qopheessa | | | | |
| 23 | Hiika jechoota amaariffaa hubachuuf adeemsi ani hordofe sirriykn dogoongora ta'uu isaa mirkaneessuun dogoon gora kiyya nan hubadha | | | | |
| 24 | Yeroo jecha barannu foyyeessuufi foyyeessuu dhabuu kiyya yeroo yeroodhaan ofegamaggama. | | | | |
| 25 | Jechoota barachuuf ykn qo achuuf osoo hin eegalin dura,adeemsa eeyyantaatin fkni (qosaa tokko,uumee ta'uu danda a) qaamaa fi.sammuu kiyya nan bashannansiisa. | | | | |
| 26 | Gilgaaloota hojjechuun dura mamaqara garaa fayyadamuun of dinqiisiisa | | | | |
| 28 | Barnoota jechaa yommuu baradhu hiika jechoota haraaf kennu sirrii yoo ta uu baatanis barnoota irratti dogoggooruun waan hin dhabamneef soda tokkoo malee yaalii kiyya itti fuufa | | | | |
| 29 | Dandeetti kiyya cimsuuf hiriyoota kiyya waliin ta ee gareen nan mari adha | | | | |
| 30 | Namoota afaan amaaariffaa dubbatan duudhaa fiaadaa isaanii beekuuf sagantaa raadiyoo fi tetevizyinii nan hardofa | | | | |

## አባሪ 4፡- በኦሮምኛ ቋንቋ የቀረበ ቃለ መጥይቅ

Gaaffii Afaanii Barattoota Kutaa 10ffaa tiif Dhiyaatu

1, Jechoota afaan amaariffaa erega barattanii booda jechota barachuuf, akkasumas yaadachuuhaaf malleen fayyadamtan maalmaali?

2, Beekumsa jechoota afaan amaariffaa irratti qabdan cimsuudhaaf yaali gootuu? Deebin keessan eyyea yoo ta'e ,gocha maal maal raawwattan?

3, Beekumsa keessan cimsuuf barnoota dareetin alabarruulee amaariffaa maal maal dubbistu? Yeroo hunda dubbistan mooyeroo tokko tokko dubbistu? isakamirratti irracaalaa xiyyeeffattu?maaliif?

4, Beekumsa jecha amaariffa irratti qabdan cimsuuf sagantaa maal maal dhaggeeffattanii beektuu ?yeree hunda darbee darbee dhaggeeffattu?

5, Barruulee adda addaa yommuu dubbistan dubbiinamootaa yommuu dhaggeeffattanii fijechoota haraa hiika isaaniihin beeknee yommuu argattan malaakkamii fayyadamtuu?

6, Dandeetti keessan cimsuuf sagantaa jechoota harraaitti go,attan baastaniirtuu?Torbee torbeen moo guyyaa guyyaan qo'attuu?

7, Barruulee afaan amaariffaa yommuu dubbistan jechoota haaraa argattan hima keessa galchuun tapha,walindubbiiykn marii gochuudhaan nishaakaltuu?maaliif kan gootuu?

8, Dandeetti keessan cimsuuf malleen jechoota haraa ittibaratamu armaan olitti ibsameen alamalleen itti fayyadamtan kanbiro jiruu?yoo jiraatan maal maali?

9, Beekumsi keessan yeroo irraa yerootti foyya'aa deemuufi deemuu dhabuu isaa hordoof tanii beektuu?haala kamiin mirkaneessituu?

10, Barnoota jechaararatti daree keessa hirmaannaa yommuu gootaniifiqabxii gaarii yommuu galmeessistan of dinqiisistuu? Akkamitti?

Yeroo Barnootaa keessan dhistanii deeggarsa naaf gootaniif galatoomaa.

## አባሪ 5፡- የተተኳሪ ተማሪዎችን ዳራ የሚያሳይ ቅጽ

የትምህርት ቤቱ ስም፡- ሩፍሴ አጠ/2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክፍል ፡- አስረኛ "ሀ"

| ተ.ቁ | የተማሪው ስም | ጾታ | ዕድሜ | ክፍል | የአፍመፍቻቋንቋ | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | አማርኛ | ኦሮምኛ | |
| 1 | አብዱ ሁሴን አሊ | ወ | 21 | 10ኛ | | x | |
| 2 | አሊ ሽፈራው አደም | ወ | 22 | 10ኛ | | x | |
| 3 | አሚናት ሙሐመድ ብሩ | ሴ | 20 | 10ኛ | | x | |
| 4 | አንሻ ሁሴን ሙሄ | ሴ | 21 | 10ኛ | | x | |
| 5 | አረቡ ሰይድ ገደፋው | ወ | 23 | 10ኛ | | x | |
| 6 | አንዋር አህመድ ኑሩ | ወ | 19 | 10ኛ | | x | |
| 7 | ድኑ መ/ድ በሽር | ወ | 18 | 10ኛ | | x | |
| 8 | ፋጡማ ኑሩ ገመቹ | ሴ | 19 | 10ኛ | | x | |
| 9 | ፎዚያ ሙህድን | ሴ | 19 | 10ኛ | | x | |
| 10 | ሀፊዝ ሙሃመድ ሁሴን | ወ | 20 | 10ኛ | | x | |
| 11 | ሁሴን እብራሂም | ወ | 21 | 10 | | x | |
| 12 | ሰኪና ሁሴን ኡመር | ሴ | 22 | 10 | | x | |
| 13 | ጀሚላ አሊ አህመድ | ሴ | 21 | 10 | | x | |
| 14 | ካውለት ዳውድ ፋሪስ | ሴ | 23 | 10 | | x | |
| 15 | ከድጃ አህመድ አሊ | ሴ | 21 | 10 | | x | |
| 16 | ከሚሳ መ/ድ ጀማል | ሴ | 18 | 10 | | x | |
| 17 | ካውለት እንድሪስ ተሰማ | ሴ | 18 | 10 | | x | |
| 18 | ካውለት ሁሴን አደም | ሴ | 19 | 10 | | x | |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 19 | ካውለት ሙሄ በላይ | ሴ | 21 | 10 | | x | |
| 20 | ሉባባ ሙ/ድ ዳውድ | ሴ | 20 | 10 | | x | |
| 21 | መ/ድ እንድሪስ ሁሴን | ወ | 19 | 10 | | x | |
| 22 | ማኢዳ አሊ ሰይድ | ሴ | 20 | 10 | | X | |
| 23 | መዲና አሊ ሰይድ | ሴ | 21 | 10 | | x | |
| 24 | መዲና አቡበከር ኑሩ | ሴ | 19 | 10 | | x | |
| 25 | ኡስማን እንድሪስ ያሲን | ወ | 18 | 10 | | x | |
| 26 | ራቢዓ እንድሪስ ሉሌ | ሴ | 19 | 10 | | x | |
| 27 | ራቢዓ ጀማል ሙ/ድ | ሴ | 20 | 10 | | x | |
| 28 | ራቢዓ ከማል የሱፍ | ሴ | 19 | 10 | | x | |
| 29 | ራውዳ ኑሩ ሙሄ | ሴ | 19 | 10 | | x | |
| 30 | ስዓዳ ሙ/ድ አማን | ሴ | 18 | 10 | | x | |
| 31 | ሰሚራ ከማል ቢሻው | ሴ | 19 | 10 | | x | |
| 32 | ሲራጅ ሙ/ድ ሃሰን | ወ | 21 | 10 | | x | |
| 33 | ዘምዘም ሀቢብ ዋሴ | ሴ | 19 | 10 | | x | |
| 34 | ሪሃና የሱፍ ሰይድ | ሴ | 19 | 10 | | x | |
| 35 | ከቢር ከማል ተሰማ | ወ | 23 | 10 | | x | |
| 36 | ሙዘየን ኑሩ ሃቢብ | ወ | 24 | 10 | | | |
| 37 | ሙስጠፋ ዋሱ አሊ | ወ | 25 | 10 | | | |
| 38 | ሲራጀ ገመቹ ጣባ | ወ | 22 | 10 | | | |

## የት/ቤቱ ስም ሩፍሴ አጠ/2ኛ ደረጃ ት/ቤት

## ክፍል 10ኛ ለ

| ተ.ቁ | የተማሪውስም | ጾታ | እድሜ | ክፍል | የአፍመፍቻቋንቋ | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | አማርኛ | ኦሮምኛ | |
| 1 | ታደሰ ደጉ ሞላ | ወ | 23 | 10ኛ | | x | |
| 2 | ዋሱ አበበ ደረጀ | ወ | 21 | 10ኛ | | x | |
| 3 | ሀሰን አህመድ እውነቱ | ወ | 24 | 10ኛ | | x | |
| 4 | ይማም ሀሰን ሞቲ | ወ | 21 | 10ኛ | | x | |
| 5 | አበበች አህመድ ደረጀ | ሴ | 22 | 10ኛ | | x | |
| 6 | ሙኒራ ሰይድ አበዱ | ሴ | 23 | 10ኛ | | x | |
| 7 | ሰለሞን ብሩ ከድር | ወ | 20 | 10ኛ | | x | |
| 8 | ዛኪር ዳውድ ሞላ | ወ | 24 | 10ኛ | | x | |
| 9 | አሚናት ጀማል | ሴ | 19 | 10ኛ | | x | |
| 1-0 | አበራሽ መሄ ዳውድ | ሴ | 23 | 10 | | x | |
| 11 | መኮነን በላይ ተሰማ | ወ | 21 | 10 | | x | |
| 12 | ጁሃር ሰይድ በላይ | ወ | 21 | 10 | | x | |
| 13 | በላይ ሃሰን ሀቢብ | ወ | 23 | 10 | | x | |
| 14 | ቢላል የሱፍ ገዱ | ወ | 22 | 10 | | x | |
| 15 | ሙክታር ኑሩ በድሩ | ወ | 23 | 10 | | x | |
| 16 | ኢዘድን ሀሰን አደም | ወ | 21 | 10 | | x | |
| 17 | ሂክማ አበዱ ደሰታው | ሴ | 21 | 10 | | x | |
| 18 | መሀድን አሊ ሰይድ | ወ | 23 | 10 | | x | |
| 19 | ሀሊማ አበዱ ዋሱ | ሴ | 18 | 10 | | x | |
| 20 | ሁሴን አሊ ወራቂ | ወ | 21 | 10 | | X | |
| 21 | ቃሲም አህመድ አሊ | ወ | 23 | 10 | | x | |
| 22 | አስማረ ዳውድ | ወ | 21 | 10 | | x | |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 23 | ፈቃዱ በሪሁን | ወ | 20 | 10 | | x | |
| 24 | ደስታው ብሩ ገድፌ | ወ | 21 | 10 | | x | |
| 25 | መሰረት ኢሱ ከድር | ሴ | 24 | 10 | | x | |
| 26 | ዘነበችወዳጆ ተመሰገን | ሴ | 23 | 10 | | x | |
| 27 | መልካሙ አለበን ብሩ | ወ | 22 | 10 | | x | |
| 28 | ከድጃ ሞላ ገዱ | ሴ | 19 | 10 | | x | |
| 29 | ሀያት ሱልጣን ሰይድ | ሴ | 21 | 10 | | X | |
| 30 | ተውፊቅ ቢላል መ/ድ | ወ | 19 | 10 | | x | |
| 31 | በደሩ ሁሴን አሊ | ወ | 20 | 10 | | x | |
| 32 | ያሲን አህመድ ሙሄ | ወ | 21 | 10 | | x | |